# ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ

## መሪ ጥቅሶች

መሳ. 4፥4 :- የእስራኤል መሪና ፈራጅ /መስፍን/ የነበረችው ነቢይቱ ዲቦራ

የሐዋ. 1፥14፥ 2፥1-4፥16-18፥ 21፥8-9 :- መንፈስ ቅዱስና የትንቢት ስጦታ ለሴቶችም ጭምር ናቸው።

ሮሜ 16:1፥ 7 :- ፌቤን ዲያቆን ነበረች። ዩልያን ደግሞ ሐዋርያ ነበረች።

1ቆሮ. 11፥3-16 በተለይ ቁ.5 :- ሴቶች በቤተክርስቲያን ይጸልዩ፥ ትንቢትም ይናገሩ ነበር።

1ቆሮ. 14፥26-40 በተለይ ቁ. 26፥34-35 :- ሴቶች ጉባዔውን ያውኩ ነበር።

ገላ. 3፥26-28 :- ወንድም ሆነ ሴት በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው።

1ጢሞ. 2፥11-15 :- ሴቶች እንዲያስተምሩ ወይም በወንድ ላይ የበላይ እንዲሆኑ አልተፈቀደም።

1ጢሞ. 3፥11-13 :- ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ሥራ ነበራቸው።

## በቤተክርስቲያን ውስጥ የሴቶች ሥራ ምንድነው?

አብዛኛውን የቤተክርስቲያን ታሪክ ስንመለከት ሴቶች ቤተክርስቲያንን የመምራት መብት አልነበራቸውም። ብዙውን ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰብኩት፥ የሚያስተምሩትና በመጋቢነት የሚመሩት ወንዶች ነበሩ። ያም ሆኖ አልፎ አልፎም ቢሆን በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች ሴቶች በቤተክርስቲያን ያስተምሩ ወይም ይመሩ ነበር። ከአለፉት ጥቂት ምዕተ-ዓመታት ወዲህ ግን ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ በመስበክ፥ በማስተማርና በመጋቢነት በማገልገል ያላቸው ተሳትፎ በአያሌው እየጨመረ መጥቶአል። ይህም የሆነው የሴቶችን መብትና ነፃነት ለማስከበር የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ዓለማዊ ማኅበሮች በተቋቋሙበት ጊዜ ነው።

ለመሆኑ ሴቶች በቤተክርስቲያን መሪነት ስላላቸው ስፍራ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? በጣም ግልጽ አይደለም። ምንም እንኳ እንደወንጌል መልእክተኛ ሚሲዮናዊ እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ቢፈቅዱላቸውም አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲሰብኩ ወይም እንዲመሩ አይፈቅዱም። በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ ብዙ አብያተክርስቲያናት ሴቶች እንዲሰብኩ፥ እንዲያስተምሩና ሌላው ቀርቶ መጋቢዎችና ኤጲስ ቆጶሳት እንኳ እንዲሆኑ እየፈቀዱ ነው።

## በቤተክርስቲያን የሚጸልዩና ትንቢት የሚናገሩ ሴቶች

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በክርስቶስ እኩል መሆናቸውን ጳውሎስ በገላትያ 3፥28 በግልጽ ሁኔታ ጽፎአል። ሁላችንም የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያስፈልገን ኃጢአተኞች ነን። እንዲያውም የምዕራቡ ዓለም ክርስቲያኖች የባሪያ አሳዳሪ እንዳይሆኑ፥ ሥርዓትን ለመቃወምና ትግሉንም ለመደገፍ ገላ. 3፥28 ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጎአል። ምንም እንኳ ወንዶችና ሴቶች በክርስቶስ አንድ ቢሆኑም በማንኛውም ገጽታቸው አንድ ዓይነት ናቸው ማለት አይደለም። እርግጥ ነው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው፤ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ድርሻ ግን ሊለያይ ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታም ባልና ሚስት

አንዳቸው ላንዳቸው መገዛት ቢኖርባቸውም በጋብቻ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ግን ሊለያይ ይችላል። (አጠቃላይ መግለጫ፥ ክርስቲያናዊ ጋብቻ በሚለው ሥር ኤፌ. 5፥21-23 ይመለከቷል)።

መንፈሳዊ ኃይልን ሊሰጣቸው መፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ደቀመዛሙርት ላይ በጴንጠቆስጤ ቀን በወረደበት ዕለት፣ ወንዶችም ሴቶችም በአንድነት እንደነበሩ የሐዋ. ምዕራፍ 1 እና 2 ግልጽ አድርጎታል። እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች መንፈሱን እንደሚያፈስና ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ትንቢት እንደሚናገሩ በዚሁ ዕለት ጴጥሮስ ኢዮኤልን ጠቅሶ አመልክቶአል (ኢዮ. 2፥28-29፤ የሐዋ. 2፥16-18)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ብዙ ሴት ነቢያት ነበሩ (ዘፀ. 15፥20፤ መሳ. 4፥4፤ 2ነገ. 22፥14፤ ነህ. 6፥14፤ ኢሳ. 8፥3)። በአዲስ ኪዳንም ወንጌላዊው ፊሊጶስ ትንቢት የሚናገሩ አራት ሴት ልጆች ነበሩት(የሐዋ. 21፥8-9)።

በ1ቆሮ. 12፥11 ደግሞ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለወንዶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ስጦታን እንደሚሰጥ ተስማምቶአል። እንዲሁም በ1ቆሮ. 11፥5 በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚጸልዩና ትንቢት ስለሚናገሩ ሴቶች ተናግሮአል። በቤተክርስቲያን የሚጸልዩና ትንቢት የሚናገሩ ሴቶች ራሳቸውን መከናነብ እንዳለባቸው ሲናገር ሴቶች በቤተክርስቲያን መጸለይና ትንቢት መናገር እንደሚችሉ በግልጽ ማመልከቱ ነው። ሁሉም በቤተክርስቲያን አገልግሎት መሳተፍ እንደሚችሉ ሲናገር (1ቆሮ. 14፥26) ይህ አባባሉ ሴቶችንም እንደሚጨምር ጥርጥር የለበትም።

## ሴቶች በዲቁና እና በሌሎችም ሥራዎች

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሴቶች በዲቁና እንዲያገለግሉ ብዙዎች ይስማሙበታል። በ1ጢሞ. 3፥8-13 ጳውሎስ ስለ ወንዶችና ባሎች ጽፎአል። በቁጥር 11 ደግሞ ስለሴቶች ይጠቅሳል። እዚህ ላይ ስለሴቶች ሲጠቅስ ሁለት ዓይነት ሴቶች ይታሰቡናል። «ስለሚስቶች» ወይም «ስለ ሴት ዲያቆናት» ሊሆን ይችላል፣ ስለየትኞቹ እንደሆነ ግን አስረግጦ መናገር አይቻልም። በሮሜ 16፥1 ላይ ጳውሎስ ፌቤን ስለምትባል ሴት አንስቶ አመስግኗታል፤ እንዲሁም አገልጋይ ወይም «ዲያቆን» ብሎአታል። (እዚህ ላይ «አገልጋይ» የሚለው ቃል በግሪክኛው[1] «ዲያቆን» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው)።

በሮሜ 16፥ 3፤ 6፤ 12 እና ፊል. 4፥2-3 ጳውሎስ የሥራ አጋሮቹ ለሆኑ ሴቶች ሰላምታ ሲያቀርብ እንመለከታለን። ጵርስቅላና ባልዋ አቂላ ብዙውን ጊዜ በአንድነት ይጠቀሳሉ፤ የማስተማር አገልግሎቱንም በጋራ ያደርጉ እንደነበረ ይመስላል (የሐዋ. 18፥18፤ 26)። በተጨማሪም በሮሜ 16፥7 ላይ ጳውሎስ «ዩሉያን» የሚላት ሴት እንጂ «ዩኒጁስ» የሚል የወንድ ስም እንዳልሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ተስማምተውበታል። (የግሪክኛው ቃል ተባዕታይ ወይም አንስታይ ሊሆን ይችላል) የሚናገረው ስለሴት ከሆነ ደግሞ ይህችኑ ሴት «ሐዋርያ» ብሏታል።

## ሴት መሪዎች

ምንም እንኳ ሴቶች ዲያቆን መሆን ቢችሉም በመጋቢነት ደረጃ ቤተክርስቲያንን መምራት ይችላሉ ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳል። መጻሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ በጣም ግልጽ መልስ አይሰጥም፣ ስለሆነም በዘመናችን ያሉ አብያተክርስቲያናት የተለያየ አመለካከት አላቸው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ከ1ቆሮ. 14፥33-35 እና 1ጢሞ. 2፥11-15 ሴቶች ዝም እንዲሉ እንጂ እንዲያስተምሩ ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዳይኖራቸው የሚናገረውን ይጠቅሳሉ። እነዚህ ቁጥሮች በማያሻማ ሁኔታ ነው የሚናገሩት፣ ብዙ አብያተክርስቲያናት ሴቶች ሕፃናትንና ሌሎች ሴቶችን እንዲያስተምሩ ቢፈቅዱም ወንዶችን እንዲያስተምሩ ግን አይፈቅዱላቸውም። በአመዛኙ እነዚህ አብያተክርስቲያናት ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲጸልዩ ወይም ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ይፈቅዳሉ፤ አብዛኞቹም ሴት ሚሲዮናውያን በአዳዲስ አብያተክርስቲያናት ወንዶችን እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ይፈቅዳሉ።

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች የሚተረጉሙዋቸው በተለየ መንገድ ነው። ጳውሎስ ሴቶች ዝም እንዲሉ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈበት ወቅት በዚያው መልእክቱ ሴቶች ሲጸልዩና ትንቢት ሲናገሩ ራሳቸውን መከናነብ እንዳለባቸው አመልክቶአል (1ቆሮ. 11፥5)። ስለዚህም ይላሉ እነዚህ ክርስቲያኖች... ስለዚህም የ1ቆሮ. 14፥34-35 ያለው ትርጓሜ ሴቶች «ሙሉ በሙሉ ጸጥ» እንዲሉ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ውስጥ «ሁከት» መፍጠር ወይም «መጮህ» የለባቸውም ለማለት የተናገረው ነው ይላሉ። ምናልባትም በጳውሎስ ዘመን የነበሩ ሴቶች በአምልኮ ፕሮግራም መሀል በቤተክርስቲያን ውስጥ ጮክ ብሎ ባሎቻቸውን የመጠየቅና የመጣራት ልማድ ሊኖርባቸው ይችላል።

በተመሳሳይ ሁኔታም እነዚህ በሁለተኛው ምድብ ያሉ ክርስቲያኖች በ1ጢሞ. 2፥11-15 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ያልተማሩ ሴቶች መገዛትና መማር እንጂ የወንዶችን ሥልጣን መሻማት እንደሌለባቸው ያሳስባል ብለው ያምናሉ። የተማረችና ለማስተማር ለምትበቃ ሴት ሥልጣንን የመስጠቱ ጉዳይ የሚወሰነው

[1] መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነው።

ግን በቤተክርስቲያን መሆኑን ያምናሉ። በብሉይ ኪዳን መጽሐፈ መሳፍንት የተጠቀሰችው ዲቦራ በእግዚአብሔር ፈቃድ አይሁድን የመሩ ሴት ነቢያት ዓይነተኛ ምሳሌ ናት (መሳ. 4፥4)።

ሦስተኛው ዓይነት የክርስቲያኖች ቡድን ደግሞ ጳውሎስ የተናገረው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ጢሞቲዎስን፥ የቆርንቶስንና የኤፌሶንን አብያተ ክርስቲያናት ብቻ የሚመለከት እንደሆነ ያምናሉ። ጳውሎስ ፍጹም ልዩ ባሕል ላላቸው ለዘመናችን አብያተክርስቲያናት ይህን እንዳልተናገረ ያምናሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ጳውሎስ ባሪያ የነበረውን አናሲሞስን መልሶ ወደጌታው ቢሰደውም ባርነትን መደገፉ አልነበረም፤ ባርነትን ቢደግፍማ ኖሮ ነፃ እንዲያወጣው ለፊልሞና አይጽፍለትም ነበር፤ በማለት የጳውሎስን ምሳሌነት ያመለክታሉ (ፊል. 17–21)። ጳውሎስ በክርስቶስ ፍርሃት አንዳችን ለሌላው እንድንገዛ ጽፎአል፤ ይህን ማድረግ ያለባቸው ሴቶች ብቻ አይደሉም (ኤፌ. 5፥21)። ኢየሱስ የባሕልን ገደብ በማፍረስ ሁሉንም ነፃ አውጥቶአል። ማኅበረሰባቸው ለሴት ነፃነትን የሚሰጥ ከሆነ የማያምኑ ሰዎች ለሴቶች መሪነት ሥልጣንን ቢሰጥ አይቃወሙም። ስለዚህ እነዚህ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ለሴቶች የመሪነት ሥፍራ ልትሰጥ ይገባል ብለው ያምናሉ።

ሁለት ወይም ሦስት ጥቅሶችን ስንመለከት ግልጽ የሚመስለንን ያህል ጉዳዩ ግልጽ አይደለም። ውሳኔያችን ምንም ይሁን ምን ያለን አመለካከት የተለያየ አመለካከት ካላቸው በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሊለየን አይገባም። ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፤ በአገልጋይና በጌታ፤ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም (ገላ. 3፥28)።

# ሕፃናትና የእግዚአብሔር መንግሥት

## መሪ ጥቅሶች

ዘፍ. 17፥10-14 - የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ይገረዝ።

መዝ. 22፥9-10 - የእናቴን ጡት በምጠባበት በሕፃንነቴ ወራት እንኳ በአንተ እንድታመን አደረግኸኝ።

መዝ. 51፥5 - ኃጢአተኛ ሆኜ እንደተወለድሁ ታውቃለህ፤ ከተፀነስሁበት ጊዜም ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ።

ማቴ. 18፥2-6 - ሕፃን ጠርቶ በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾች . . .

ማቴ. 21፥15-16 - ከልጆችና ከሚጠቡት ሕፃናት አፍ ምስጋናን ለአንተ አዘጋጀህ።

ማር. 10፥14-16 - ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ ተው አትከልክሉአቸው። የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ላሉት ናት።

ሉቃ. 1፥15 - በእናቱ ማሕፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ይሆናል።

የሐዋ. 2፥38-39 - የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነው።

## ጥያቄው

ለመዳን ማመንና መጠመቅ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል (ማር. 16፥16)። ኃጢአታችን እንዲሰረይልን ንስሐ መግባትና መጠመቅ እንዳለብንም ታዝዘናል (የሐዋ. 2፥38)። በልባችን እንድናምን በአፋችንም እንድንመሰክር ተነግሮናል (ሮሜ 10፥9-10)። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳለው በዮሐ. 3፥16 ተነግሮናል።

እዚህ ላይ ግን መናገር የማይችሉ ሕፃናት ዕጣስ ምን ሊሆን ነው? የሚል ጥያቄ ይነሣል። በትክክል ንስሐ ሊገቡ፥ ሊያምኑ፥ እምነታቸውንም በአፋቸው ሊመሰክሩ ይችላሉን? ይህን ማድረግ ካልቻሉ ታዲያ እንዴት መዳን ይችላሉ? ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ይነሣል፥ አንድ ሕፃን ቢሞት ወዴት ነው የሚሄደው? ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይስ ወደ ገሃነም? መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ መልስ ስለማይሰጠን ጥያቄዎቹ ከባድ ናቸው። ሕፃናትንና የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ ጥቂት ጥቅሶች ተሰጥተዋል፤ ያም ቢሆን በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ነው።

## ሕፃናት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ይላል (ሮሜ 3፥23፥ 5፥12)። ዘማሪው ደግሞ ከተወለደ በኋላ ብቻ ሳይሆን ገና በእናቱ ማሕፀን ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛ መኖኑን ተናግሮአል (መዝ. 51፥5)። ኢዮብም ተመሳሳይ ነገር ተናግሮአል (ኢዮ. 25፥4)። ስለዚህም ሕፃናት እንኳ ሳይቀሩ ሁላችንም ኃጢአተኛ ባሕርይ እንዳለንና ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ጠላቶች መሆናችንን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። ሰው ሁሉ ከኃጢአቱ እንዲድንና እንዲጸድቅ ከተፈለገ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል።

ከእርሱ ከራሱ ረድዔትና ጸጋ የተነሣ አዲስ የተወለዱ ሕፃናት እንኳ በእግዚአብሔር መታመን እንደሚችሉ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያመለክታል (መዝ. 22፥9-10)። ኢየሱስ ወደ እርሱ እንዲመጣ

አንድን ሕፃን ጠራና በእኔ ከሚያኑ ከእነዚህ ከታናናሾች . . . በማለት ተናገረ (ማቴ. 18፥6)። ከዚህም በተጨማሪ ከሕፃናትና ከሚጠቡ አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ የሚለውን ከመዝሙር 8፥2 በመጥቀስ ተናግሮአል (ማቴ. 21፥16 ይመለከቷል)። አጥማቂው ዮሐንስ ገና በእናቱ ማሕፀን እንዳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላ ለወላጆቹ ተስፋ ተሰጥቶ ነበር (ሉቃ. 1፥15፥ 41–44)። ከዚህ እንደምንረዳው አንዳንድ ሕፃናት በእግዚአብሔር ማመንና መታመንን የሚችሉ ይመስላል።

ወደ እርሱ ከመምጣት ትንንሽ ልጆችን እንዳይከላከሉ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአል፤ እንዲያውም ጸልዮላቸዋል፣ ባርኮአቸዋል (ማር. 10፥13–16)። ይህ ሕፃናትንም ይጨምራል (ሉቃ. 18፥15)። ጨቅላዎችንም የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ላሉት ናትና በማለትም ተናግሮላቸዋል (ማር. 10፥14)። እግዚአብሔር ሕፃናትን በበጎ ዓይን ነው የሚያያቸው። መላእክቶቻቸው ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ (ማቴ. 18፥10)። እዚህ ላይ ግን በመንግሥተ ሰማይ ጠባቂ መላእክት ያሉዋቸው ሁሉም ሕፃናት ይሁኑ ወይም በኢየሱስ የሚያምኑት ብቻ ግልጽ አይደለም (ማቴ. 18፥2–6፤ ማር. 9፥42)።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ ይሆኑ ዘንድ ማንኛውንም ወንድ እንዲገርዙ እግዚአብሔር ለብሉይ ኪዳን አይሁዳውያንን አዝዞአቸዋል። ግርዘቱ የሚፈጸመው ሕፃኑ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ሲሆን ይህ ግርዘት በእግዚአብሔርና በአይሁዳውያን መካከል ለሚኖረው ቃል ኪዳን ምልክት ነበር (ዘፍ. 17፥10–13)። እንዲያውም የማይገረዝ ሕፃን ሁሉ የእግዚአብሔርን ኪዳን ማፍረሱ ስለሆነ «ከወገኖቹ እንደአንዱ ሆኖ አይቆጠርም» ብሎ እግዚአብሔር አዝዟል (ዘፍ. 17፥14)። ስለሴት ሕፃናት ግርዘትም ሆነ ቃል ኪዳኑን በተመለከተ ስለሚጠብቃቸው ዕጣ ግን ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም። ከብሉይ ኪዳን ሕግጋት ነፃ መሆናችንን አዲስ ኪዳን በግልጽ ይናገራል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን አካላዊ ግርዘት አስፈላጊ አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆነው በእምነት እንጂ የአይሁድ ሕግን በመፈጸማችን አይደለም። *«በእምነት ሉማካይነት ሁላችሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ»* (ገላ. 3፥26)።

## ሕፃናት በቤተክርስቲያን ውስጥ

ትናንሽ ሕፃናት እንዲሁም ገና የተወለዱ ጨቅላዎች[1] በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ የተወሰነ እምነት ሊኖራቸው እንደሚችልና በእግዚአብሔር መንግሥትም ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገልጾአል (መዝ. 22፥9–10፤ ሉቃ. 18፥15–16)። ይህ ግን ሁሉንም ልጆች ያጠቃልላል ወይም ጥቂቶችን ብቻ? ይህስ ሊረጋገጥ የሚችለው እንዴት ነው? እነዚህን ጥያቄዎች በተመለከተ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተለያዩ መልሶች ተሰጥተዋል።

ብዙ ክርስቲያኖች ጥምቀት ግርዘትን እንደተካና ሕፃናትንም ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ለመጨመር ዓይነተኛ መንገድ እንደሆነ ያምናሉ። ኃጢአተኛ ባሕርያችን በእምነት ተወግዶ እንዲጣል የውኃ ጥምቀት «የክርስቶስ ግርዘት» እንደሆነና በዚህም የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደሆንን ያስባሉ። ኢየሱስ ሕፃናት ወደ እርሱ ከመምጣት እንዳይከለከሉ አዝዞአል (ማር. 10፥14)። እንዲሁም ያመነና የተጠመቀ ማንም እንደሚድን ተስፋ ሰጥቷል (አጠቅላይ መግለጫ በሚለው ውስጥ የውሃ ጥምቀትን ይመለከቷል)። ከእነዚህ ክርስቲያኖች ጥቂቶቹ ሕፃናት በኢየሱስ ማመን እንድሚችሉ ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ወላጆቻቸው ስለልጃቸው ሊያምኑ ይችላሉ፤ ያላቸውንም እምነት እግዚአብሔር እንደሚቀበል ያስባሉ (1ቆሮ. 7፥14)። ከዚያ በኋላ ደግሞ ለራሱ ማሰብ ሲችል ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን የመቀበል ወይ ያለመቀበል ውሳኔ ይኖረዋል።

ሌሎች ብዙዎች ደግሞ የሚከተለውን ሁለተኛ አስተሳሰብ ያምናሉ፥ እንደእነዚህ ሰዎች አመለካከት እግዚአብሔር ጥቂት ሰዎችን እንጂ ሁሉም ሰው እንዲድን አልመረጠም (ዮሐ. 15፥16፤ 19፤ ሮሜ. 9፥18 ከአጠቃላይ መግለጫ፥ ደህንነት የሰው ምርጫ ወይስ የእግዚአብሔር ምርጫ የሚለውን ይመለከቷል)። እግዚአብሔር አንዳንድ ሕፃናት እንዲድኑ ሲመርጥ ሌሎችን ግን አይመርጥም። እነዚያ እግዚአብሔር የመረጣቸው ከሞቱ መንግሥተ ሰማይ ይገባሉ፤ ያልተመረጡት ግን አይገቡም።

ሌሎች ደግሞ ሦስተኛ አመለካከት አላቸው። እነዚህ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የደህንነትን መንገድ ለሁሉም (ወጣቶችንም ሽማግሌዎችንም ጨምሮ) ቢያቀርብም ሁሉም አይቀበሉትም በማለት ያምናሉ። ብዙዎቹ እግዚአብሔርን ይቃወማሉ። ይህም ሕፃናትንም ይጨምራል በማለት ይናገራሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ገና አእምሮአቸው ባይዳብርም ሕፃናት በመንፈሳቸው ወይም በልባቸው ማመን እንደሚችሉ ያምናሉ (መዝ. 22፥9–10፤ ማቴ. 18፥5–6፤ ሉቃ. 1፥15)። ይሁን እንጂ ሁሉም ሕፃናት ያምናሉ ብለው አያስቡም። እንደ አዋቂዎች ሁሉ አንዳንዶቹ እግዚአብሔርን ይቃወማሉ። ሲሞቱ መንግሥተ ሰማይ የሚገቡት የሚያምኑት ብቻ ናቸው።

---

[1] በሉቃስ 18፥15 ላይ ሕጻናት ተብሎ የተተረጎመው ገና የተወለዱ ጨቅላዎችን ነው።

ሌሎች ደግሞ አራተኛ አመለካከት አላቸው። እንደ እነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ ሁሉም ሕፃናት (ቢያንስ የክርስቲያን ወላጆች ሕፃናት) ወዲያውኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር መንግሥት ናቸው (ማር. 10፥14–15፣ 1ቆሮ. 7፥14)። ስለዚህም ሁሉም ሕፃናት (ቢያንስ የክርስቲያን ወላጆች ሕፃናት) ሲሞቱ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይገባሉ በማለት ያምናሉ። በመጨረሻም ምንም እንኳ ሕፃናት በባሕርያቸው ኃጢአተኞች ቢሆኑም ኃጢአትን ግን አልፈጸሙም የሚል አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች አሉ። ሕፃናት «ንጹሐን» ናቸው ስለዚህም ሁሉም ሕፃናት ሲሞቱ ወዲያውኑ መንግሥተ–ሰማይ ይገባሉ በማለት ያምናሉ።

## ማጠቃለያ

ስለዚህ ጉዳይ ያለን እምነት ምንም ይሁን ምን የወላጅነት ኀላፊነታችን ግን ግልጽ ነው። ጥምቀት ለእያንዳንዱ ሰው አስፈላጊ መሆኑ እውነት ነው። ሕፃናት ይጠመቁም ለጌታ አልፈው ይሰጡም በእግዚአብሔር እጅ ልናኖራቸውና ለደህንነታቸውም በእርሱ ልንታመን ይገባናል። ስለእግዚአብሔርና ስለቃሉ ልናስትምራቸው ይገባል (ዘዳ. 4፥9–10፥ 6፥6–7፣ መዝ. 78፥5–6)። በፍቅር ልንቀጣቸውና ልንገስጻቸውም ይገባል (ኤፌ. 6፥4፣ ቆላ. 3፥21)። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነው (የሐዋ. 2፥39)።

# ክርስቲያናዊ ጋብቻ

## መሪ ጥቅሶች

ዘፍ. 1፥26-28፤ 2፥23-24 - ከውድቀት በፊት ወንድና ሴት የነበሩበት ሁኔታ።

መኃ. ምዕራፍ 1-8 - ዓይነተኛ የፍቅር ጋብቻ።

ማቴ. 5፥31-32፤ 19፥3-9 - ስለጋብቻና ፍቺ ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት።

1ቆሮ. 7፥1-17 - ስለጋብቻና ፍቺ ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት።

ኤፌ. 5፥21-33 - ባልና ሚስት አንዳቸው ለሌላው መገዛት እንደሚገባቸው።

1ጴጥ. 3፥1-7 - ባልና ሚስት እርስበርስ መከባበር አለባቸው።

## እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለው እቅድ

እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮናል፤ ወንድም ሆነ ሴት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል (ዘፍ. 1፥26)። እግዚአብሔር ጋብቻን የደነገገው ለሦስት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ኅብረት ነው። ወንድ ብቻውን መሆኑ መልካም እንዳይደለ እግዚአብሔር አየ፤ ስለዚህም ረዳት የምትሆነውን ፈጠረለት (ዘፍ. 2፥18)። ጋብቻ የተደነገገበት ሁለተኛው ምክንያት ልጆች እንዲወለዱና ቤተሰብ እንዲመሠረት ነው። እንዲበዙና እንዲባዙ እግዚአብሔር ለወንድና ለሴት ነገራቸው (ዘፍ. 1፥28)። ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ለወሲባዊ እርካታ ነው። በዚህም ምክንያት ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ። ወንድና ሴት ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍ. 2፥24-25፤ ምሳ. 5፥15-21፤ መኃ. 1-8)። አዳምና (የመጀመሪያው ወንድ) ሔዋን (የመጀመሪያዋ ሴት) አንድ ላይ ምድርን ሁሉ እንዲገዙ ተፈጥረዋል (ዘፍ. 1፥26-28)።

በኃጢአት ምክንያት ግን አዳምና ሔዋን አስቀድሞ እግዚአብሔር ካቀደው እቅድ ተሰናከሉ። ወዲያውም ኃጢአታቸው በመካከላቸው መተፋፈርንና መለያየትን (ዘፍ. 3፥7)፥ መካሰስን (ዘፍ. 3፥12)፥ በሚስት ላይ የወንድ የበላይነትን አመጣ (ዘፍ. 3፥16)። ከዚህም በተጨማሪ ተፈጥሮ የሚገዛላቸው መሆኑ ቀርቶ ጠላታቸው ሆነ (ዘፍ. 3፥17-19)። ከዚያ በኋላ ሌሎች ክፉ ነገሮችም ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ከእነዚህም መካከል መጋደል (ዘፍ. 4፥8)፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት (ዘፍ. 4፥19) እና በቀል (ዘፍ. 4፥23) ይገኙበታል። መፋታትም ተለመደ። ብዙ ሚስቶችን ስለማግባትና (ዘፀ. 21፥10፤ ዘዳ. 21፥15-17) መፋታትን (ዘዳ. 24፥1-4) አስመልክቶ የሙሴ ሕግ ዝርዝር ነገሮችን ጽፎአል። ብዙ ሚስቶችን ማግባትና መፋታት ግን የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም። የእግዚአብሔር እቅድ ከመጀመሪያውም ሰው በአንድ የትዳር ጓደኛ ጸንቶ እንዲኖር ነበር (ማቴ. 19፥4-9)።

## የክርስቲያን ጋብቻ

በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ካለው መንፈሳዊ ኅብረት (ኤፌ. 5፥32) ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ለክርስቲያኖች ጋብቻ ከፍተኛ ትርጉም አለው። ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በነበረበት ወቅት የመጀመሪያውን ተአምር በማድረግ ጋብቻን ባርኮአል (ዮሐ. 2፥1-11)። የእግዚአብሔር መንግሥት መጀመሩንም አውጆአል። ስለዚህም በባልና በሚስት መካከል አዲስ ሕብረትን መጠበቅ አለብን። ጳውሎስ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባርያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ

በክርስቶስ አንድ ሰው ናችሁና (ገላ. 3÷28) ብሏል። ታዲያ ይህን ማለቱ በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት እኩል ናቸው ማለት ነውን?

ባልና ሚስት በወሲባዊ ግንኙነታቸው እኩል መሆናቸውን ሁሉም ክርስቲያኖች ያምናሉ። እያንዳንዳቸው የጋራ ጋብቻ ኃላፊነታቸውን መፈጸም እንደሚኖርባቸውም ጳውሎስ በግልጽ ጽፎአል (1ቆሮ. 7÷3)። የሚስት አካል የራስዋ ሳይሆን የባልዋ መሆኑን ገልጾአል (1ቆሮ. 7÷4)። ይህ በጳውሎስ ዘመን ለነበሩ ሰዎች አዲስ አልነበረም፤ ከአዳምና ከሔዋን ዘመን አንስቶ እስከ ጳውሎስ ዘመን ድረስ ሰዎች ሚስት የባልዋ ንብረት እንደሆነች ሲያስቡ ኖረዋል። ጳውሎስ ግን ዐረፍተ ነገሩን እዚያ ላይ ብቻ አላቆመም። በዚያው ቁጥር ላይ የባል አካል የራሱ ሳይሆን የሚስቱ መሆኑንም ገልጾአል። ይህ አባባሉ በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ለነበሩ አንባቢዎች በፍጹም አዲስ ትምህርት ነበር። በተጨማሪም ለጳውሎስ ይተጉ ዘንድ ተስማምተው ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስበርስ ከወሲባዊ እርካታ እንዳይከላከሉ ተናግሮአል (1ቆሮ. 5÷7)። አንዳንድ ኃይማኖቶች ሴት ወንድ ዘሩን የሚዘራባት «እርሻ» ናት በማለት ያስተምራሉ። በክርስትና እምነት መሠረት ግን ሙሉ በሙሉ የጎበረቱ ተሳታፊ እንጂ ንብረት ወይም ዕቃ አይደለችም። የክርስቲያን ጋብቻ የተሟላ ጎብረትና አንድነት ነው።

ባልና ሚስት በሌላው የጎብረታቸው ገጽታ በሙሉ እኩል ናቸውን? ለዚህ ጥያቄ ክርስቲያኖች የተለያዩ መልሶች አሉዋቸው። በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ የባልና የሚስት ድርሻን አስመልክቶ ሁለት ዋና የአስተሳሰብ ዘርፎች አሉ። የመጀመሪያውና ብዙ ክርስቲያኖች የሚቀበሉት አስተሳሰብ ሚስት በባልዋ አስተዳደር ሥር ስለሆነች ልትታዘዘው ይገባል የሚለው ነው። ለዚህም አባባላቸው ጳውሎስ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ (1ቆሮ. 11÷3)፤ በማለት የጻፈውን ይጠቅሳሉ። ከዚህም ሌላ ምንም እንኳ በጌታ አንዳቸው ለሌላው አስፈላጊ ቢሆኑም (1ቆሮ. 11÷11-12)፤ ጳውሎስ ሴት ከወንድና ለወንድ መፈጠርዋንም ይናገራል (1ቆሮ. 11÷8-9)። እነዚህ ክርስቲያኖች «ራስ» ሲል ባል የሚስቱ መሪ መሆኑን፤ እንዲሁም ሚስቱን «መመገብ» «መንከባከብ» እንዳለበት ያመለክታል ብለው ያምናሉ። እነዚህ ቃላትም ባል ለሚስቱ ያለበትን ኃላፊነት ያመለክታል ይላሉ (ኤፌ. 5÷25፤ 5÷9)። አባት ለልጆቹ ያለበትንም ኃላፊነት ይጠቅሳሉ (ኤፌ. 6÷4፤ 1ጢሞ. 3÷4-5)። እነዚህ ክርስቲያኖች ክርስቶስ አካሉ ለሆነችው ቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ሁሉ ወንድም የሴት ራስ ነውና ሴቶች ለጌታ እንደሚገዙ ሁሉ በማንኛውም ነገር ለባሎቻቸው መገዛት እንዳለባቸው ጳውሎስ የተናገረውን ይጠቅሳሉ (ኤፌ. 5÷22-24)። ባሎችም ቢሆኑ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳትና ራሱንም አሳልፎ እንደሰጠላት (ኤፌ. 5÷25)፥ እንዲሁም የራሳቸውን አካል እንደሚወዱ አድርገው ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ታዝዘዋል (ኤፌ. 5÷28)። ሐዋርያው ጴጥሮስም ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ አዝዞአል፤ ለዚህም ለአብርሃም የታዘዘችለትን ሣራን ምሳሌ አድርጎ ያቀርባል (1ጴጥ. 3÷1-6) በማለት ሀሳባቸውን ይገልጻሉ።

ይሁን እንጂ እነዚህ ክርስቲያኖች እንደሚሉት በጋብቻ ያለውን መገዛት በአንድ ወገን ብቻ ልንመለከተው አይገባም። በኤፌሶን ያለው ክፍል የሚጀምረው በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ (ኤፌ. 5÷21) በሚል ለሁሉም አማኞች በተሰጠ ትእዛዝ ነው። ምንም እንኳ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ቢሆንም ራሱን ለእግዚአብሔር አብ አስገዝቶአል (ፊል. 2÷6-8)። በተመሳሳይ ሁኔታም መገዛት ሲል በእኩልነት ውስጥ ያለ መገዛት ማለቱ እንደሆነ እነዚህ ክርስቲያኖች ያምናሉ። ወንድና ሴት በተፈጥሮአቸው እኩል ቢሆኑም እያንዳንዳቸው የተለያዩ ድርሻዎች አላቸው፤ ስለዚህም አንዳቸው ለሌላው የሚገዙት በተለያየ መልኩ ነው። ሁላችንም ለክርስቶስ እንደምንገዛው ሁሉ በቤት ውስጥ መሪ በመሆኑ ሚስት ለባልዋ ትገዛለታለች፤ ወንድ ደግሞ ክርስቶስ ራሱን ለቤተክርስቲያን እንደሰጠ ሁሉ ራሱን በመካድና ሁለንተናውን በመስጠት ለሚስቱ ይገዛል።

በክርስቲያናዊ ጋብቻ ውስጥ የባልና የሚስትን ድርሻ አስመልክቶ የቀረበው ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ ሁለቱም ምንም የተለየ ድርሻ የላቸውም የሚል ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች ልጆችና ባሪያዎች እንዲታዘዙ ሊነገርም (ኤፌ. 6÷1፤5) ሚስቶች ግን ለባሎቻቸው እንዲታዘዙ አልተነገራቸውም ይላሉ። ልክ አንዳችን ለሌላው መገዛት እንዳለብን ዓይነት (ኤፌ. 5÷21) ሚስቶችም ለባሎቻቸው እንዲሁ እንዲገዙ ታዝዘዋል። ስለዚህም ባሎችም ቢሆኑ ለሚስቶቻቸው መገዛት ይኖርባቸዋል። ጴጥሮስ ደግሞ በዘመኑ ከነበረው ባሕል ተጻራሪ በሆነ መልኩ ሚስቶች ባሎቻቸውን ሳይሆን ባሎች ሚስቶቻቸውን ማክበር እንዳለባቸው ገልጾአል (1ጴጥ. 3÷7)። ብዙ ክርስቲያን ምሁራን እንደሚስማሙበት ግሪክኛው «ራስ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ገዢ» የሚል ትርጉም የለውም፤ ከዚያ ይልቅ በአዲስ ኪዳን ውስጥ «የሕይወት ምንጭ መገኛ» ወይም «መነሻ» የሚል ትርጉም ነው ያለው (ኤፌ. 1÷22፤ 4÷15፤ ቆላ. 1÷18፤ 2÷10፤19)። ስለዚህም እንደእነዚህ ክርስቲያኖች አመለካከት በ1ቆሮ. 11÷3 ክርስቶስ የእያንዳንዱ ሰው «ሕይወት ምንጭ» መሆኑን ከክርስቶስ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ሁሉ ሴትም ከወንድ መምጣትዋን የሚያመለክት ነው። ይህ አተረጓጎም ከ1ቆሮ. 11÷8፤ 11-12 ጋር በሚገባ ይስማማል። እነዚህ ክርስቲያኖች፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ያቀደው፤ ባልና ሚስት እኩል እንዲሆኑ ነበር ምንም እንኳ በኤደን ገነት በነበሩበት ወቅት በኃጢአት ምክንያት ሴቲቱ ብትረገምም (ዘፍ. 3÷1-6፤16) ያ መርገም በክርስቶስ ተሽሮአል፤ ስለዚህም

ክርስቲያናዊ ጋብቻ ይህን እውነት ማንጸባረቅ አለበት። በጋብቻ አማካይነት ወንድና ሴት አንድ አካል የሚሆኑ ከሆነ (ዘፍ. 2፥24) አንደኛው «ገዢ» ሁለተኛው ደግሞ «ተገዢ» ሊሆን አይችልም የሚል አስተሳሰብ አላቸው።

የትኛውንም ዓይነት አመለካከት ብንቀበል መጽሐፍ ቅዱስ ግን ባልና ሚስት አንዳቸው ለሌላው መሰጠት እንደሚኖርባቸው ግልጽ አድርጎታል። ኢየሱስ ራሱም ቢሆን ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል (ማር. 10፥7) የሚለውን የብሉይ ኪዳን ቃል የጠቀሰው በመደገፍ ነበር። እንዲህም ስለተባለ ሰው በልቡ እናትና አባቱን «ይተዋል» ማለቱ እንጂ የግዴታ ከወላጆቹ መነጠል አለበት ማለት አይደለም። ወንድ ከወላጆቹ እንዲያውም ከልጆቹ በላይ ራሱን ለሚስቱ መስጠት አለበት፤ በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ሁለት አካል ሳይሆኑ አንድ አካል ናቸው (10፥8)። በአንዳንድ ባሕሎች የትዳር ጓደኛ «የአካል ክፋይ» እንደሆነ ይታሰባል።

ከማንኛውም ሰው በላይ እግዚአብሔር በሕይወታችን ከፍተኛውን ስፍራ መያዝ አለበት። ባልና ሚስት ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር በቀረቡ መጠን በዚያው ልክ እርስ በርስ ይቀራረባሉ። በመክብብ 4፥9–12 አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል፤ በሦስት የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም ይላል። በሦስተኛነት ደረጃ እግዚአብሔር የተጨመረበት የባልና የሚስት ውህደት ጠንካራ ጥምረት ነው።

## መፋታትና እንደገና መጋባት

ክርስቲያናዊ ጋብቻን ስንፈጽም የምናደርገው ቃል ኪዳን በምዕመናን ፊት ብቻ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔርም ፊት ጭምር ነው። ጋብቻ የዕድሜ ልክ ትስስር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መፋታትን እንደሚጠላ ይናገራል (ሚል. 2፥14–16)። በብሉይ ኪዳን ዘመን መፋታት በጣም የተለመደ ነበር፤ ስለዚህም እግዚአብሔር በሚረባ በማይረባው እንዳይፋቱ አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት። የተፈታችው ሴት ሕጋዊ ጥንቃቄ እንዲደረግላትም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። የሙሴ ሕግ ባል ሚስቱን ሊፈታ የሚችልበት በቂ ምክንያት እንዳለው ይገልጻል፤ ይህም ምክንያት የሚስቱ መርከስ ነው። ይሁን እንጂ ሲፈታት የጽሑፍ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት (ዘዳ. 21፥1–4)። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አንዳንድ ፈሪሳውያን ወንድ በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን መፍታት ይችላል በማለት ያስተምሩ ነበር (ማቴ. 19፥3)። ኢየሱስ የመለሰላቸው ግን እግዚአብሔር ያበጀውን ጋብቻ ማፍረስ ስህተት እንደሆነ ነበር። «እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» አለ (ማቴ. 19፥6)። ኢየሱስ መፋታት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነና ሙሴ መፋታትን የፈቀደበት ምክንያት ግን ከአይሁዳውያን ልብ ጥንካሬ የተነሣ እንደሆነ ተናግሮአል (ማቴ 19፥8)። ጋብቻን ማፍረስ ትክክል እንዳልሆነ የሁሉም ክርስቲያኖች እምነት ነው።

ከዚህም ቢተጨማሪ ኢየሱስ «እኔ ግን፥ አንድ ሰው በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት ቢያገባ አመንዝራ ነው እላችኋለሁ» (ማቴ. 19፥9) አለ። በሌላ ስፍራ ደግሞ «በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ምክንያት ይሆንባታል። የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል» አለ (ማቴ. 5፥32)። በእነዚህ ሁለት አባባሎቹ ኢየሱስ ምን ማለቱ ነው? ለዚህ አባባሉ ክርስቲያኖች ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች አሉዋቸው።

በመጀመሪያ፥ መፋታት አልተፈቀደም፤ የትዳር ጓደኛ በሕይወት እያለ እንደገና ማግባትም ከልክል ነው ብለው ብዙ ክርስቲያኖች ያምናሉ (ሮሜ 7፥2–3)። በማር. 10፥11–12 ላይ ኢየሱስ የተናገረው ቃል በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር የሚለውን እንደማይጨምር ይናገራሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ዓይን የሚታዩት ከመጀመሪያ የትዳር ጓደኛቸው ጋር እንደተጋቡ ሆነው ስለሆነ፥ ዳግም ጋብቻ የሚፈጽሙ እንደገና ዝሙትን ይፈፅማሉ ብለው ያምናሉ። ሚስትን መፍታት እንድታመነዝር ወይም ደግሞ ሌላ እንድታገባ ያደርጋታል፤ ይህም ማመንዘር ነው በማለት ያምናሉ (ማቴ. 5፥32)። ባልዋ በሕይወት እያለ ሌላ ወንድ የምታገባ ሴት አመንዝራ ናት፤ በማለት ጳውሎስ በሮሜ 7፥3 የተናገረውንም ይጠቅሳሉ። ከዚህም በተጨማሪ ጳውሎስ ከትዳር ጓደኛቸው የተፋቱ ሰዎች ሳያገቡ መኖር ወይም እርቅ ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራል (1ቆሮ. 7፥11)። ስለዚህም በዚህ አተረጓጎም መሠረት የተፋታ ሰው የመጀመሪያው የትዳር ጓደኛው በሕይወት እስካለች ድረስ እንዲያገባ አልተፈቀደለትም ማለት ነው።

አንዳንዶች የሚከተሉት ደግሞ ሁለተኛውን አመለካከት ነው፥ እንደዚህኛው አመለካከት ከአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሣ መፋታት ይፈቀዳል፤ ይኸውም ትዳሩ ከፈረሰ ማለት ነው። ለምሳሌ ያህል ከሁለት አንዱ ዝሙት ቢፈጽም ዝሙቱ እንዲፈጸም ያደረገው ፍቺው አይደለም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ደግሞ ሚስት ወይም ባል ትቶ ከሄደ ‹ያለምንም ይፋ ፍቺ› ወይም ደግሞ በሌሎች ያልተለመዱ ሁኔታዎች ማለትም አንዱ በሌላው ላይ በሚያደርሰው ጭካኔ መፋታት ይቻላል፤ ምክንያቱም ድርጊቱ ከአመንዝራነት ያላነሰ ነውና። እንደነዚህ ክርስቲያኖች አመለካከት የሚያምን ወይም የማታምን የትዳር ጓደኛ የሚያምነውን ወይም የምታምነውን የትዳር ጓደኛ ትቶ ወይም ትታ ለመሄድ ከፈለገች የሚያምነው ወይም የምታምነው የትዳር ጓደኛ ፍቺውን ይቀበል የሚለውን የጳውሎስን ምክር ሊቀበል ይገባል ይላሉ (1ቆሮ. 7፥15)።

እንደገና ማግባትን አስመልክቶም ትዳሩን ያፈረሰ ባል ወይም ትዳሯን ያፈረሰች ሴት የመጀመሪያው የትዳር ጓደኛ በሕይወት እስካለች ድረስ እንደገና ማግባት አይፈቀድለትም (1ቆሮ. 7፥11)። ሌሎች ደግሞ ለትዳሩ መፍረስ ምክንያት ያልሆነው ወገን አንደገና ለማግባት ነፃ ነው ይላሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ክርስቲያን የሆነው ወገን ባልም ሆነ ሚስት በምንም ዐይነት ግዴታ አይያዝም (1ቆሮ. 7፥15) የሚለው የጳውሎስን አባባል ይጠቅሳሉ።

ሌሎች ደግሞ ሦስተኛ አመለካከት አላቸው፥ እንደእነዚህ ሰዎች አመለካከት ምን ጊዜም ቢሆን ትዳርን ማፍረስ ትክክል አይደለም። ይሁን እንጂ፥ የመጀመሪያው ጋብቻ ፍቺ ምክንያት ምንም ይሁን ምን እንደገና ማግባት ይፈቀድለታል። ኢየሱስ እንደተናገረው በሙሴ ሕግ መሠረት ጋብቻው ሕጋዊ ቢሆንም፥ ሌላይቱን ለማግባት በማለት ብቻ ያለበቂ ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሰው አመንዝሮአል (ማቴ. 19፥9)። ከዚሁም ጋር አያይዘው እነዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ . . . አመንዝራ ያደርጋታል ቢልም፤ በመፈታትዋ ብቻ አመንዝራ ሆናለች ማለቱ አይደለም፤ የሚል መከራከሪያ ሃሳብ ያቀርባሉ። ኢየሱስ የተፈታችው ሴት (ምንም እንኳ ባታመነዝርም) ውላ አድራ ሌላውን ታገባለች ወይም ደግሞ ታመነዝራለች ማለቱ ሊሆን እንደማይችል ይናገራሉ። አንዳንድ ሴቶች እንደገና ላያገቡ ወይም ላያመነዝሩ ይችላሉ። እንደእነዚህ ሰዎች አመለካከት ምንም እንኳ ዝሙት ባትፈጽምም ሚስቱን የሚፈታ ሰው «አመንዝራ ሆና እንድትታይ» ያደረጋታል ማለቱ ነው። ምክንያቱም የተፈታችው ለትዳርዋ ታማኝ ስለመሆንዋ እንደሆነ ያስባሉና። እንደገና ካገባችም አዲሱ ባልዋም አመንዝራ ይመስላል ይላሉ። ይህ አባባል በሮሜ 7፥3 ላይ ባልዋ በሕይወት እያለ ሌላውን የምታገባ ሴት አመንዝራ ትባላለች ከሚለው ከጳውሎስ አባባል ጋር ይስማማል፤ እንዲህም ሲል ግን በእርግጥ አመንዝራ ናት ማለቱ አልነበረም።

ይህን ሦስተኛውን አመለካከት የሚከተሉ ክርስቲያኖች፤ አማኞች በምንም ዓይነት ሁኔታ መፋታት የለባቸውም፤ የማያምነው ወገን ለመፋታት ከፈለገ ግን መቀበል አለባቸው ይላሉ (1ቆሮ. 7፥10–16)። በ1ቆሮ. 7፥8–9 ላይ «ያላገባ» የሚለው ቃል በ1ቆሮ. 7፥25 «ድንግል» ከሚለው ጋር የተለየ እንደመሆኑ መጠን ከ8–9 ባሉት ቁጥሮች ላይ የሚናገረው «አስቅድመው አግብተው» ለነበሩ ወይም የትዳር ጓደኛቸው በሞት ስለተለያቸው ወገኖች ነው። እንግዲህ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ ሥጋቸውን መቆጣጠር ካልቻሉ እንዲያገቡ ፈቅዶላቸዋል ማለት ነው። ስለዚህም ይህን አተረጓጎም በመከተል እነዚህ ክርስቲያኖች የፍቾውን ምክንያት አይመረምሩም። ያለፈውን ጋብቻቸውን በማፍረሳቸው በትክክል ንስሐ ከገቡ ማንም ቢሆን እንደገና እንዲያገባ ተፈቅዶለታል ይላሉ።

የፍቺና ዳግም የማግባት ጉዳይ በጣም ውስብስብ ነው። ስለዚህም ጉዳዩን አስመልክተን አንድ ውሳኔ ላይ ከመድረሳችን በፊት የተሰጡትን ጥቅሶች በጸሎት መንፈስ ሆነን በጥንቃቄ ልንመረምራቸው ይገባል። ስለሆነም ማንም ቢሆን ለመፋታትም ሆነ እንደገና ለማግባት እቅድ ከማውጣቱ በፊት የቤተክርስቲያኑን መጋቢ ወይም ሽማግሌዎች ማማከሩ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት የተለያዩ መመሪያዎች ሊኖራቸው ይችላል።

## ድርብ ጋብቻ

በብሉይ ኪዳን የምንመለከታቸው የተለያዩ ሰዎች ከአንድ በላይ ሚስቶች ነበሯቸው፤ ይህ ግን አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት የፈጸሙት ኃጢአት ውጤት ሊሆን ይችላል። በጋብቻ ሁለቱ «አንድ አካል» ይሆናሉ፤ ሌላ ሦስትኛ ሰው መጨመሩ ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አይጣጣምም። አስቀድሞ የተፈቀደው ምንም ይሁን ምን ክርስቲያኖች በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ማግባት እንደሌለባቸው አዲስ ኪዳን ግልጽ አድርጎታል (1ቆሮ. 7፥2)። ሁሉ ክርስቲያኖች በዚህ ይስማማሉ። ይሁን እንጂ አንድ ሰው በጌታ ከማመኑ በፊት ከአንድ በላይ ሚስቶች ከነበሩት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግላቸው ይገባል እንጂ ሊተዋቸው አይገባም (ዘፀ. 21፥10)። በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ግን የቤተክርስቲያን መሪ ለመሆን እንዲመረጥ ጳውሎስ አልፈቀደም (1ጢሞ. 3፥2፤ 12፤ ቲቶ 1፥6)።

ካገባ ወይም ካላገባ እንዲሁም ከሴትኛአዳሪ ጋር ቢሆንም ክርስቲያኖች ከትዳር ጓደኛቸው በቀር ምንም ዓይነት ወሲባዊ ግንኙነት እንዳያደርጉ በጥብቅ ተከልክሎአል (1ቆሮ. 6፥15)። ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የከበረ ይሁን፤ ባልና ሚስት ታማኝነትን በማጉደል ጋብቻን አያርክሱ ምክንያቱም ሴሰኞችንና አመንዝሮችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል (ዕብ. 13፥4)።

# ፈውስና አርነት

## መሪ ጥቅሶች

ማቴ. 8፥16–17 – ፈውስና ነፃ መውጣት በኢየሱስ አገልግሎት።

ማቴ. 12፥43–45 – ስለክፉ መናፍስት ያስተምራል።

ማር. 5፥1–17 – ኢየሱስ አጋንንት የነበሩበትን ሰው ነፃ አወጣ።

ማር. 9፥14–29 – ኢየሱስ የሚጥል በሽታ ከነበረበት ልጅ አጋንንት አወጣ።

ማር. 16፥16–18 – ፈውስና ነፃ ማውጣት የአማኞች ምልክት ናቸው።

1ቆሮ. 12፥9–10 – የፈውስ ተዓምራትን የማድረግና መናፍስትን የመለየት ስጦታዎች

ያዕ. 5፥14–16 – የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ዘይት እየቀቡ ለሕመምተኛው የሚያደርጉት ፀሎት።

## የበሽታዎች መለኮታዊ ፈውስ

ከሕመም መፈወስን አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ተስፋዎች አሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ አይሁዳውያን የፈውስና (ዘፀ. 15፥26) ከበሽታ የመጠበቅ ተስፋ ተሰጥቶአቸው ነበር (መዝ. 103፥1–5)። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን የበሽታ ምክንያት እንደሆነ ይናገራል (ሉቃ. 13፥16፤ የሐዋ. 10፥38)። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ከተቀባበት ምክንያቶች አንዱ ሕመማንን ለመፈወስ እንደሆነ ተናግሮአል (ሉቃ. 4፥17–18፤5፥17)። ኢየሱስ የታመሙትን ሁሉ እንደፈወሰ (ማቴ. 8፥16)፥ ደዌና ሕማምን ሁሉ እንደፈወሰ (ማቴ. 4፥23) መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህም የመፈወስ ኃይል ለኢየሱስ ደቀመዛሙርትም ተሰጥቶአቸው ነበር (ማቴ. 10፥1፤8፤ ማር. 6፥7፤13፤ ሉቃ. 10፥9)። መፈወስ የአማኞች አንዱ ምልክት መሆኑንም ኢየሱስ ተናግሮአል (ማር. 16፥18)። በአብዛኛው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ስለፈውስ እንመለከታለን። ያዕቆብም ቤተክርስቲያን ለሕሙማን እንድትጸልይና የታመሙትም እንዲፈወሱ ተናግሮአል (ያዕ. 5፥14–16)። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል የፈውስና ተአምራት የማድረግ ስጦታዎችም ይገኙበታል (1ቆሮ. 12፥9–10፤28)። በጥንት ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ዘመንም ሆነ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ብዙ ፈውሶች ተደርገዋል።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ልክ ቀድሞ እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ይፈውሳል ብለው ያምናሉ። ለዚህም አባባላቸው «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው» የሚለውን ከዕብ. 13፥8 ይጠቅሳሉ። ምንጊዜም ቢሆን ኢየሱስ ለመፈወስ ፈቃደኛ መሆኑን ለማሳየትም ማር. 1፥40–41 ያለውን ያቀርባሉ። በዓለም ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ክርስቲያኖች በመለኮት ኃይል መፈወሳቸውን ይመሰክራሉ፤ ብዙዎችም ሕመማን ሲፈወሱ መመልከታቸውን ይናገራሉ። አዳኛችን በመስቀል ላይ ኃጢአታችንን መሸከም ብቻ ሳይሆን ሕመማችንን ጭምር እንደተሸከመ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ይጠቅሳሉ (ዘኁ. 21፥8–9፤ ኢሳ. 53፥4–5)። በትንቢተ ኢሳ. 53 ያለው ክፍል በዕብራይስጡ «ድካማችንን ወሰደ፤ ደዌያችንን ተሸከመ» ነው የሚለው፤ በማቴ. 8፥17 የተጠቀሰውም በዚህ መልኩ ነው። እንግዲህ በመስቀል ላይ ኢየሱስ ኃጢአታችንና ደዌያችንን ከወሰደ ዛሬም ቢሆን ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚል ሁሉ ደዌያችንንም እንደሚፈውስ ማመን አለብን ማለት ነው። እንደ እነዚህ ክርስቲያኖች እምነት ጳውሎስ የሥጋዬ መውጊያ የሚለው ሕመምን ሳይሆን ያሰቃየው የነበረውን የሰይጣን መልእክተኛ ነው (2ቆሮ. 12፥7)። ብዙ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዛሬም ቢሆን እንደሚሠሩና ፈውስና ተአምራትን የማድረግ ስጦታዎችም እንደሚገኙበት ያምናሉ (1ቆሮ. 12፥9–10)። ከእነዚህ ክርስቲያኖች ጥቂቶቹ እግዚአብሔር ማንኛውንም ዓይነት ሕመማችንን እንደሚፈውስ ያምናሉ። ሌሎች

ደግሞ አብዛኞቹ ሕመሞች ሊፈውሱ ቢችሉም ሁሉም ዓይነት ሕመም ይፈወሳል ብለን ማሰብ ግን የለብንም ይላሉ።

ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ እግዚአብሔር በሐኪሞችና በመድኃኒቶች አማካይነት እንጂ በዘመናችን በልዕለ-ትፈጥሮአዊ ሁኔታ ሰዎችን እንደሚፈውስ አያምኑም። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖች አንድም ሰው በመለኮታዊ መንገድ ሲፈውስ አልተመለከቱም። ስለዚህም መለኮታዊ ፈውስ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ምዕተ-ዓመታት ለነበሩ ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ እንደሆነ ያስባሉ። ስለታመመውና ጳውሎስ ትቶት ስለመጣው ጓደኛውም ይጠቅሳሉ (2ጢሞ. 4፥20)። ጳውሎስ የሥጋዬ መውጊያ (2ቆሮ. 12፥7) ያለውም አካላዊ ሕመም እንዲያውም የዓይን ሕመም (ገላ. 4፥15) እንደነበረ ያመለክታሉ። በማቴ. 8፥16-17 ያለውን ክልፍ ሲተረጉሙትም፤ ኢየሱስ ሕሙማንን እየፈወሰ ደዌያችንን የወሰደው በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ ነው፤ በመስቀል ላይ የሞተው ግን ለኃጢአታችን ብቻ ነበር ይላሉ።

ሦስተኛው አመለካከት ደግሞ፥ እውነቱ ያለው በእነዚህ ሁለት አመለካከቶች መካከል መሆኑን ይቀበላል። ይህን አመለካከት የሚቀበሉ ሰዎች እነዚህ ሁለት አመለካከቶች በከፊልም ቢሆን የየራሳቸው እውነት እንዳላቸው ያምናሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከአጠቃላይ መግለጫው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ይመለከታል።

## ለፈውስ መጸለይ

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ተፈውሰዋል። አንድን ነገር እንድንቀበል ከተፈለገ መጠየቅ እንዳለብን ኢየሱስ ተናግሯል (ማቴ. 7፥7፤ ያዕ. 4፡2)። የተለያዩ ሰዎችንም እምነታቸው እንደፈወሳቸው ተናግሯል (ማቴ. 8፡10-13፤ ማር. 10፥52)። ሐዋርያቱም እንዲሁ በእምነት ፈውሰዋል (የሐዋ. 3፡16)። ሌሎች ደግሞ «በመታዘዛቸው» ተፈውሰዋል (2ነገ. 5፡1-14፤ ሉቃ. 17፥14፤ ዮሐ. 9፥7)። በኢየሱስ ወይም ከሐዋርያቱ በአንዱ «ትእዛዝ» ብዙ ሽባዎች ተፈውሰዋል (ማር. 2፥10-11፤ ዮሐ. 5፥8፤ የሐዋ. 3፥6፤ 14፥10)። ኢየሱስ የሰጣቸውን ተስፋ በፈውስ አገልግሎታቸው እንዲለማመዱ ለደቀመዛሙርቱ ነግሯቸዋል (ማር. 11፡22-24፤ ዮሐ. 14፥13-14)። «ዘይት በመቀባት» ጸሎትም ብዙ ሕሙማን ተፈውሰዋል (ማር 6፥13)። ያዕቆብም ሕመምተኛው እንዲፈወስ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ዘይት ቀብተው እንዲጸለዩለት መክሯል (ያዕ. 5፡14-16)። ብዙዎች ደግሞ እጅ ተጭኖ ሲጸለይላቸው ተፈውሰዋል (ማር. 6፥5-6፤ ሉቃ. 4፥40፤ የሐዋ. 28፡8)፤ የሚያምኑት እጆቻቸውን በድውዮች ላይ እንደሚጭኑና እነርሱም እንደሚፈወሱ ኢየሱስ ተናግሮአል (ማር. 16፥16፤ ዕብ. 6፥1-2)። የኢየሱስን ልብስ በመንካት (ሉቃ. 6፥19 8፥43-46)፥ የጴጥሮስ ጥላ ስላረፈባቸው (የሐዋ. 5፡15)፥ እንዲሁም የጳውሎስን ጨርቅ ወይም ልብስ በመንካታቸው (የሐዋ. 19፥12) ባልተለመደ ሁኔታ ብዙዎች ተፈውሰዋል። አንድ ጊዜም ኢየሱስ ለበሽተኛ ሰው ደጋግሞ መጸለይ ያስፈለገበት ጊዜ ነበረ (ማር. 8፥22-25)።

ይሁን እንጂ ማንም ሰው ቢሆን ዘመናዊ መድኃኒቶችን ወይም ሳይንሳዊ የሕክምና ዘዴዎችን መቃወም የለበትም። እግዚአብሔር በቀጥታ መፈወስ ይችላል፤ ብዙውን ጊዜ ደግሞ የተለያዩ «መንገዶች» በመጠቀም ይፈውሳል። በመንካት፣ በዘይት፣ እንዲሁም በጭቃ እንኳ ተጠቅሞ ፈውሶአል (ዮሐ. 9፥6-7)። በተመሳሳይ ሁኔታም መድኃኒቶችን እንደመፈወሻ መንገዶች ልንመለከታቸው ይገባል። «ስለሆድህና ስለዘወትር ደዌህ» ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ (1ጢሞ. 5፥23) በማለት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው እንመለከታለን። በተለያዩ ሐዋርያዊ ጉዞዎቹ አብሮት የነበረውን ሉቃስን፥ የተወደደ ባለመድኃኒቱ ሉቃስ (ቆላ. 4፥14) በማለት ጠርቶታል። ስለዚህም በቀጥታ ከእግዚአብሔር ብቻ ወይም ደግሞ ከሐኪሞችና ከመድኃኒቶች ብቻ ሳይሆን ከሁለቱም ማለትም በቀጥታ ከእግዚአብሔርና ከመድኃኒቶች ፈውስ ማግኘት እንደሚቻል መቀበል አለብን (2ነገ. 20፥5-7)። ከዚያ በኋላ ደግሞ እኛን ለመፈወስ ስለተጠቀመባቸው መንገዶች ሁሉ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

አንዳንድ ሕመምተኞች ለምን እንደማይፈወሱ የተለያዩ ምክንያቶች ተሰጥተዋል። ለጸሎታችን መልስ አለማግኘት ዋናው ምክንያት አለማመን ነው፤ ይህም የራሳችን አለማመን (ማር. 9፥23-24)፥ ለፈውስ የሚጸልዩልን ሰዎች አለማመን (ማቴ. 17፥19-20) ወይም በዙሪያችን ያሉ ሌሎች ሰዎች አለማመን ሊሆን ይችላል (ማር. 6፥5-6)። ምናልባትም ሌሎችን ይቅር አለማለትን (ማር. 11፥24-25)፥ አለመታዘዛችን (2ነገ. 5፥1፤ 8፥4) ወይም ከትዳር ጓደኛችን ጋር ያለን ያልተስተካከለ ግንኙነትን (1ጴጥ. 3፥7) የመሳሰሉና ንስሐ ያልገባንባቸው ኃጢአቶች (ዮሐ. 5፥14፤ ያዕ. 5፥17) ሊኖሩ ይችላሉ። ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ወይም ኃጢአታችንን ሳንናዘዝ የጌታን እራት መካፈልም ሕመምን ሊያመጣ ይችላል (1ቆሮ. 11፥27-30)። አንዳንድ ሰዎች ካለማወቃቸው የተነሣም ይሁን ወይም እግዚአብሔር ሊፈውሳቸው እንደሚችል ባለማመናቸው ፈውስን አይጠይቁም (ያዕ. 4፥2)። ለአካላችን ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆኑትን ሌሎች የመፈወሻ መንገዶች ባለመቀበል ለሚደርስብን ሕመም እግዚአብሔርን እየተፈታተንነው ነው ማለት ነው፤ ይህንን ደግሞ እግዚአብሔር ከልክሏል (ማቴ. 4፥6-7)።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የማንፈወሰው ትክክለኛው ጊዜ ስላልሆነ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ አልዓዛርን ለመፈወስ ወዲያውኑ አልሄደም፤ በኋላ ግን ከሞት አስነስቶታል (ዮሐ. 11፥6፤ 43–44)። ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ የበለጠውን ተአምር አደረገ። ኃይሉን ለማሳየት እግዚአብሔር አንድን ሰው ሳይፈውሰው ዓመታት ሊያልፉ ይችላሉ፤ በኋላ ግን እርሱ በመረጠው ሰው ወይም በመረጠው ሁኔታ ሊፈውሰው ይችላል (ማር. 9፥29፤ ዮሐ. 5፥5–9፤9፥3)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰውየው የተወሰኑ ዓመታት ብቻ በሕይወት እንዲኖር ስለፈቀደ ሊሆን ይችላል። ከብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ አሥራ አምስት ዓመታትን ብቻ ሲጨምርለት እንመለከታለን፤ ከዚያ በላይ እንዲኖር ግን አልፈቀደለትም (2ነገ. 20፥5–7)። አንዳንድ ጊዜ ስለህመሙ ምንነት ያለን ግንዛቤ የተሳሳተ ሊሆን ይችላል፤ አካላዊ ሕመም ብቻ መስሎ የሚታየን ሕመም ምናልባት ከክፉ መናፍስት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

## ከአጋንንት ነፃ መውጣት

አካላዊ ሕመምን አስመልክቶ ብዙ ተስፋዎች እንደተሰጡን ሁሉ ከርኩሳን መናፍስት ወይም ከአጋንንት ነፃ እንደምንውጣም መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ተስፋዎችን ሰጥቶናል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ከተቀባበት ምክንያት አንዱ የታሰሩትን ለመፍታት (ሉቃ. 4፥18) እንደሆነ ተናግሮአል። በሄደበት ስፍራ ሁሉ በአጋንንት ከተጠቁት ሁሉ አጋንንትን አውጥቶአል (ማቴ. 4፥24፤ ማር. 1፥34፤ 3፥11)። ይህንንም አጋንንት የማውጣት ሥልጣኑን ለመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ሐዋርያት በኋላም ለሌሎቹ ሰባ ሁለት ሰዎች ሰጥቶአቸዋል (ሉቃ. 9፥1፤ 10፥1፤ 17–19)። አጋንንትን ማውጣት ካመኑት ሰዎች ሥራ አንዱ መሆኑን ኢየሱስ አመልክቶአል (ማር. 16፥17)፤ ይህንንም ከሐዋርያት ሥራ በስፋት እንመለከታለን (የሐዋ. 5፥16፤ 8፥7፤16፥18፤ 19፥11–12)። መናፍስትን መለየትም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው (1ቆሮ. 12፥10)።

አጋንንት ሰዎችን ለማጥቃት ወደዚህ ምድር የሚመጡ የሙታን መናፍስት አይደሉም። የሞቱ ሰዎች መናፍስት ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ወደመንግሥተ ሰማይ (ፊል. 1፥23) ወይም ደግሞ የመጨረሻውን ፍርድ ቀን ለመጠበቅ ወደገሃነም እንደሚሄዱ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (ዕብ. 9፥27፤ ራዕይ 20፥5፤ 13)። አጋንንት የሰይጣን አገልጋዮች የሆኑ (ማቴ. 12፥26–27፤ ማር. 3፥22–26) እርኩሳን መናፍስት ናቸው (ማቴ. 10፥1፤ 12፥43)። ሰይጣንና መናፍስቱ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ነበር በኋላ ግን በእግዚአብሔር ላይ አመጹ (ኢሳ. 14፥12–15፤ ሕዝ. 28፥13–17)። አጋንንት በጣም ብዛት ያላቸውና በየትኛውም አገር የሚገኙ ናቸው (ማር. 5፥9፤ ኤፌ. 6፥12)። ወደ ሰዎችና ወደ እንስሳት በመግባት መቆጣጠር ይችላሉ፤ እንዲያውም ከአካል ውጪ መሆንን አይፈልጉም (ማቴ. 12፥43–45፤ ማር. 5፥2፤12–13)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለይተው አውቀውታል (ማር. 1፥23–24፤ 34፤ የሐዋ. 19፥15) ከዚህም የተነሣ በክርስቶስ ማንነት «ያምናሉ» ማለት ይችላል (ያዕ. 2፥19)። ይሁን እንጂ የመጨረሻ ዕጣቸው በጥልቁ ውስጥ «መሠቃየት» መሆኑንም ያውቃሉ (ማቴ. 8፥29፤ ሉቃ. 8፥31)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጣዖት የተሠዋ በቀጥታ ለአጋንንት የተሠዋ መሆኑን ተናግሮአል (1ቆሮ. 10፥19–21)።

አንዳንድ ጊዜ አጋንንት በቀጥታ አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ «ሊያድሩበት» ወይም አእምሮውና አካሉ በርኩሳን መናፍስት ሊያዝ ይችላል (ማር. 5፥15–16)። ብዙውን ጊዜ ግን የሰውየው አእምሮና አካል በክፉ መንፈስ «ሊጠቃ» ወይም «ሊጨቆን» ይችላል እንጂ ሙሉ በሙሉ አይቆጣጠሩትም ወይም አይገዙትም (ማቴ. 9፥32፤ 12፥22፤ ማር. 9፥17–29፤ ሉቃ. 6፥18)።

አማኞች የእግዚአብሔር ስለሆኑና የሚገዛቸውም እርሱ ራሱ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ክፉ መናፍስት ሊያድሩባቸው እንደማይችሉ የሁሉም ክርስቲያኖች እምነት ነው (1ቆሮ. 6፥19–20)። ይሁን እንጂ አማኞች በውስጣቸው በአጋንንት «ሊጨቆኑ» ወይም «ሊጠቁ» እንደሚችሉ የሚያምኑ ብዙ ክርስቲያኖች ናቸው። ለዚህም አባባላቸው የጳውሎስን አካል ያሰቃየው የነበረውን *የሰይጣን መልእክተኛ* (2ቆሮ. 12፥7) እና ለጣዖት የተሰዋውን በመብላት *ክአጋንንት ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ አልፈልግም* (1ቆሮ. 10፥20–22) በማለት ለአማኞች የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ያቀርባሉ። በአጋንንት ምክንያት የታመሙትንና ወደ ኢየሱስ በመምጣት ነፃ የሆኑትን የብዙ ሰዎችን ምሳሌም ያቀርባሉ (ማር. 3፥10–11፤ ሉቃ. 6፥18–19)። እነዚህ ሰዎች ሙሉ በሙሉ በአጋንንት ቁጥጥር ሥር ያሉ ሳይሆኑ በውስጣቸው በክፉ መናፍስት «የተጨቆኑ» ወይም«የተጠቁ» መሆናቸውን ያምናሉ። ክፉ መናፍስት ክርስቲያኖች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፤ እንዲያውም አንዳንዶቹ የአጋንንትን ሐሰተኛ ትምህርት እስከመቀበል እንኳ ይደርሳሉ (1ጢሞ. 4፥1–3)። ጳውሎስም ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከክፉ መናፍስት ጋር እንደሆነ ተናግሮአል (ኤፌ. 6፥12)። *መንፈሶች የእግዚአብሔር መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መርምሩም ተብለናል* (1ዮሐ. 4፥1–3)።

ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ አማኞች በውስጣቸው ምንም ዓይነት ክፉ መናፍስት ሊኖሩባቸው እንደማይችሉ ያምናሉ። በአንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስና ክፉ መናፍስት በአማኙ ውስጥ መኖር እንደማይችሉ ይናገራሉ (1ቆሮ. 6፥9)። ከእነዚህ ክርስቲያኖች አንዳዶቹም እውነተኛ ክርስቲያን በምንም ዓይነት በክፉ መናፍስት መጠቃት እንደማይችል ያምናሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ክፉ መናፍስት ከውጭ ሆነው ክርስቲያኖችን ሊያጠቁዋቸው ወይም ሊጫኑዋቸው ይችላሉ፤ ሆኖም ወደ አካላቸው ውስጥ መግባት አይችሉም ይላሉ።

ይህ ጉዳይ ለሌሎች የምናደርገውን የጸሎት አገልግሎት የሚወስን በመሆኑ ጠቃሚ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ ነው። አንድ አማኝ አጋንንት ሊኖሩበት ከቻሉ ከአንዳንድ ሕመሞችና ስሜታዊ ችግሮች ነፃ እንዲሆን ወይም ደግሞ በአንዳንድ ኃጢአቶቹ ላይ ድል እንዲያገኝ አጋንንቱ መውጣት አለባቸው። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ኃጢአቶቻችን የራሳችን ኃጢአተኛ ባሕርይ ውጤት እንጂ የአጋንንት ወይም የሰይጣን ውጤቶች አለመሆናቸውንም መገንዘብ አለብን (ገላ. 5፥19–21)።

## ነፃ ለማውጣት መጸለይ

ክርስቲያኖች አጋንንት ሊኖሩባቸው ቢችሉም ባይችሉም ቢያንስ ክርስቲያን ያልሆኑ ወይም የማያምኑ ሰዎችን እንዴት ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ነፃ ማውጣት እንደሚቻል ማወቅ ይኖርብናል። ክርስቲያኖች በሙሉ በኤፌ. 6፥10–17 የተዘረዘሩት የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያዎች ያስፈልጉዋቸዋል። እነርሱም፤ እውነት፥ ጽድቅ፥ ሰላም፥ እምነት፤ ደኅንነትና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። ነፃ ወደ ማውጣት አገልግሎት ከመግባታችን በፊት በጸሎት መዘጋጀቱ በጣም ጠቃሚ ነው (ማር. 9፥28–29፤ ኤፌ. 6፥18)። አንዳንድ ክርስቲያኖች በማርቆስ 9፥29 ላይ ያለው ቃል «በጸሎት» ብቻ ሳይሆን «በጾምና በጸሎት» ተብሎ መተርጎም እንዳለበት ያምናሉ፤ ስለዚህም ነፃ የማውጣቱ አገልግሎት ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት የተለየ ጊዜ መመደቡ አስፈላጊ ነው ማለት ነው። የሚቻል ከሆነ ነፃ የማውጣትን አገልግሎት ከሌሎች ጋር እንጂ ብቻችንን ባናደርገው መልካም ነው። በዚህ ነፃ የማውጣት አገልግሎት የተሰማሩ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ ክርስቲያኖች መሆን አለባቸው (የሐዋ. 19፥13–16)።

ወደ አገልግሎቱ ከመግባታችን በፊት ከምንጸልይለት ሰው ጋር መወያየት ይኖርብናል። ክርስቲያን ካልሆነ፥ ክርስቲያን ለመሆንም ፈቃደኛ ካይደለ (እንዲህ ከሆነ ደግሞ ያለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሆናል) ወይም ደግሞ ከተጸለየለት በኋላ ክትትል ማድረጉ የማይቻል ከሆነ፥ እንግዲህ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ለመጸለይ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል ማለት ነው። አጭርና በችኮላ የሚደረግ ጸሎት የሰውየውን ችግር ከበፊቱ ይልቅ ሊያባብሰው ይችላል (ማቴ. 12፥43–45)። አንዳንዶች ደግሞ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ጣዖታት ካላወጣና ካላጠፋ በቀር ሰውየው ነፃ መውጣት እንደማይችል ያስባሉ (የሐዋ. 19፥19)። አለበለዚያ ግን ክፉው መንፈስ በቀላሉ ይመለስበታል።

ብዙ የሥጋ በሽታዎች ከአጋንንት ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ የአእምሮና የአካል ሕመሞች ደግሞ ከአጋንንት ጋር የተያያዙ መስለው ይታያሉ፤ ግን ላይሆኑም ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል የሚጥል በሽታ ከአጋንንት ጋር የተያያዘ መስሎ ሊታየን ይችላል፤ ብዙ ጊዜ ግን ከአንጎል መጎዳት ጋር የተያዘ ሆኖ ይገኛል። እዚህ ላይ መናፍስትን የመለየት ስጦታ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ይህ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ስጦታ ሲሆን የግለሰቡ ችግር ከአጋንንት ጋር የተያያዘ መሆን አለመሆኑን ለይተን እንድናውቅ ያስችለናል (1ቆሮ. 12፥10)።

ነፃ የማውጣትን አገልግሎት ከመጀመራችን በፊት የእግዚአብሔርን ጥበቃ መጠየቅ አለብን፤ በዚህም አገልግሎት የሚሳተፉ ሁሉ ክርስቲያኖች መሆን አለባቸው (የሐዋ. 19፥13–16)። ሰይጣንና ኃይላቱ ሁሉ መታሠር አለባቸው (ማቴ. 16፥19፤ 18፥18)። የሚጸለይለትም ሰው ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት። ለፈውስ ስንጸልይ እግዚአብሔርን «መጠየቃችን» ነው፤ (ድምፃችንን ዝቅ አድርገን ወይም በልባችን ሊሆን ይችላል)። ስለነፃ ማውጣት ስንጸልይ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና ሥልጣን አጋንንቱ እንዲወጡ «እናዝዛቸዋለን» (ሉቃ. 10፥17፤ ሐዋ. 16፥18፤ 19፥13–16) ይሁን እንጂ ከሚገባ በላይ መጮህ የለብንም፤ የሰው ጩኸት አጋንንቱን ሊያስደነግጠው አይችልም። አጋንንቱ ሰውየውን ወይም ሌሎችን ሳይጎዳ እንዲወጣ ለፍርድ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲቀርብ መታዘዝ አለበት። የኢየሱስ ስም ኃይል ስላለው ወዲያውኑ ነፃ ያወጣል፤ ሰውየውም ነፃ መውጣቱን ያውቃል።

የጸለይንለት ሰው ከአጋንንት ነፃ ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ፍቅርና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ልንጸልይለት ይገባል (ማቴ. 12፥43–45)። ነፃ የወጣው ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አለበት። ሰይጣንን መቃወም እንዲችልና አጋንንቱ ወደ ሕይወቱ እንዲመለስ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ከምናስባቸው ኃጢአቶች እንዲርቅ ልናስተምረው ይገባል (ያዕ 4፥7፤ 1ዮሐ. 1፥9)። አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ነፃ እንዳይወጣ የሚያግዱ ዋና ዋና ምክንያቶች፤ አለማመን (ማቴ. 17፥16–20)፥ ክርስቶስን አለመቀበል፥ ሌሎችን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ አለመሆን፥ ኃጢአትን አለመናዘዝና መንፈሱን አለመለየት ናቸው። (መንፍሱን ካልለየን ደግሞ አጋንንት ከሌሉበት ሰው አጋንንትን ማውጣት እንሞክራለን ማለት ነው)።

## ማጠቃለያ

ፈውስና ነፃ ማውጣት እግዚአብሔር ምን ይህል እንደሚወደን፥ እንዲሁም እግዚአብሔር ለመንፈሳችን ብቻ ሳይሆን ለአእምሮአችንና ለአካላችንም እንደሚያስብ ያመለክታሉ። እግዚአብሔር ከሕመማችንና ከድካማችን ሊፈውሰን ከባርነት ነፃ ሊያወጣንም ዝግጁ ነው። እግዚአብሔር ኦሪቾን እንዲሳካና ጤንነትም እንዲኖረን ይፈልጋል (3ዮሐ. 2)።

# ክፉን ስለመቃወም — የእኛ ድርሻ እስከ ምን ድረስ ነው?

## መሪ ጥቅሶች

ዘጸ. 20፥13 — አትግደል

ዘጸ. 21፥12–17፤ 22፥18–20 — ለአንዳንድ ኃጢአቶች የተሰጠ የሞት ቅጣት።

ኢያ. 8፥1–8 — ሰዎች በጦርነት እንዲጠፉ እግዚአብሔር ትእዛዝ ስጥቶአል።

1ሳሙ. 15፥2–3 — ሰዎች በጦርነት እንዲቀጡ እግዚአብሔር ትእዛዝ አውጥቶ ነበር።

ማቴ. 5፥38–48 — ክፉ የሚያደርግባችሁን ሰው አትበቀሉት፤ ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ግራ ጉንጭህን አዙርለት ... ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤

ሉቃ. 6፥30 — ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፥ ገንዘብህን የሚወስድብህን ሰው እንዲመልስልህ አትጠይቀው።

ሮሜ 13፥1–7 — መንግሥታዊ አቋም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ሲሆን ዓላማውም ክፉዎችን ለመቅጣት ነው።

1ጴጥ. 2፥13–14 — ባለሥልጣኖች የተሰየሙት በእግዚአብሔር ሲሆን ዓላማውም ስሕተት የሚሠሩትን ለመቅጣት ነው።

## ጥያቄዎቹ

ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረንም ያሳየንም እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ነው፤ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ አላጠፋም (አልሻረም) (ማቴ. 5፥17)፤ ይሁን እንጂ ሁለቱን በምናወዳድርበት ጊዜ ሕግ ከሚለው ይልቅ የኢየሱስ ትምህርቶች ጠለቅ ያሉና በጣም መንፈሳውያን የሆኑ ናቸው፤ ሕግ ብዙ ጊዜ የሚያወራው ስለ ሰዎች ውጫዊ ጠባይ ነው፤ ኢየሱስ ግን ሰዎች በልባቸው የሚያስቡትን ነገር ይመለከት ነበር፤ ከሕግ ብዙ ነጥቦችን በመውሰድም ያጠነከራቸው ነበር፤ ይህንንም ያደረገው ከሕግ ይልቅ ፍቅር ብልጫ እንዳለው በማሳየት ነው።

ለምሳሌ ሕጉ ግድያን ይኮንናል፤ ኢየሱስ ግን በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ቁጣና ጥላቻ እንኳን ይፈርድበታል (ማቴ. 5፥21–22)፤ ሕጉ «አታመንዝር» ይላል፤ ኢየሱስ ግን በሰው ክፉ የፍትወተ ሥጋ ምኞት ላይ ይፈርዳል (ማቴ. 5፥27–28)፤ ሕግ ባልንጀራችንን እንድንወድድ ያዘናል፤ ኢየሱስ ግን «ጠላቶቻችሁንም ውደዱ» ብሎ አዝዞናል (ማቴ. 5፥43–47)፤ ሕግ ከመጠን ያለፈ ግላዊ በቀል እንዳንወስድ ይከለክለናል፤ ኢየሱስ ግን «ጨርሶ ምንም ዐይነት በቀል አትውሰዱ» በማለት ያዝዘናል፤ እርሱም «. . . *ክፉ የሚያደርግባችሁን ሰው አትበቀሉት፤ ነገር ግን ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ግራ ጉንጭህን አዙርለት፤ አንድ ሰው ሸሚዝህን ለመውሰድ ፈልጎ ቢከስህ ኮትህንም እንዲወስድ ተውለት*» ብሎናል (ማቴ. 5፥39–40)፤ ኢየሱስ እንደገናም «*ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ ገንዘብህንም የሚወስድብህንም ሰው እንዲመልስ አትጠይቀው*» ብሎአል (ሉቃ. 6፥30)፤ በድጋሚም «*ሰዎች ለእናንተ ሊያደርጉላቸሁ የምትፈልጉትን እናንተም እንዲሁ ለእነርሱ አድርጉላቸው*» ብሎ ተናግሮአል (ማቴ. 7፥12፤ ሉቃ. 6፥31)።

ክፉውን ስለመቃወም ብዙ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ፤ ክፉውን ጨርሶ መቃወም የለብንም ማለት ነውን? ስሕተት የሚሠሩትን ለመቃወም ጨርሶ ምንም ኃይል መጠቀም የለብንም ማለት ነውን? ጳውሎስና ጴጥሮስ «የመንግሥት ባለሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙት አጥፊዎችን ለመቅጣት ነው፤ *እነርሱም ሰይፍ የታጠቁት በከንቱ አይደለም*» ይላሉ (ሮሜ 13፥1–7፤ 1ጴጥ. 2፥13–14)። ማኅበረ ሰቦችና የመንግሥት ተቋማት በኀይል እንዳይጠቀሙና ማንንም እንዳይጎዱ ታዝዘዋልን? እንዲህ ከሆነ ክርስቲያን የፖሊስ አባል ሊሆን ይችላልን? ወንጀለኞችንስ ለመቆጣት በጠመንጃ ወይም በዱላ መጠቀም ይችላልን? ክርስቲያን የፍርድ ቤት ዳኛስ ሊሆን ይችላልን? በበደለኛውስ ላይ የሥጋ ቅጣት ማስተላለፍ ወይም የሞት ቅጣት ማስተላለፍ ይችላልን? ደግሞስ ክርስቲያን የጦርሠራዊት አባል በመሆን በጦርነት ሊዋጋ ይችላልን?

**የመጀመሪያ አመለካከት፦** ማንም ሰው ቢሆን ክፉውን መቃወም የለበትም

ብዙ ክርስቲያኖች «ማንም ሰው በምንም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ቢገኝ ክፉ አድራጊውን ለመቃወም ኃይል መጠቀም የለበትም» የሚል እምነት አላቸው፤ ኢየሱስ የጠየቀን እርሱን እንድንከተል ነው (ማር. 8፥34–35)፤ ትሑት አገልጋዮችም እንድንሆን ምሳሌ ትቶልናል (ማር. 10፥42–45)፤ ክርስቶስን በመከራው እንድንከተለው ታዝዘናል (1ጴጥ. 2፥19–24)፤ ጳውሎስ «ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በጭራሽ አትበቀሉ» ብሎናል (ሮሜ 12፥17–21፤ 1ተሰ. 5፥15)፤ ጴጥሮስም በበኩሉ «የሚረግሙአችሁን መርቁ» ይለናል (1ጴጥ. 3፥8–9)። እነዚህ ክርስቲያኖች ሕግ በክርስቶስ እንደተፈጸመ ያምናሉ (ማቴ. 5፥17)፤ ታዲያ ክርስቶስ ስለ ፍቅር ያለው አስተሳሰብ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም ግብረገባዊነቱ ከፍ ብሎ የሚታይ ነው፤ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ወደ «ፍቅር ሕግ» ስለለወጠው (ሮሜ 13፥10)፥ በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር የተፈቀደ ነገር ዛሬ የክርስቲያኖች መለኪያ ሊሆን አይችልም።

ስለዚህ እነዚህ ክርስቲያኖች «አማኞች በጦር ሠራዊት ውስጥ ተገኝተው ሰብአዊ ፍጡሮችን መውጋትና መግደል አይገባቸውም» የሚል አስተሳሰብ አላቸው፤ የጦርነት መነሻ ምክንያት ኃጢአት መሆኑን ያመለክታሉ (ያዕ. 4፥1–4)፤ ስለሆነም «*ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉ*» (ማቴ. 26፥52) የሚሉትን ጥቅሶች ይጠቀማሉ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩት በቀድሞዎቹ ጦርነቶች ለእስራኤላውያን ይዋጋ የነበረው ራሱ እግዚአብሔር እንደነበረም ያስታውሳሉ (ዘጸ. 14፥13–14፥ 24–28፤ ኢያ. 5፥13–15፤ 6፥1–5፤ መሣ. 4፥14–15፤ 7፥2–7፥22)፤ በኋላም በእግዚአብሔር ያልተፈቀዱ ጦርነቶች በነቢያት እንደተወገዙ ያወሳሉ። ነቢያት እስራኤላውያንን በእግዚአብሔር መደገፍ እንጂ በጦርሠራዊት ብዛት መታመን እንደማይኖርባቸው የሚያስጠነቅቁዋቸው ነበሩ (ኢሳ. 31፥1–3፤ ዘካ. 4፥6)፤ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ቢሆን እግዚአብሔር ሰዎች ሰላማውያን እንዲሆኑ ግልጥ ባለ ሁኔታ መለኪያውን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ያሳይ ነበር፤ ለምሳሌ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ቢጠይቅ አልተፈቀደለትም፤ ምክንያቱም በጦርነት እጆቹ በደም ተበክለው ስለነበር ነው (1ዜና. 28፥3)።

ጦርነትን በሚመለከት፥ ከነዚህ ክርስቲያኖች አብዛኛዎቹ «ሰውን በሞት መቅጣት ትክክል አይደለም» በማለት ያምናሉ፤ ክፉዎችን መቃወም አይገባም ከሚሉት ጥቅሶች ጋር (ማቴ. 5፥39)፥ ኢየሱስ ስታመነዝር የተያዘችውን ሴት እንዳትቀጣ መከልከሉን ጨምረው ያመለክታሉ (ዮሐ. 8፥1–11)፤ ስለዚህ ከእነዚህ ክርስቲያኖች ብዙዎቹ «ክርስቲያን ዳኛ ወይም የመንግሥታዊ አስተዳደር አባል መሆን አይገባውም፤ ምክንያቱም በዚያ ምክንያት ክፉ አድራጊዎችን ለመቅጣት ሰይፍ ይጨብጣል፥ የሞት ፍርድም ለመስጠትና ወደ ጦርነትም ለማዝመት ይወስናል» በማለት ያስባሉ፤ እንዲሁም «ክርስቲያን የፖሊስ አባል መሆን አይችልም» በማለት ያምናሉ፤ ምክንያቱም ፖሊስ የሚሆን ሰው በሌላው ሰው ላይ ጭካኔ ያሳያል ወይም ማኅብረሰብን ለመጠበቅ ሲል ወንጀለኛውን ሊገድል ይችላል፤ እንደዚህ የሚያምኑ ሰዎች «እኛ እኮ የሰማይ ዜጎች ነን፤ ከምድራዊ አሳብ ጋር ምንም ከፍል የለንም (ፊል. 3፥20)፤ እኛ የተጠራነው ለሰላም ሕይወት ነው» ይላሉ ዕብ. 12፥14)። ምንም እንኳ እነዚህ ክርስቲያኖች ራሳቸው ከመንግሥት ጋር ምንም ከፍል እንደሌላቸው ቢቆጥሩም፥ ለአገራቸው መንግሥት ግብር ይከፍላሉ፤ ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ይጸልያሉ (ማር. 12፥13–17፤ ሮም 13፥1–7፤ 1ጢሞ. 2፥1–2፤ 1ጴጥ. 2፥13–17)።

**ሁለተኛ አመለካከት፦** ክፉውን መቃወም የሚገባቸው በሥልጣን ላይ የሚገኙ ሰዎች ብቻ ናቸው።

ሌሎች ብዙ ክርስቲያኖች ይህንን የኢየሱስን አባባል በተለየ መንገድ ይተረጉሙታል፤ እነዚህ ክርስቲያኖች «እያንዳንዱ አማኝ በግላዊ ኑሮው የኢየሱስን ቃል መከተል ይኖርበታል» ብለው ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ የኢየሱስ ንግግር ስለ መንግሥታት ወይም ስለፖሊስ ሠራዊትና ሕዝባዊ አገልግሎትን ስለሚፈጽሙ ሌሎች ባለሥልጣናት በሚመለከት አልነበረም፤ እኛም አማኞች በግለሰብ ደረጃ በአንድ «ወንድም» ወይም «ባላንጣ» ተበድለን ቢሆን ኢየሱስ የሚለን «ቁጣህን ተው? ከወንድምህ ጋር ታረቅ፤ ከባላንጣህ ጋር ተስማማ» ነው የሚለን (ማቴ. 5፥22–26)። በግለሰብ ደረጃ አንዱ በጥፊ ቢመታን ከእርሱ

ጋር መደባደብ ወይም መበቀል አይኖርብንም። ይልቁንም ሌላውን ጉንጫችንን አዙረን በመስጠት ፍቅራችንን ማሳየት ይኖርብናል (ማቴ. 5፥38–41)፤ በግል ደረጃ ለሚለምነን መስጠት ወይም ማበደር ይኖርብናል (ማቴ. 5፥42)፤ ይህንንም ማድረግ የሚገባን ለጠላቶቻችንም ጭምር ነው (ሉቃ. 6፥35)፤ በዚህ በሁለተኛው አመለካከት ኢየሱስ የሚናገረው በግል ደረጃ ነው።

እነዚህ ክርስቲያኖች በተጨማሪም ሌላ የሚሉት ነገር አላቸው፤ ኢየሱስ ይናገር የነበረው የጦር መሣሪያ ባልታጠቀ ሕዝብ መካከል ለሚገኙ ግለሰቦች ነበር። ይህን በሚናገርበት ጊዜም በባላገር በየቀኑ ስለሚገጥመው የኑሮ ክርክር እያሰበ ሳይሆን አልቀረም፤ ኢየሱስን ይሰሙ የነበሩ ሰዎች ንግግሩን ለፖሊስ ወይም ለጦር ሠራዊት እንደተናገሩ አድርገው አልቆጠሩም፤ በዚህ አመለካከት መሠረት እነዚህ ባለሥልጣናት ክፉውን የሚቃወሙ ናቸው። ከዚህም በላይ እነዚህ ክርስቲያኖች «ባለሥልጣናቱ ስሕተት ሠርተው ከተገኙ እነርሱንም ቢሆን መቃወም ያስፈልጋል» ይላሉ። ለምሳሌ በአዲስ ኪዳን ባለሥልጣናትን ስለመቃወም ሦስት ምሳሌዎችን እናገኛለን፤ ከእነዚህም ምሳሌዎች የመጀመሪያው ኢየሱስ ራሱ ተቆጥቶ ክፉውን እንደተቃወመ፤ ሰዎችን በጅራፍ በመግረፍ ከቤተ መቅደስ እንዳስወጣና የገንዘብ ጠረጴዛዎችንም እንደገለበጠ እናገኛለን (ዮሐ. 2፥13–16)። ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ያለ አግባብ አንድ ሰው ጉንጩን በጥፊ ሲመታው መቃወሙን እንመለከታለን (ዮሐ. 18፥19–23)። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ጳውሎስ ለበላይ ፍርድ ቤት ባመለከተ ጊዜ በራሱ ላይ የተደረገውን ክፉ ሥራ እንደተቃወመ ያሳያል (የሐዋ. 25፥11)፤ እነዚህ ምሳሌዎች ስለ ተጠቀሱ እነዚህ ክርስቲያኖች እኛም በዚህ መንገድ ክፉዎችን መቃወም እንደሚኖርብን ያምናሉ።

ጦርነትንም አስመልክቶ እነዚህ ክርስቲያኖች ጦርነት ኃጢአት እንደሆነ ይገነዘባሉ። ይሁን እንጂ መንግሥት ክፉ አድራጊዎችን የሚቀጣበት ሰይፍ መያዙን ጳውሎስ ይደግፋል በማለት ይጠቅሳሉ (ሮሜ 13፥4)። ዮሐንስ መጥመቁን ጥቂት ወታደሮች «እውነተኛ ንስሐ ለመግባት ምን ማድረግ ይኖርብናል?» ብለው ጠየቁት፤ እርሱም «የሚከፈላችሁ ደመወዝ ይብቃችሁ» አላቸው እንጂ «ከእንግዲህ ወዲህ ወታደር መሆን አይገባችሁም» አላላቸውም (ሉቃ. 3፥14)። እነዚህ ክርስቲያኖች ነገሮችን ለያይተው ይመለከታሉ። ለምሳሌ በአንድ በኩል በብሉይ ኪዳን ሕግ በእግዚአብሔር የተፈቀዱ ኢየሱስ ግን ጨርሶ ማድረግ አይገባችሁም ያለው እንደ መፋታት (ማቴ. 5፥31)፤ እንደ መሐላ (ማቴ. 5፥33) ያሉት ይጠቀሳሉ። በሌላ በኩል እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በተለይ እንዲፈጸሙ ያዘዛቸው ነገሮችና ኢየሱስም ቢሆን የእነርሱን መኖር ያልተቃወማቸው እንደ ፍርድ ስለ ሞት ቅጣት ወይም በትክክለኛ ምክንያት የሚደረግ ጦርነት ያሉት ናቸው (ዘኁ. 31፥1–7፤ ኢያ. 6፥8፤ መሣ. 4፥14–16፤ 7፥2–22፤ 1ሳሙ. 15፥2–3)። ዮሐንስ በራእይ ኢየሱስን በመጨረሻው ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት ለማድረግ የሚነሡትን ጨርሶ ለማጥፋት የሚመጣ የጦር መሪ አድርጎ ያቀርበዋል (ራእ. 19፥11–19)። ስለዚህ እነዚህ ክርስቲያኖች ብዙ ጦርነቶች ትክክል እንዳልሆኑና ስሕተት መሆናቸውንም ይረዳሉ፤ አንዳንድ ጦርነቶች ደግሞ ትክክልና አስፈላጊ መሆናቸውንም ያምናሉ። ከእነዚህ ክርስቲያኖች አብዛኛዎቹ የሞት ቅጣትም መኖር እንዳለበት ያምናሉ፤ በአዲስ ኪዳን እንኳ እግዚአብሔር በጴጥሮስ ተጠቅሞ በእግዚአብሔር ላይ ሐሰት የተናገሩ ሁለት ሰዎች መሞት እንዳለባቸው ተናግሮአል (የሐዋ. 5፥1–10)፤ እነዚህ ወገኖች «ጦርነት ወይም የሞት ቅጣት ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አንዳንድ የተጓደሉ ፍትሐችን ለመቃወም ወይም የአንዳንድ ኃጢአቶችን አስከፊነት ለማሳየት የሚጠቀምበት መንገድ ነው» ብለው ያምናሉ።

በመንግሥት ውስጥ ስለሚኖራቸው የሥራ ድርሻ እነዚህ ክርስቲያኖች የሚያመለክቱት ጳውሎስ የተናገረውን ነገር ነው፤ እርሱ «ለመንግሥት ታዘዙ፤ ሕጎችን ፈጽሙ፤ ታክስም ክፈሉ» ብሎአል ይላሉ (ሮሜ 13፥1–7)፤ ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ የሮም ገዥ ክርስቲያኖችን በጭካኔ የሚያሳድድ ቢሆንም ጳውሎስ በበኩሉ *ባለሥልጣናት ሁሉ በእግዚአብሔር የተሾሙና የእግዚአብሔር አገልጋዮችም* እንደሆኑ ይናገር ነበር (ሮሜ 13፥1፥4፥6)፤ የታክስ ሰብሳቢዎችም ቢሆኑ ሥራቸውን ለቅቀው መሄድ የለባቸውም፤ ነገር ግን ተገቢውን ታክስ ብቻ መቀበል ይኖርባቸዋል (ሉቃ. 3፥12–13፤ ሮሜ 13፥6–7)፤ እነዚህ ክርስቲያኖች «የመንግሥት አስተዳደር ወይም የፖሊስ ሠራዊት አባል መሆን መልካም ነው፤ በዚህ ዓይነት የመንግሥት አስተዳደርም ሆነ የፖሊስ ሠራዊት የእግዚአብሔርን የፍትሕ መንገድ እንዲከተሉ በተገቢውም ጊዜ ምሕረት እንዲያደርጉ ለማደፋፈር ይቻላል» የሚል እምነት አላቸው፤ እንደገናም «ክርስቲያኖች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ እንደ ብርሃን ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል» ይላሉ (ማቴ. 5፥14–16)፤ እነርሱ በግል ደረጃ ለመበቀል የራሳቸውን ንብረት ለመጠበቅ የሚያጠቁአቸውን መልሰው ማጥቃት እንደሌለባቸው ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ የፖሊስ ሠራዊት ወይም የመንግሥት አስተዳደር አባል በሚሆኑበት ጊዜ ግን «ክፉ አድራጊዎች መቀጣት አለባቸው፤ የሌሎችም ንብረት መጠበቅ አለበት» የሚለውን አሳብ ያስፈጽማሉ።

**ሦስተኛው አመለካከት፦ ግለሰቦችም በተናጠል ክፉውን መቃወም ይችላሉ**

ሦስተኛዎቹ የክርስቲያን ክፍሎች «ማንኛውም ግለሰብ አስፈላጊ ከሆነ በዓመፃ ተጠቅሞ ክፉውን መቃወም ይችላል» የሚል እምነት አላቸው። እነዚህ ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ኢየሱስ ክፉውን ስለመቃወም ትምህርት ሲሰጥ ሰው በማንኛውም ሁኔታ ይጠቀምበታል ብሎ አላሰበም። እነዚህ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስን የሚሰሙ ሰዎች ባይናገሯቸውም እንኳን ሊያስተውሉት የሚችሉት ግልፅ የሆኑ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ አንድ ሰካራም አንዱን ጨዋ ሰው መትቶ ሊገድለው ቢሞክር ይህ ሰካራም በተቻለ መንገድ ሁሉ ሊገታ ይገባዋል፤ በተጨማሪም ልጆች ወላጆቻቸውን በጥፊ መምታት ወይም መሳደብ አይገባቸውም፤ አንዱን ጣፋጭ ሲከለክሉ ሌላውን ጣፋጭ መፍቀድ አይገባም በማለት አሳባቸውን ይሠነዝራሉ። ሁላችንም ብንሆን ክፉውን መቃወም እንደሚገባን እግዚአብሔር የሚፈልግ መሆኑን የሚያስረዱ እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ምሳሌዎችም አሉ በማለት ያምናሉ።

እነዚህ ክርስቲያኖች «ጥቃቱ የተሠነዘረው በራስ ላይ በሆነ ጊዜ እንኳን ግለሰቦች ዓመፀኛ ወንጀለኛን ሊቃወሙ ይችላሉ» የሚል እምነት አላቸው። እነርሱ እንደሚያምኑት ከኢየሱስ አነጋገሮች አንዳንዶቹ በጣም የመጠቀ አስተያየት ያላቸው ናቸው። ኢየሱስ ግን ይጠቀምባቸው የነበረው እኛ ቃል በቃል እንድንተረጎማቸው ሳይሆን (ማቴ. 5፥29–30)፥ ትምህርቱን ግልጥና ጉልህ አድርጎ ለማሳየት ነበር። እነርሱም የሚያመለክቱት በኢየሱስ ዘመን የነበረ ማንኛውም አስተማሪ ይህን የመሰለ ግነታዊ የአነጋገር ዘይቤ ብዙ ጊዜ ይጠቀም እንደነበረ ነው። እነርሱ ክርስቲያን የሚያጠቃው ሰው እንኳ ቢኖር ከሰው ጋር ጨርሶ መጣላት አይገባውም ይላሉ (ማቴ. 5፥39)፤ «ነገር ግን አንድ ሰው በእኛ ላይ ቋሚ ጉዳት ሊያደርግ ቢፈልግ ወይም ሊገድለን ቢሞክር ራሳችንን ለማዳን ስንል መልሰን ልንቃወመው እንችላለን» ይላሉ፤ ክርስቲያኖች ለጠላቶቻቸው መልካም ማድረግ እንዳለባቸውና ሌሎች ሰዎች በጣም የተቸገሩበት ነገር ካለ በልግሥና በመስጠት ምሕረት ማሳየት እንደሚገባ ያምናሉ (ማቴ. 5፥43–44፤ ሉቃ. 6፥30–36)፤ ነገር ግን እነርሱ አንድ ያልተቸገረ ሰው ቢለምነን ወይም ሊሰርቀን ቢሞክር ገንዘባችንን ሁሉና ንብረታችንን በሙሉ መስጠት ይገባናል ብለው አያምኑም።

እነዚህ ክርስቲያኖች ከዚህ በፊት በሁለተኛው አመለካከት የተጠቀሱትን ክርክሮች በሙሉ ይቀበላሉ፤ ማለትም በፖሊስ፣ በጦር ሠራዊትና በመንግሥት ሥራ መካፈል የመሰሉትን ይቀበላሉ፤ በነዚህ ሥራዎች መካፈል ልንቀበለው የሚገባ ነገር ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን እንደሚችልም ያምናሉ።

ጥቂት ክርስቲያኖች ከነዚህ ከሦስት አመለካከቶች አንዳንዶቹ ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ሊወስኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለነዚህ ጥያቄዎች ወደ ውሳኔ ሊደርስ የሚገባው በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በቂ ማሰላሰልና ጸሎት እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ካገኘ በኋላ መሆን አለበት። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመረምር የበሰሉ መንፈሳዊያን ክርስቲያኖች በነዚህ ጥያቄዎች የተለያየ አሳብ እንደነበራቸው እናገኛለን፤ መጽሐፍ ቅዱስም ለነዚህ ጥያቄዎች ግልጥ ያለ መልስ አይሰጥም። እኛም ብንሆን የትኛውንም አመለካከት ብንይዝ ሌላ አመለካከት በያዘ ሰው ላይ መፍረድ አይገባንም፤ ወይም የተለያየ አመለካከት በማያዛችን እርስ በርስ መጣላት አይኖርብንም።

## ስደት – የእኛ ምላሽ ነው

ክፉውን መቃወምን አስመልክቶ የሚነሳው ሌላ ጥያቄ ደግሞ በአማኞች ላይ የሚደረገው ስደት ነው። ስደት ስለምናደረገው መልካም ነገር ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን (ማቴ. 5፥10–11፤ ሉቃ. 6፥22፤ 1ጴጥ. 2፥20)፤ ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ የሚያደርሱት ሥቃይ ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ በአንድ መንገድ ወይም በሌላ ስደት እንደሚደርስባቸው አዲስ ኪዳን ያስተምረናል (ማር. 13፥9፤ ሉቃ. 21፥12፤ 2ጢሞ. 3፥12)። ኢየሱስም ክርስቲያኖች በመሆናችን ስደት ቢመጣብን እንዴት መመለስ እንዳለብን አስተምሮናል፤ ደስ እንድንሰኝ እንጂ (ማቴ 5፥10–12) መፍራት እንደማይገባን ነግሮናል (ማቴ. 10፥26)። ጳውሎስ በስደት ደስ ይሰኝ እንደነበረ ይነግረናል፤ ምክንያቱም በሚሰደድበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ጸጋ በብዛት ያገኝ ነበር። ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉን ነገር *በትዕግሥት* እንዲቀበል ይረዳዋል (2ቆሮ. 12፥7–10)። ሆኖም ኢየሱስ ደግሞ እንደ *እባብ ብልሆች* እንድንሆንና *ራሳችንንም በትጋት* እንድንጠብቅ ነግሮናል (ማቴ. 10፥16–17)።

አሳዳጆቻችንን በተመለከተ «*የሚያሳድዱአችሁን መርቁ* እንጂ *አትርገሙአቸው*» ተብለናል (ሮሜ 12፥14) እንድንወዳቸውና እንድንጸልይላቸውም ታዝዘናል (ማር. 5፥44)፤ በመንግሥት ባለሥልጣናት ፊት እንደምንቀርብና ወደ ወህኒም እንደምንጣል ተነግሮናል። ሆኖም ስለምንናገረው ነገር በቅድሚያ ማሰብ አይገባንም፤ በዚያን ጊዜ ምን መናገር እንዳለብን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ያስተምረናል (ማር. 13፥9–11፤ ሉቃ. 21፥12–19)።

ኢየሱስ በእርሱ በማመናችን ምክንያት ሰዎች ሲያጠቁን እኛም መልሰን ማጥቃት እንዳለብን አላስተማረንም። ራሱ ኢየሱስ ከመያዙ በፊት ለደቀመዛሙርቱ ሰይፍ እንዲገዙ ነግሮአቸው ነበር (ሉቃ. 22፥35–38)፤ ነገር ግን በሰይፋቸው እርሱን እንዲከላከሉ አልፈቀደላቸውም (ሉቃ. 22፥51)። ይልቁንም «ሰይፍ የሚመዝዙ በሰይፍ ይጠፋሉ» በማለት አስጠነቀቃቸው (ማቴ. 26፥52)፤ ብዙ ክርስቲያኖች በኢየሱስ በማመናቸው ምክንያት ስደት የሚደርስባቸው ሰዎች በዓመፅ ራሳቸውን መከላከል እንደሌለባቸው ያስባሉ።

## ማጠቃለያ

ስለነዚህ ኢየሱስ ስለተናገራቸው ከባድና አስቸጋሪ አባባሎች የፈለገውን አስተሳሰብ ብንከተልም የተቻለውን ያህል በሰላም መኖር እንዳለብን ክርስቲያኖች በሙሉ ይስማማሉ፤ (ዕብ. 12፥14)። የጌታ መንግሥት በምድር ላይ በሚመሠረትበት ቀን ሊኖር የሚችለውን አስደሳች ሁኔታ በናፍቆት ወደፊት ለማግኘት እንቃትታለን፤ በዚያን ቀን ሰዎች *ሰይፋቸውን ወደ ማረሻ፥ ጦራቸውንም ወደ ማጭድ ይለውጣሉ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ጦርነት አያነሣም፥ ከዚያም በኋላ የጦር ትምህርት የሚማር አይኖርም* (ኢሳ. 2፥4፤ ሚካ. 4፥3)። እስከዚያም ጊዜ ድረስ *የሚቻላችሁ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አድርጉ* (ሮሜ 12፥18)።

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት

## መሪ ጥቅሶች

ሕዝ. ከምዕራፍ 37–47 የእስራኤል መታደስ፥ የሚደርስባቸው የጦርነት ወረራ፥ የአዲሱ ቤተመቅደስ መሠራት።

ዳን. ከምዕራፍ 7–12 ዳንኤል ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ያያቸው ራእዮች።

ማቴ. ምዕራፍ 24 የመጨረሻ ዘመን ምልክቶች።

ማር. ምዕራፍ 13 የመጨረሻ ዘመን ምልክቶች።

ሉቃ. 17፥20–37፤ 21፥5–36 የእግዚአብሔር መንግሥት ስለ መምጣቱ።

1ቆሮ. 15፥12–58 በአካል ስለመነሣት።

1ተሰ. 4፥13–18 ስለ ጌታ መምጣት።

2ተሰ. 2፥1–10 ጌታ ከመምጣቱ በፊት *ዓመፀኛው ሰው* ይገለጣል።

2ጴጥ. 3፥3–13 በጌታ ቀን ሁሉ ነገር በእሳት ይጠፋል።

1ዮሐ. 2፥18፤ 4፥1–3 የክርስቶስ ተቃዋሚና የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ።

ራእ. ከምዕራፍ 6–22 ስለ እግዚአብሔር ቁጣ፥ ስለ ሰው መከራ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ ስለሚያደርጋቸው ነገሮችናስለ ክርስቶስ ድል አድራጊ መንግሥት።

## የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኢየሱስ ክርስቶስ «በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ ዳግመኛ ተመልሶ ይመጣል» የሚለውን አሳብ ክርስቲያኖች ሁሉ ያምናሉ (ማቴ. 25፥31–46፤ ራእ. 20፥11–15 አጠቃላይ ጽሑፍ ላይ መግቢያ የሚለውን ይመለከቷል)። ኢየሱስ ስለራሱ መሞትና መነሣት ብቻ አስቀድሞ አልተናገረም (ማቴ. 16፥21፤ ማር. 8፥31–32፤ 9፥9–10፤ 10፥33–34)፤ ነገር ግን ስለዳግም ምፅዓቱም አስቀድሞ ተናግሮአል፤ (ማቴ. 16፥27፤ 25፥31፤ ማር. 8፥38፤ 13፥26)። ከሞት ከተነሣም በኋላ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በማጽናናት አርባ ቀናት በምድር ላይ ኖረ (የሐዋ. 1፥3)። ወደ ሰማይ ማረጉን በተመለከቱበት ወቅት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ በነበረበት ሁኔታ ተመልሶ ይመጣል ተብሎ ለደቀመዛሙርቱ ተነገራቸው (ሉቃ. 24፥51፤ የሐዋ. 1፥9–11)። ገና ሲጀመር አንሥቶ ሐዋርያት ለአማኞች የክርስቶስን *ዳግም ምፅዓት እንዲጠብቁና ተሰፋ እንዲያደርጉ* ያስተምሩአቸው ነበር (የሐዋ. 3፥19–21፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 9፥28)።

ኢየሱስ እንደሚሄድና በመንግሥተ ሰማይ *ቦታ እንደሚያዘጋጅልን፥ ተመልሶም እንደሚመጣና ከእርሱ ጋር እንኖር ዘንድ ይዞን እንደሚሄድ* ቃል ገብቶልናል (ዮሐ. 14፥2–3)። ኢየሱስ ለተከታዮቹ በመጨረሻ ቀን ከሞት *እንደሚያስነሣቸውም* ተስፋ ሰጥቶአቸዋል (ዮሐ. 6፥39–40፤ 54)። በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ሕያው እንደሚሆኑም ጳውሎስ ነግሮናል። *ይህም እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል። የመጀመሪያው ፍሬ (በኩር) ክርስቶስ ነው፤ በኋላም በሚመጣበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ሁሉ ይነሣሉ። ከዚያ*

*በኋላ የመጨረሻው ጊዜ ይመጣል* (1ቆሮ. 15፥22-24)። ጳውሎስ ይህን በአካል መነሣታችንን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን የመጠቅለላችን የመጨረሻ ደረጃ ነው ይለናል። በዚህ ጊዜ ደኅንነታችን ፍጹም ስለሚሆን እኛ እንከብራለን (ሮሜ 8፥18-25፥30፤ ፊል. 3፥20-21 ከአጠቃላይ ጽሑፉ ላይ የደኅንነት መንገድ የሚለውን ይመለከቷል)።

ይህ ትንሣኤ በድንገት የሚፈጸም ክንዋኔ ነው። በአንደኛ ተሰሎንቄ 4፥13-17 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔር አስቀድመው የሞቱትን አማኞች *መንፈስ ከኢየሱስ ጋር ያመጣቸዋል* በማለት ጽፎአል። *ጌታ ራሱም በታላቅ የትእዛዝ ድምፅ፥ በመላእክት አለቃ ድምፅ ከሰማይ ይወርዳል፥ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል።* በክርስቶስ *ያምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚህ በኋላ እኛ በሕይወት የምንገኘው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን።* ለዘላለምም *ከጌታ ጋር እንሆናለን።* ሙታን ጨርሶ የማይሞት አዲስ ሰውነት ይሰጣቸዋል፤ በሕይወት ያሉትም አሮጌው ሰውነት *ተለውጦ* አዲስ ሰውነት ይለብሳሉ። *ይህም ሁሉ በድንገት ወይም በዐይን ቅጽበት የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ይሆናል* (1ቆሮ. 15፥51-53)። ኢየሱስ ከደመና *የመለከት ድምፅ* ይሰማል ብሎናል፤ ይህም የሚፈጸመው የተመረጡትን ለመሰብሰብ መላእክቱን በሚልክበት ጊዜ ይሆናል (ማቴ. 24፥30-31፤ ማር. 13፥26-27)። እንደገናም እንዲህ በማለት አስጠንቅቆናል፤ በአንድ አልጋ ላይ አብረው ከተኙ (ወይም በአንድ ማሣ ላይ አብረው ከሚሠሩ ወይም እህል አብረው ከሚፈጩ) ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛው ይቀራል (ማቴ. 24፥40-41፤ ሉቃ. 17፥34-35)። ብዙዎቹ ይህንን ሁኔታ ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር ያመሳስሉታል።

ዳግም ምፅዓት በራሱ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ፍትሕና ሰላምን በምድር ላይ *ያመጣል*። ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕ እንደሚሆን ብዙ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተመዝግበዋል። አንዳንዶቹ ትንቢቶች ስለሕዝቡ ኃጢአትና ሐዘን ክርስቶስ እንደሚሞት አስቀድመው ይናገራሉ (መዝ. 22፥1-31፤ ኢሳ. 53፥1-12፤ ዳን. 9፥25-26)። እነዚህም ትንቢቶች ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት ኢየሱስ በተሰቀለና ከሞትም በተነሣ ጊዜ ተፈጽመዋል። ሌሎች ትንቢቶች ደግሞ መሲሑ የጽድቅ መንግሥት በእግዚአብሔር ለተመረጡት ሕዝቦች ማለትም ለአይሁዳውያን እንደሚመሠረት ይናገራሉ (ኢሳ. 2፥1-4፤ 11፥1-16፤ ኤር. 23፥3-8፤ ሕዝ. 37፥15-28)። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ሕይወቱ እነዚህ ትንቢቶች አልተፈጸሙም።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ዳግም ምፅዓት በጣም ቅርብ እንደሆነ ወይም *በቶሎ* ሊሆን እንደሚችል አድርገው ይናገራሉ (ዕብ. 10፥25፤ ያዕ. 5፥9፤ 1ዮሐ. 2፥18፤ ራእ. 22፥7፥12፥20)። ነገር ግን ትክክለኛውን ቀን ወይም ሰዓት *ማንም ሰው* ሊያውቅ አይችልም (ማቴ. 24፥36፥44፤ ማር. 13፥32-35)። ኢየሱስም የእርሱ ለፍርድ መምጣት በሰማይ ላይ እንደሚታይ የመብረቅ *ብልጭታ* እንደሚሆን፤ መንግሥታት በሙሉ የእርሱን *ምልክት በሰማይ ላይ እንደሚመለከቱ*፤ በዚያን ጊዜም *ማልቀስ* እንደሚጀምሩ ተናግሯል (ማቴ. 24፥27፥30፤ ሉቃ. 17፥24፤ ራእ. 1፥7)። ኢየሱስ፥ ተመልሶ መምጣቱን፤ ሌባ ቤት ሰብሮ እንደሚገባ ወይም ሎሌዎቹ ሳያስቡትና ሳይጠነቀቁ ወደ ቤቱ ከሚመለስ ጌታ ጋር *ያመሳስለዋል* (ማቴ. 24፥42-51፤ ማር. 13፥34-37፤ ራእ. 3፥3፤ 16፥15)። ጳውሎስና ጴጥሮስም ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል (1ተሰ. 5፥1-4፤ 2ጴጥ. 3፥10)።

ይሁን እንጂ በቅድሚያ አንዳንድ ምልክቶች እንደሚኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፤ ከዚህም የተነሣ የኢየሱስ መምጫ *መቃረቡን* እናውቃለን (ማር. 13፥28-29)። ኢየሱስም[1] «*ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል*» ብሎናል (ማቴ. 24፥14፤ ማር. 13፥10)። *በመጨረሻዎቹ ቀናት* ክፉ ሰዎች በክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ፥ ብዙ ሰዎች እምነታቸውን ይተዋሉ፤ ብዙዎች ደግሞ በዳግም ምፅዓት *ያላግጣሉ* (ማቴ. 24፥9-14፤ 2ጢሞ. 3፥1-7፥13፤ 2ጴጥ. 3፥3-10፤ ይሁ. 17-19)። እንዲሁም በምድር ላይ ብዙ ጦርነቶች፥ የምድር መናወጦች፥ ረሀቦች፥ ተላላፊ በሽታዎች፥ እንደሚኖሩና፥ በፀሐይ በጨረቃና በከዋክብት ላይ ብዙ ምልክቶች እንደሚታዩ ኢየሱስ አስቀድሞ ተናግሮአል (ማር. 13፤24-28፤ ሉቃ. 21፥10-11፥ 25-26፤ ራእ. ምዕራፍ 6፥8፥9፥16)። ይህም የመከራ ዘመን «*ታላቁ መከራ*» ተብሎ ይጠራል (ዳን. 12፥1፤ ማር. 13፥19-20፤ ራእ. 7፥14)።

እንዲሁም ኢየሱስ፥ *ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት* ተገልጠው ልዩ ልዩ ምልክቶችንና *ተአምራትን በማሳየት ሰዎችን እንደሚያታልሉ* ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል (ማር. 13፥6፥21-23) ዮሐንስም በመልዕክቱ ሲጽፍ «ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መምጣታቸውን» ብቻ ሳይሆን፤ አንድ የተለየ *የክርስቶስ ተቃዋሚም ይመጣል* በማለት ነው (1ዮሐ. 2፥18-22፤ 4፥1-3)። ጳውሎስም ለተሰሎንቄን ሰዎች

---

[1] ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ እንደሚፈርስና ከተማይቱም በጦር ሠራዊት እንደምትከበብ ትንቢት ተናግሮአል (ሉቃ. 21፥6፥ 20-24)። በ70 ዓ.ም. ላይ ኢየሩሳሌምና በውስጧ የነበረው ቤተ መቅደስ በሮም ሠራዊት ፍርሶአል። አንዳንድ ምሁራን እንደሚያምኑት ኢየሱስ ትንቢት የተናገረበት አስጸያፊ ርኩሰት የሮም ንጉሠ ነገሥት ካሊጉላ (37-41 ዓ.ም.) የራሱን ምስል ይመለክ ዘንድ በሐውልት መልክ ቀርጾ በአይሁድ መቅደስ ውስጥ ሊያቆመው ሞክሮ ሳይሳካለት የቀረው ነው። ሌሎች ደግሞ ይህንኑ የኢየሱስ ትንቢት ወደ ፊት በመጨረሻ ቀኖች ይሆናል ብለው ያምናሉ።

በመደጋገም ያረጋግጥላቸው የነበረውም ነገር ይኸው ነው። *ሕገ ወጥ የሆነው የዓመፅ ሰው* ገና አልተገለጠም፤ ይህ ሰው ብዙ *አሳሳች ተአምራትን፥ ምልክቶችንና አስደናቂ ነገሮችንም ያደርጋል*፤ «እኔ *እግዚአብሔር* ነኝ» በማለት *በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ይቀመጣል* (2ተሰ. 2፥1-10፤ ራእ. 13፥14-15)። ይህ በቤተመቅደስ ውስጥ ቆሞ የሚታየው ጣዖት፤ ኢየሱስ በትንቢት ቃል «*የሚያረክሰውን አስጸያፊ ነገር በተቀደሰ ስፍራ ቆሞ ታያላችሁ*» በማለት ያስጠነቀቀው ነው (ዳን. 9፥26-27፤ 12፥11፤ ማቴ. 24፥15፤ ማር. 13፥14)።

በራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ 6-16 ያለው ክፍል በክርስቶስ ዳግም ምፅዓትና በጽድቅ መንግስቱ ላይ በመግዛቱ ፍፃሜአቸውን ስለሚያገኙ ታላላቅ መከራዎችና መዓቶች ምልክታዊ ራዕዮችን ያቀርባል። ከምዕራፍ 13-19 ያለው ክፍል ከባሕር እንደሚወጣ *አውሬ* ስለተመሰለ ስለ አንድ የፖለቲካዊ ገዥና የክርስቶስ ተቃዋሚ ለተባለው ብዙ ክፉ *ሥራዎችን* ስለሚሠራለት *ሐሰተኛ ነቢይ* የሚናገር ነው (ዳን. 7፥24-25፤ 9፥26-27፤ 11፥36-45፤ 12፥1-13፤ ማር. 13፥14፥22፤ 2ተሰ. 2፥1-10፤ 1ዮሐ. 2፥18)። ይህ ገዥ በምድር ላይ የሚገኙትን የጦር ሠራዊት ወደ አርማጌዶን ይሰበስባል፤ እርሱም እዚሁ ስፍራ ላይ ተመልሶ በሚመጣው በክርስቶስ ይሸነፋል (ራእ. 16፥16፤ 17፥14፤ 19፥11-21)። ሕዝቅኤል ከምዕራፍ 38-39 እና 2ተሰሎንቄ 2፥8 በድጋሚ ስለዚሁ ጦርነት ያወሳሉ።

ራእይ 20፥1-7 ስለ አንድ *ሺ ዓመት* ይናገራል፤ በዚህ በሺ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሰይጣን ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ስለሚታሰር ሕዝቦችን ማታለሉ ይቀራል። ይህም ክፍለ ዘመን «ሚሌኒየም» ተብሎ ይጠራል። ይህ ስም በላቲን «አንድ ሺ» ማለት ነው። በአውሬው አስከፊ ግዛት ውስጥ እርሱ ላቆመው ምስል አንሰግድም በማለት የተገደሉት ሰዎች ነፍሳት ከሞት ይነሣሉ፤ *የቀሩት ሙታን የሺው ዓመት ክፍለ ዘመን እስከሚፈጸም አይነሡም*። ከሞት የሚነሡት ግን ለአንድ ሺ ዓመት ከክርስቶስ ጋር አብረው ይነግሣሉ። ይህ የአንድ ሺ ዓመት ክፍለ ዘመን እንዳለቀ ሰይጣን ይፈታል፤ ሕዝቦችንም ማታለል ይጀምራል፤ በእግዚአብሔርና በሕዝቦቹ ላይ ጦርነት ለማስነሣትም ያሰባስባቸዋል። *ከሰማይም እሳት* ወርዶ ይደመስሳቸዋል፤ ሰይጣንም ወደ ገሃነም ይጣላል። *በሙታን የመጨረሻው ፍርድ ይበየንባቸዋል፤ ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ይጣላል* (ራእ. 20፥7-15)።

## ስለ ዳግም ምፅዓት ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ የተነገረ ቢሆንም፤ ብዙ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች አሉ። አንድም ጥቅስ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚሆኑትን ነገሮች የቅደም ተከተል ተራ አያስቀምጥም። ከዚህም የተነሣ ስለ ዳግም ምፅዓት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ቀርበዋል። እነዚህ ሦስት አመለካከቶች ስለ ኢየሱስ ዳግም ምፅዓት የተለያየ እምነት አላቸው፤ በተለይም በራእይ ምዕራፍ 20 ላይ ባለው በሺው ዓመት ጊዜ የተለያየ አሳብ ያቀርባሉ።

*የመጀመሪያው* አመለካከት «የሺ ዓመት *መንግሥት* በምድር ላይ አይኖርም» የሚል ነው። ይልቁንም ራእዩ ምሳሌያዊ በሆነ *መንገድ* የሚያመለክተው፤ ክርስቶስ በአሁኑ ወቅት ከሞቱ አማኞች ጋር በሰማይ ነግሦ *መኖሩን* ነው። ይህን የመጀመሪያውን አመለካከት የያዙ ክርስቲያኖች «ሺ ቁጥር የነገሮች *ሙሉ* በሙሉ መፈጸም ምልክት እንደሆነና የሚወክለውም በኢየሱስ የመጀመሪያና በዳግም ምፅዓቱ *መካከል* ያለውን *ሙሉ* ጊዜ ነው» በማለት ያምናሉ። *የዘንዶው* ወይም *የሰይጣን* (ራእ. 20፥2) መታሰር፤ ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ የሰይጣንን *መንግሥት* መገልበጡንና ሲቋቋመው የኖረውን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚያመለክት *መንፈሳዊ* ምልክት ነው ብለው ያምናሉ (ሉቃ. 10፥18፤ 2ተሰ. 2፥7፤ 1ዮሐ. 3፥8)። እነዚህ ክርስቲያኖች እስከ አሁን የሞቱ አማኞች *ነፍሳት* (ራእ. 20፥4) አሁን ያሉት ከክርስቶስ ጋር እንደሆነ አጥብቀው ይናገራሉ (2ቆሮ. 5፥6-8፤ ፊል. 1፥23-24፤ 1ተሰ. 4፥14፤ 2ጴጥ. 1፥13-14)። እንዲሁም *የእግዚአብሔር መንግሥት* አስቀድሞ ጀምሮአል (ማቴ. 11፥12፤ 12፥28፤ ቆላ. 1፥13)፤ ነገር ግን እንደዚህ ዓለም የሚታይ *መንግሥት* አይደለም ይላሉ (ሉቃ. 17፥20-21፤ ዮሐ. 18፥36-37፤ ሮሜ 14፥17)። እነዚህ ክርስቲያኖች *ሰባ ጊዜ ሰባት* የሚለው የዳንኤል ትንቢት (ዳን. 9፥24-27) በሚገባ ተፈጽሞአል ብለው ያምናሉ፤ አፈጻጸሙም የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ፥ የቤተክርስቲያን አመሠራረት፥ የሮም ንጉሠ ነገሥት በአይሁድ ቤተመቅደስ ሐውልቱን ለማስቀመጥ መሞከሩ፤ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ማፍረሳቸውና የአይሁዳውያን መሥዋዕት እንዲቀር ማድረጉ፤ ይህንንም የመሳሰሉ ድርጊቶች ተራቸውን ይዘው *መፈጸማቸው* ነው ያላሉ። ይህን አመለካከት የያዙ ሰዎች የመጀመሪያው ትንሣኤ (ራእ. 20፥5) *መንፈሳዊ* ትንሣኤ ነው፤ እርሱም ለእኛ ለምናምነው የሚያመለክተው እግዚአብሔር *ከክርስቶስ ጋር ሕያው እንዳደረገን ከሞትም እንዳስነሣን. . . በሰማያዊ ስፍራም ከእርሱ ጋር እንዳስቀመጠን* ነው (ኤፌ. 2፥4-6፤ 5፥14፤ ቆላ. 3፥1) ብለው ያምናሉ።

በዚህ በመጀመሪያው አመለካከት «ሁለተኛው ትንሣኤ» የአካል ትንሣኤ ሲሆን እርሱም የሚፈጸመው ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት አንድ አካላዊ ትንሣኤ ብቻ ይኖራል፤ ይህም ማለት አማኞችም ሆኑ የማያምኑ በአንድ ጊዜ ይነሣሉ፤

የሚኖረውም ፍርድ አንድ ብቻ ነው (ዳን. 12፥2፤ ማቴ. 25፥31–46፤ ዮሐ. 5፥28–29፤ ራእ. 20፥11–15)። አማኞች ክርስቶስን በአየር ላይ ሊመጣ ይገናኙታል (1ተሰ. 4፥17)፤ ይሁን እንጂ ወዲያውኑ ከእርሱ ጋር ወደ መሬት በመውረድ ሰይጣንን ከምድራዊ መንግሥቱ ላይ ፈንቅለው ይጥሉታል። እርሱና ተከታዮቹ በሙሉ በአንድ የመጨረሻ ጦርነት አብረው ይወድቃሉ (ራእ. 19፥11–21፤ 20፥7–10)። አይሁዳውያን ምድራዊ መንግሥት እንደሚኖራቸው በብሉይ ኪዳን የተነገረላቸው ትንቢት በሙሉ፤ ለክርስቲያን ቤተክርስቲያን ተዘዋውሮአል ብለው ያምናሉ (ኢዮ. 2፥28–32 ከሐዋ. 2፥14–21፤ ዘካ. 9፥9–13 ደግሞ ከማቴ. 21፥1–9፤ ሚል. 4፥1–6 ከማቴ. 11፥11–14፤ 17፥10–13፤ ሮሜ 4፥16፤ ገላ. 4፥22–31 ጋር ያገናዝቡል)። እንግዲህ እነዚህ ትንቢቶች በአሁኑ ቤተክርስቲያን በምሳሌነት ተፈጻሚዎች ሆነዋል። አለበለዚያም በራእይ ምዕራፍ 21–22 በተጻፈው ዓይነት በመጨረሻ በሚገለጡት *አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር* ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በማለት ያምናሉ።

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ያለው ሁለተኛው አመለካከት «ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣው በምድር ላይ ለረዥም ዘመን እውነተኛ ሰላምና ብልጽግና ሆኖ በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔርና ወደ ክርስቶስ በእምነት ከተመለሱ በኋላ ነው» የሚል ነው። ይህም ረዥም ዘመን አንድ ሺ ዓመት የሚያህል እርዝማኔ ላይኖረው ይችላል። ይህን ሁለተኛውን አመለካከት የያዙ ሰዎች የመጀመሪያው አመለካከት ካላቸው ጋር የሚስማሙበት ነገር አለ፤ ይኸውም «የእግዚአብሔር መንግሥት የጀመረው ክርስቶስ በመጀመሪያው በመጣ ጊዜ ነው» በሚለው አሳብ ነው። ነገር ግን እነዚህ ክርስቲያኖች የክርስቶስ መንግሥት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚገዛ ለምድር የሚታየው ቀስ በቀስ ነው በማለት ያምናሉ (ማቴ. 28፥18፤ ኤፌ. 1፥19–23)። *የመንግሥቱ ወንጌል* (ማቴ. 24፥14) በመጨረሻ ብዙ ሰዎችን ለክርስቶስ ይማርካል፤ በቤተክርስቲያን በኩልም የአንድ ሺ ዓመት (ረዘም ያለ ጊዜ) ሰላምና መንፈሳዊ በረከት ያመጣል (ኢዮ. 2፥28–32፤ የሐዋ. 2፥17–21)። «በመጨረሻ ቀኖች የምድር መንግሥታት እርስ በርሳቸው ጦርነት ማድረግን በማቆም እግዚአብሔርን ለማወቅ ብርቱ ጥረት ያደርጋሉ» የሚሉ ብዙ ትንቢቶችን ያጣቅሳሉ፤ (ኢሳ. 2፥1–4፤ ሚኪ. 4፥1–5፤ ዘካ. 8፥20–23)። እነዚህ ክርስቲያኖች ሌሎች ብዙ ትንቢቶች ክርስቶስ ከሰማይ ከመውረዱ በፊት በቤተክርስቲያን በኩል መንግሥቱን እንደሚያስተዳድር በምሳሌ ያሳያሉ ብለው ያምናሉ። (መዝ. 2፥72፤ ኢሳ. 11፥6–10፤ ሕዝ. 37፥15–28፤ ዘካ. 9፥9–10)። ይህ ሁለተኛው አመለካከት ከመጀመሪያው አመለካከት ጋር የሚስማማበት ሌላም አሳብ አለ፤ ይኸውም የክርስቶስ ተመልሶ መምጣት፥ የአካላዊ ትንሣኤና የመጨረሻው ፍርድ እነዚህ ሁሉ በራእይ ምዕራፍ 21–22 የተነገረው *አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር* ከመጀመሩ በፊት በአንድ ጊዜ ይፈጸማል የሚል ነው።

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ሦስተኛው አመለካከት፥ «የአንድ ሺው ዓመት ምድራዊ መንግሥት ከመጀመሩ በፊት ኢየሱስ ወደ ምድር ይወርዳል» የሚል ነው። በዚህ ሺ ዓመት ዘመንም አማኞች ሁሉ ከሞት ተነሥተው ከኢየሱስ ጋር አብረው ይነግሣሉ። ይህን ሦስተኛውን አመለካከት የያዙ ክርስቲያኖች፤ ነቢያት በምልክት ይናገሩ እንደነበረ ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ በምልክት የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው አጥብቀው ይናገራሉ። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ለአይሁዳውያን የተሰጡ ተስፋዎች ወደፊት በሚገለጠው የሺው ዓመት መንግሥት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በማለት አቋማቸውን ይገልጻሉ (ኢሳ. 11፥1–16፤ 65፥18–25፤ ኤር. 23፥5–8፤ ሕዝ. 37፥15–28፤ ዘካ. 14፥9–21)። በሮሜ 11፥25–29 ባለው ክፍል አይሁዳውያን በመጨረሻ ወደ ወንጌል እንደሚመለሱ ለማሳየት ጳውሎስ ወደ ብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ይጠቁማል። በተጨማሪም እነዚህ ክርስቲያኖች በትንቢት የሚነገሩ የጊዜ ክፍለ ዘመናት በሙሉ እውነተኛ ጊዜን የሚያመለክቱ ናቸው እንጂ ምሳሌያዊ ምልክቶች ብቻ አይደሉም በማለት ያምናሉ። ከራእይ ምዕራፍ 6–19 ያለው ክፍል የሚገልጠው ወደፊት ስለሚሆን ታላቅ የመከራ ጊዜ ነው፤ የሚፈጸመውም ክርስቶስ ለሺው ዓመት መንግሥት ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት ነው ብለው ይቀበላሉ (ዳን. 12፥1፤ ማር. 13፥24–27፤ ሉቃ. 21፥10–11፤25–27)። *የዳንኤል ሰባ ሰባት* (ዳን. 9፥24–27) በታሪክ ውስጥ 490 ዓመት የያዘ ነው ያላሉ። የመጀመሪያው 69 «ሰባት» (ወይም 483 ዓመት) የሚጀምረው *የመመለስ አዋጅና የኢየሩሳሌም መታደስ በተነገረበት ቀን*፤ ማለትም 445 ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ ነው[2] (ነህ. 2፥1–9)። ይህም ዘመን *የተቀባው፥ ገዥው ኢየሱስ፥ መሲሕ እስከሚመጣበት ጊዜ ይዘልቃል*። ይህ የተቀባውም ይቆረጣል (ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ተፈጽሞአል)፤ እንዲሁም ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደስዋም ይፈርሳሉ (ይህም በ70 ዓ.ም. በሮም ሠራዊት ተፈጽሞአል)። በዳንኤል ሰባኛው «ሰባት» ወይም በመጨረሻው ሰባት ዓመት ሊሆኑ የሚገባቸው ነገሮች ከክርስቶስ በኋላ እስከነበረው መቶ ዓመት ድረስ አልተፈጸሙም። ነገር ግን በመጨረሻው ሰባት ዓመት፤ በታላቁ መከራ

---

[2] ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎችም እንደሚያምኑት ከእነዚህ 483 ዓመታት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ዓመት 360 ቀናት ርዝመት እንዳለው ነው (እያንዳንዱም ወር 30 ቀናት አሉት) እንግዲህ 3 1/2 ዓመት (ወይም 42 ወራት) በዳንኤል ወይም በራእይ የተነገረው 1260 ቀናት ርዝመት ያለው ጊዜ ነው (ዳን. 7፥25፤ 12፥7–11፤ ራእ. 11፥2–3፤ 12፥6፤14)። ስለዚህ የዳንኤል 69 «ሰባቶች» ወይም 483 ዓመታት በኢየሱስ ታሪካዊ አገልግሎት ዘመንና በ30 ዓ.ም. አካባቢ በነበረው በሞቱ
ጊዜ አያልቁም።

ጊዜ ይፈጸማሉ። ይህም ማለት ክርስቶስ መንግሥቱን ለማቋቋም ከመመለሱ በፊት ቀደም ብሎ መሆኑ ነው።

ይህ ሦስተኛው አመለካከት፤ ወደ ፊት ሊመጣ ያለውን የዳንኤልን ንጉሥ ወይም ገዥ (ዳን. 7፥24–25፤ 9፥26–27፤ 11፥36) ከጳውሎስ የአመድ ሰውና (2ተሰ. 2፥1–10) ወይም በራእይ ምዕራፍ 13–19 ከተናገረለት አውሬ ወይም ሐሰተኛው ነቢይ ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ገዥ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በሰባት ዓመቱ ታላቅ መከራ አጋማሽ ላይ ያፈርሳል። ይህንንም የሚያደርገው ምስሉ እንዲመለክ (ዳን. 9፥27፤ 12፥11፤ ማር. 13፥14፤ 2ተሰ. 2፥4፤ ራእ. 13፥14–15) በአዲሱ የአይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ውስጥ በማስቀመጥ ነው (ሕዝ. 40–47)። በዚህ በታላቁ መከራ ዘመን ከአይሁዳውያን ብዙዎቹና ከዓለም ሕዝቦችም መካከል አብዛኛዎቹ እምነታቸውን በኢየሱስ ላይ ያደርጋሉ (ሮሜ 11፥25–31፤ ራእ. 7፥4፥9፥14)። ይሁን እንጂ አውሬው ላቆመው ምስል አንሰግድም በማለታቸው ብዙ ስደትና ሞት ይደርስባቸዋል (ራእ. 6፥9–11፤ 14፥3፤ 15፥2–4፤ 20፥4)። ከታላቁ መከራም በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በድል አድራጊነት ስለሚመለስ የአውሬው ሠራዊት በአርማጌዶን በሙሉ ያልቃል (ዘካ. 14፥1–9፤ ራእ. 19፥11–21)። እነዚህ ክርስቲያኖች ማቴዎስ 25፥31–46 በሕይወት ባሉት ህዝቦች ላይ የሚመጣውን ፍርድ ያስረዳል፤ ይህም የሚሆነው የአንድ ሺው ዓመት ምድራዊ መንግሥት ከመጀመሩ በፊት ነው የሚል አቋም አላቸው። እንዲሁም በራእይ 20፥1–12 የተነገሩት ሁለቱም ትንሣኤዎች እውነተኛ የአካል ትንሣኤዎች ናቸው፤ አንደኛው ሺው ዓመት ከመጀመሩ በፊት የሞቱት አማኞች ትንሣኤ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ከሺው ዓመት በኋላ የሚነሡት በክርስቶስ ሳያምኑ የሞቱት ሰዎች ናቸው፤ እነርሱም የሚነሡት የመጨረሻ ፍርዳቸውን ለመቀበል ነው። ከዚህ በኋላ አሮጌው ምድርና ሰማይ በእሳት ተቃጥሎ ይደመሰሳል፤ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም ይፈጠራል (2ጴጥ. 3፥10–13፤ ራእ. 21፥1) ብለው ያምናሉ።

ይህንን ሦስተኛ አመለካከት የያዙ፥ ጌታን በአየር ለመቀበል የአማኞች ትንሣኤ መቼ እንደሚሆን (ሰውነታቸው መቼ እንደሚለወጥ) በሚሰጡት ሃሣብ እርስ በእርስ አይስማሙም። አብዛኛዎቹ «የኢየሱስ ዳግም ምፅዓት ወደ ምድር ሁለት ጊዜ በመገለጥ ነው» ይላሉ። በመጀመሪያ አጭርና ድንገተኛ በሆነ ሁኔታ በደመና ውሰጥ ይመለሳል፤ የሚመለሰውም ታላቁ መከራ ከመጀመሩ በፊት በኢየሱስ ያመኑትን ሁሉ ከሞት ለማስነሣት ነው (1ተሰ. 4፥17)። ከዚያ በኋላ ለበጉ ሠርግ ግብዣ ወደ አየር ተመልሶ ይሄዳል (ማቴ. 24፥1–13፤ ራእ. 19፥9)። ይህ የመጀመሪያው መገለጥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ ዓይነት ሳይታሰብ በድንገት ይሆናል (ማቴ. 24፥42–51፤ 1ተሰ. 5፥1–4፤ ራእ. 3፥3)። ሁለተኛው መገለጥ ኢየሱስ ከሞት ከተነሡት አማኞች ጋር ወደ መሬት የሚመለስበት ጊዜ ነው፤ በዚህ ጊዜ አውሬውን ድል ነሥቶ መንግሥቱን በምድር ላይ ያቋቁማል። ኢየሱስ በዮሐንስ 14፥2–3 ላይ ከመንግሥተ ሰማይ ተመልሶ እኛንም ይዞን እንደሚሄድ ተስፋ ሰጥቶናል። እነዚህ ክርስቲያኖች በሚሄዱትና በሚቀሩት መካከል ድንገተኛ መለየት ይሆናል በማለት ይጠቁማሉ (ማቴ. 24፥40–41)። ጳውሎስ «እግዚአብሔር የጠራን ለቁጣ አይደለምና» ብሎአል (1ተሰ. 5፥9)፤ ኢየሱስም «ከሚመጣው ክፉ ነገር ሁሉ ለማምለጥ እንድትችሉ ጸልዩ» ሲል አስጠንቅቋል (ሉቃ. 21፥36)። እነዚህ ክርስቲያኖች «ራእይ 20፥4–6 ለአውሬው አንሰግድም በማለት ራሳቸው ተቆርጦ የሞቱትን ትንሣኤ ብቻ የሚናገር ነው ብለው ያምናሉ። ታላቁ መከራ ከመጀመሩ በፊት እውነተኞቹ ክርስቲያኖች በሙሉ ተነሥተው ወደ ሰማይ ይወጣሉ፤ ከዚህ በኋላ በራእይ 20፥4–6 ላይ ያለው ትንሣኤ በሰባቱ ዓመት የታላቁ መከራ ዘመን ያመኑትንና የሞቱትን ሰዎች ነፍሳት የሚመለከት ብቻ ነው። ያላመኑት ሰዎች የሚነሡት ግን ከመጨረሻው ፍርድ በፊት ይሆናል።

ይሁን እንጂ በዚህ ሦስተኛው አመለካከት (የሺው ዓመት መንግሥት ከመጀመሩ በፊት ኢየሱስ ይመለሳል) የሚለውን አቋም የያዙ ሌሎች ደግሞ፤ በሰባቱ ዓመት ታላቁ የመከራ ጊዜ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ መከራ ትቀበላለች ብለው ያምናሉ። በዳግም ምፅዓት ጊዜ በሕይወት የሚገኙ አማኞች ወደ ሰማይ ተነጥቀው ከክርስቶስና ከእርሱ ጋር ከሚመጡት አማኞች ጋር ይገናኛሉ ከሚለው አሳብ ጋርም ይስማማሉ። ነገር ግን ይህ የሚሆነው ከሰባቱ ዓመት ታላቁ መከራ መጨረሻ ላይ ነው ብለው ይቀበላሉ። ኢየሱስ ወዲያውኑ ሥራውን በምድር ላይ በመቀጠል አውሬውን በአርማጌዶን ላይ ድል ነሥቶ መንግሥቱን ያቋቁማል። እነርሱ እንደሚያመለክቱት የመለከቱ በድንገት መነፋትና ከሞት የተነሡ አማኞች መሰብሰብ፤ በማቴዎስ 24፥15–31 ከክፉ ስደትና መከራ በኋላ፥ ከክርስቶስ በኃይልና በክብር መመለስ ጋር ይያያዛል። ይህም የሚሆነው ከታላቅ ስደትና መከራ በኋላ ነው። በሉቃስ 17፥26–37 ባለው ትንቢት መሠረት «አንዱ በድንገት ሲነጠቅ ሌላው ወደ ኋላ ይቀራል» የሚለው ከድንገተኛው ጥፋት ጋር ተያይዟል። ኢየሱስ ሁለት ጊዜ እመለሳለሁ ብሎ በጭራሽ አላስተማረም፤ ስለሆነም የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት የአንድ ጊዜ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ይህም እንደመጀመሪያውና እንደ ሁለተኛው ዋና አመለካከት መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ከነዚህ ከሁለቱ አመለካከቶች ተለይተው ዳግም ምፅዓቱ የሚሆነው ክርስቶስ በምድር ላይ አንድ ሺ ዓመት ከመንገሡ በፊት ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ሁለት ትንሣኤዎች ብቻ እንዳሉ ይቀበላሉ፤ የመጀመሪያው በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት አማኞች ሁሉ ይነሣሉ፤ ይህም የሚሆነው ከታላቁ መከራ በኋላና የሺው ዓመት መንግሥት ከመጀመሩ በፊት ነው። በሁለተኛው ትንሳኤ ደግሞ ከመጨረሻው ፍርድ በፊት በክርስቶስ ሳያምኑ የሞቱት ሁሉ ይነሣሉ።

## ማጠቃለያ

ማንኛውንም አመለካከት የያዝን ቢሆን፥ በዚህ ጉዳይ ላይ መከራከርና መጣላት አይኖርብንም። ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድንኖር እኛን ለማስነሣት ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ሁላችንም እናምናለን። ዝርዝር ሁኔታዎቹ ለደኅንነታችን በጣም አስፈላጊዎች አይደሉም። የዳግም ምፅዓት ሐሳብ በግል ሕይወታችንና አገልግሎታችን ሊያበረታታን ይገባል፤ የእምነታችንና የምስክርነታችን መብራት ሳናጠፋ እርሱን መጠባበቅ እንዳለብን ብርቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (ማቴ. 25፥1–13)። በጠባያችን ንቁዎች መሆን እንዳለብን፤ ራስ መግዛት፤ ቅዱስና ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖረን እንደሚገባ፥ ለኑሮ በመጨነቅ ልባችንን ማከበድ እንደማይኖርብን ተነግሮናል (ሉቃ. 21፥34–36፤ 1ተሰ. 5፥4–11፤ 2ጴጥ. 3፥11–14)። ጸንተን በመቆም ማዳመጥ ይኖርብናል። በእንቅልፍ እንዳንወሰድ፥ አሳባችንን በሌሎች ላይ እንዳንጥል፥ ይልቁንም ጌታ እንድንሠራው የሰጠንን ሥራ በታማኝነት የምናገለግል ሆነን መገኘት ያስፈልገናል (ማቴ. 24፥45–51፤ 25፥14–30፤ ማር. 13፥35–37፤ 1ቆሮ. 3፥11–15፤ 15፥58፤ 2ቆሮ. 5፥10)፤ የተሰጠንም ሥራ ወንጌልን ማዳረስ (ማቴ. 24፥14፤ ማር. 13፥10)፤ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ሊሆኑ ይችላሉ (ማቴ. 25፥31–46)። በግል የምንገባው ንስሓ፥ የግል ጠባያችን መለወጥ፥ የግል ምስክርነታችን፥ የጌታን መመለስ ሊያፋጥን ይችላል (ማር. 13፥10፤ የሐዋ. 3፥19–21፤ 2ጴጥ. 3፥11–12)። የእግዚአብሔር ጸጋ . . . ራሱን በመቆጣጠር፥ በቅንነት፥ በመንፈሳዊነት በዚህ ዓለም እንድንኖር ያስተምረናል፤ በዚህ ዐይነት የተባረከውን ተስፋችንን እንጠብቃለን። ይህም የምንጠብቀው ተስፋ የታላቁ አምላካችን የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ የክብር መገለጥ ነው (ቲቶ. 2፥11–13)። «አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ቶሎ ና!» (ራእ. 22፥20)።

---

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በዳንኤል ትንቢትና በዮሐንስ ራዕይ የተጠቀሰው ማነፃፀሪያ የሦስት ዓመት ተኩል (አርባ ሁለት ወራት) ጊዜ የ1260 ቀናት ርዝመት ስላለው፥ እነዚህ 483 ዓመታት እያንዳንዳቸው 360 ቀናት ወይም በወር ሰላሳ ቀናት አሏቸው ብለው ያምናሉ።

# የቤተክርስቲያን ዓላማ

ኢየሱስ ልክ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት እነዚህን የመጨረሻ ቃላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው፤ « . . . *መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም በይሁዳ አገር ሁሉ፥ በሰማርያ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ*» (የሐዋ. 1፥8)። እኛ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች መሆን ይገባናል፤ የቤተክርስቲያን ዓላማ በዓለም ሁሉ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ሆኖ መገኘት ነው። የቤተክርስቲያን ዋና ዓላማ ይህን ማድረግ ነው፤ ሌሎቹ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉት ክንውኖች ከዚህ በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ሴቶችንና ወንዶችን ለእርሱ ለመማረክ፤ ዓለምን በቃሉና በኑሮ ምስክርነት መድረስ ማለት ነው። ለዓለም ብርሃን ሆነን መገኘት ማለት ነው። ኢየሱስም «. . . *ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት የእናንተም ብርሃን በሰው ሁሉ ፊት ይብራ!*» ብሏል (ማቴ. 5፥16)። ብርሃናችሁ ይብራ፤ ይህን የምናደርግ ከሆነ በዓለም ውስጥ የክርስቶስ አምባሳደሮች እንሆናለን። ጳውሎስም «*እኛ በክርስቶስ ስም አምባሳደሮች ነን*» ብሎ ጽፎልናል (2ቆሮ. 5፥20)። እንደ *አምባሳደሮችም* ሥራችን ወንዶችንና ሴቶችን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ማድረግ ነው።

በመጨረሻም፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር መሆን ማለት ወደ ዓለም ሁሉ መሄድና ሰዎችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ማለት ነው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ « . . . *ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩአቸው*» (ማቴ. 28፥19–20) ብሎአቸዋል።

ምስክሮች ለመሆን ምክንያት የሚሆነን ነገር ምንድን ነው? ፍቅር ነው። ሁለተኛው ታላቅ ትእዛዝ «*ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ*» (ማር. 12፥31) ይላል። እኛ አማኞች የሕይወትን እንጀራ አግኝተናል፤ ሌላውን ሰው የምንወድ ከሆነ እርሱም የሕይወት እንጀራ የት እንደሚያገኝ እናሳየዋለን።

ኢየሱስ ወደራሱ የሚጠራንና ወደ ቤተክርስቲያንም እንድንገባ የሚያደርገን ሄደን ፍሬ እንድናፈራ ነው። ኢየሱስ «*እኔ መረጥሁአችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ ሄዳችሁ ብዙ ፍሬ እንድታፈሩ ፍሬአችሁም ነዋሪ እንዲሆን ሾምሁአችሁ*» (ዮሐ. 15፥16) ሲል ተናግሮአል። በዚህ ዐውድ ፍሬ በመጀመሪያ የሚያመለክተው አዳዲስ ደቀ መዛሙርትን ነው። ኢየሱስ «*አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ*» (ዮሐ. 20፥21) ሲል ተናግሮአል፤ ኢየሱስ የተላከው ለምን ነበር? እርሱ ወደዚህ የተላከው *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም*» የሚለውን ለመፈጸም ነው (ዮሐ. 3፥16)፤ እስቲ ስለዚህ ጉዳይ አሰብ እናድርግ፤ እኛም ወደ ዓለም የምንላከው በዚሁ ምክንያት ነው፤ አብ ኢየሱስን በላከበት ዓላማ እኛም ተልከናል ማለት ነው። ዛሬም እኛ ወይም ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ሰዚህ ምድር ላይ ሲሠራ የነበረውን ሥራ ቀጥለን ለመሥራት ተሹመናል፤ ወንዶችና ሴቶች መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ ወይም የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ መንገዱን የምናሳያቸው ብርሃን ነን።

እንግዲህ የቤተክርስቲያን ዋና ዓላማ ሌሎችን መድረስ መሆኑን እናያለን። ይህም ማለት ልክ ብርሃን ወደ ጨለማ እንደሚደርስ ማለት ነው። ነገር ግን በጣም አሳዛኙ ነገር ብዙ አብያተክርስቲያናት አንዴ ከተቋቋሙ በኋላ በራሳቸው የውስጥ ጉዳይ ብቻ ይወጠራሉ። እንደ ክበብ ወይም እንደ ግል ድርጅታዊ አቋም ይሆናሉ፤ አባሎቹም ዘወትር የሚያስቡት ሊያገኙ ስለሚችሉት በረከት ነው። በቤተ ክርስቲያናቸው አማካይነት ለሌሎች ስለ ሚያስተላልፉት በረከት በጭራሽ አያስቡም። የቤተክርስቲያን ዓላማ ለክርስቲያኖች ሰላማዊ መጠጊያ ቦታ ብቻ እንድትሆን አልነበረም፤ ነገር ግን ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ ምስክሮችን ማለትም፥ አምባሳደሮችን፥ ፍሬ አፍሪዎችን፥ ደቀ መዛሙርት አድራጊዎችንና ሚሲዮናውያን አዘጋጅታ እንድትልክ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ በቤተክርስቲያን የምትመሰክር ሚሲዮናዊ ቤተክርስቲያን ነች። በአውሮፓ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው እንዴት ነበር? ጳውሎስ የሚባል አንድ ግለሰብ በመቄዶኒያ (ግሪክ) ወደምትገኝ ፊልጵስዩስ ወደተባለች አንዲት ከተማ ስለሄደና በዚያም ቤተ ክርስቲያን ስላቋቋመ ነው (የሐዋ. 16፥9–

15፤40)። በሕንድ አገርስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተጀመረ? ክርስቲያኖች ወደ ሕንድ አገር ሄደው ወንጌልን ስለሰበኩ ነው። ብዙዎቹ እንደሚሉት ወደ ሕንድ አገር የሄደው የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ሐዋርያው ቶማስ ነው። በቻይናስ ቤተክርስቲያን እንዴት ተጀመረ? በኮሪያስ? በአፍሪካስ? በነዚህ ሁሉ አገሮች ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በተመሳሳይ ምክንያት ነው፤ ምስክሮች ወደነዚህ ቦታዎች ሄዱ፤ ወንጌልንም ሰበኩ።

በእርግጥ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ወደ ሩቅ ቦታ ሄዶ ወንጌል መስበክ አለበት ማለት አይደለም። እንዲያውም ይህን ለማድረግ የተጠሩት ጥቂቶች ናቸው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ክርስቲያን በሚኖርበት አካባቢና በሥራውም ቦታ ለሚያገኙት ሁሉ ምስክር መሆን ይጠበቅበታል (የሐዋ. 1፡8)። እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ማሰብ ያለበት ነገር የቤተክርስቲያን ዋና ዓላማ ምስክር ሆኖ መገኘት መሆኑን ነው፤ ምስክር የሚሆነውም በአካባቢው ብቻ ሳይሆን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ነው።

ቤተክርስቲያን እንደ አካል ነች (1ቆሮ. 12፥27)። የልብ ዋና ተግባር ደምን ማሠራጨት ነው፥ የሳምባም ዋና ሥራ መተንፈስ ነው፥ የጆሮም ዋና ሥራ መስማት ነው፥ የእግርም ዋና ሥራ መራመድ ነው፤ ነገር ግን የእያንዳንዱ (ብልት) አጠቃላይ ተግባር አካል እንዲኖርና እንዲሠራ መርዳት ነው። የእያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባልም ሥራው እንደዚህ መሆን ይገባዋል።

የትኛዋም ቤተክርስቲያን የማትመሰክር፥ በወንጌል ሌሎችን የማትደርስ ብትሆን በመሞት ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን ነች። በእርግጥም የአንዲት ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ጤንነት የሚለካው ልትማርክ በምትችላቸው ክርስቲያኖች ብዛት ሳይሆን፥ በምትልካቸው ወንጌላውያን ወይም ምስክሮች ብዛት ነው።

አንዳንድ ሰዎች፤ የወንጌል ስርጭት እንደ ሌሎች አገልግሎቶች ሁሉ በእኩል ደረጃ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ከሆኑ ሥራዎች አንዱ ነው ይላሉ። እንደ እነርሱም አባባል ቤተክርስቲያን አራት እግሮች እንዳለው መቀመጫ ናት። እነዚህ አራት ነገሮች አምልኮ፥ ክርስቲያናዊ ኅብረት፥ ማስተማርና ወንጌላውያንን ማስራጨረት ናቸው። ነገር ግን የዚህ ዐይነቱ አሠራር ስለእንዲት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አሠራር በቂ ያልሆነ አመለካከት ነው። የወንጌል ስርጭት አገልግሎት በመቀመጫው ከፍታ ላይ ተቀምጦ የሚያበራ መብራት ነው። ስለዚህም መቀመጫው ሦስት እግሮች ብቻ ያሉት ሲሆን እነርሱም አምልኮ፥ የክርስቲያን ኅብረትና ማስተማር የተሰኙት ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ፤ ወደ መጨረሻው ለመድረስ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች እንጂ በራሳቸው የሥራ ፍጻሜ ናቸው ማለት አይደለም። በሌላ አነጋገር መቀመጫውን በመደገፍ፤ ቤተክርስቲያን ወንጌልን የምታሰራጭበትን መንገድ የሚረዱ ዘዴዎች ናቸው።

ስለዚህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዋና ዓላማ ወንጌል ማሰራጨት (ምስክርነት፥ የወንጌል ሥራ) እንደሆነ፥አንደገና ማሳሰብ አለብን። በሌላ አነጋገር ወንጌልን ማሰራጨት ከቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች አንዱ ነው ማለት አንችልም፤ ይልቁንም ሁሉንም አጠቃሎ የያዘ የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ነው።

ይህንን እውነት በአእምሮአችን ስንይዝ የቤተክርስቲያንና የእያንዳንዱ አማኝ አገልግሎት ተገቢ ሚዛን ሊይዝ ይችላል። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች የምናተኩረው በሁለተኛ ደረጃ ጉዳዮች ላይ በመሆኑ አጠቃላይ እቅዳችንንና ዓላማችንን እንስታለን። በሁለተኛ ደረጃ ያሉት ነገሮች (ስለ ማኅበራዊ ፍትሕ፥ አካባቢን ስለመጠበቅ፥ ስለ መልካም ጤንነት፥ ስለ መልካም ትምህርት፥ ስለ ኢኮኖሚያዊ መሻሻል ስለ መሳሰሉትም) ማሰብ በጣም ጥሩና ልንሳተፍበትም የተገባ ነው፤ በእርግጥም ክርስቲያኖች በእነዚህ ጉዳዮች ተካፋይ ሊሆኑ ይገባቸዋል፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ጉዳዮች ወንዶችንና ሴቶችን ወደ ክርስቶስ እንደመጥራት ወይም ወደ ደኅንነት እንዲመጡ ማድረግ ከመሰለው ዋና ጉዳይ ጋር ሲመዛዘኑ በሁለተኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው። አንድን ግለሰብ በዚህች ምድር ላይ ለጥቂት ዓመታት የተሻሻለ ሕይወት እንዲኖረው ሞራል መስጠት፥ ያንኑ ግለሰብ በመንግሥተ ሰማይ የዘላለም ሕይወት እንዲኖር ከመምራት ጋር ሲወዳደር በጣም ትንሽ ነው። እኛ ሁል ጊዜ ዐይናችንን በአገልግሎታችን ዋና ግብ ላይ ማድረግ ይኖርብናል። ይህም ዋና ግብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ማድረግና ወደ መንግሥቱም እንዲገቡ ማስቻል ነው (2ቆሮ. 5፥18–20 ያለውን ክፍልና ማብራሪያውን ይመለከቷል)

ኢየሱስም ዐይኖቹን በግቡ ላይ ያደርግ ነበር። ሰብኳል፥ አስተምሯል፥ ፈውሷል፥ እንዲሁም ብዙ ተዓምራትን ፈጽሟል፤ ነገር ግን የእነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ግብ አንድ ነበር፤ ይህም ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ነው። ፈውሶቹና ሌሎችም የተአምራት ሥራዎቹ በራሳቸው ፍፃሜ ናቸው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሰዎች ቃሉን ይሰሙት ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። እርሱ ተአምራት ሠሪ ተብሎ ለመታወቅ ፍላጎት አልነበረውም፤ እንዲያውም ከፈወሳቸው ሰዎች አብዛኛዎቹ ለማንም እንዳይናገሩ ይነግራቸው ነበር። ሰዎች ዐይናቸውን ከመንፈሳዊ ችግራቸው ላይ አንስተው ወደ ሌላ እንዲያደርጉ አይፈልግም። ሰዎች ወደ መንደራቸው አስገብተው ሊያቆዩትና እንዲፈወሳቸው ለማድረግ በሚፈልጉ ጊዜ ፈቃደኛ አልሆነም። ይልቁንም «*እኔ የተላክሁት ለዚህ ስለሆነ ወደ ሌሎችም ከተሞች ሄጄ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል ማብሠር ይገባኛል*» ይላቸው ነበር (ሉቃ. 4፥43)። የኢየሱስ ዋና ሥራ ወንዶችና ሴቶችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማምጣት ነበር። እንግዲህ የእርሱ ዋና ሥራ ይህ ከሆነ፥ የእኛም ሥራ በግለሰብ ደረጃም ቢሆን በቤተክርስቲያን ደረጃ ይኸው መሆን አለበት።

ስለ ቤተክርስቲያን ዓላማ ወይም ተልዕኮ ሊባል የሚገባ አንድ የመጨረሻ ነገር አለ፤ ያ ተልዕኮ ከተፈጸመ በኋላ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል፤ የዓለምም ፍጻሜ ይሆናል። ኢየሱስ «*ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር*

*እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል፣ በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል»* ብሎአል (ማቴ. 24፥14)።

እኛ ወንጌልን ለእያንዳንዱ ጎሣና በባሕል ለተጣመረ ብሔረሰብ እስከናደርስ ድረስ ኢየሱስ እየጠበቀን ነው፤ በዓለም ላይ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ በባሕል የተጣመሩ ብሔረሰቦች አሉ።

በማቴዎስ 24፥14 እና 28፥19 እነዚህ በባህል የተጣመሩ ብሔረሰቦች «ሕዝቦች[1]» ተብለው ይጠራሉ። የእነዚህ ብሔረሰቦች ብዛት 10,000[2] ያህል እንደሚሆን ይገመታል፤ በመካከላቸው የራሳቸው ተወላጅ የሆነ ቋሚ የወንጌል ምስክር የላቸውም። የእያንዳንዱ ክርስቲያን ዋና ተግባር ለእነዚህ እስከ አሁን ወንጌል ላልደረሳቸው የክርስቶስ ወንጌል እንዲደርሳቸው መርዳት ነው። በተጨማሪም የምትመሰክርና ራሷን የምትተካ ቤተክርስቲያን በእያንዳንዱ ጎብረተሰብ መካከል እንድትቋቋም ማድረግ ነው። ይህን የመሰለ ሥራ እስኪከናወን ድረስ የቤተክርስቲያን ዓላማ ፍጻሜውን ሊያገኝና ክርስቶስም ተመልሶ ሊመጣ አይችልም።

ሥራው ምን ያህል ትልቅ ነው? የዓለም ሕዝብ ብዛት እድገት እየጨመረ በመሄዱ በታሪክ ውስጥ ከምንጊዜውም ይልቅ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የበዙት ዛሬ ነው። በሌላ አቅጣጫ ይህን ከባድ ሥራ መስራት የሚችሉ እጅግ ብዙ ክርስቲያኖችም ያሉት በአሁኑ ጊዜ ነው። ሥራው ሊሠራ ይችላል፤ በ100 ዓ.ም. ክርስቲያን ላልሆኑ 360 ለሚሆኑ ሰዎች ሊመሰክር የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበር። በ1950 ዓ.ም. ደግሞ 20 ለሚሆኑ ሰዎች የሚመሰክር አንድ ሰው ብቻ ነበር፤ ዛሬ ግን 7 ለሚሆኑ ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች የሚመሰክር አንድ ሰው ማግኘት ይቻላል። በ2000 ዓ.ም. የሚመሰክር ክርስቲያን፥ ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር ሊመዛዘን አንድ ለአራት ሆኖ ይገኛል፤ ማለትም አንድ የሚመሰክር ክርስቲያን አራት ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች ይመሰክራል ማለት ነው። በእርግጥ ሥራው ሊሠራ ይችላል!

በአሁኑ ጊዜ ወንጌልን ውጤት በሚያስገኝ መልኩ ለመስማት ዕድል ያላገኙ 2 ቢሊዮን የሚጠጉ ሰዎች አሉ። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዓላማ ወደ እነዚህ ሰዎች መድረስ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ሌሎችን ወንጌላውያን አድርጎ ለመላክ ተጠርተዋል፤ ይህም ማለት ለእነርሱ በመጸለይ፥ እነርሱን በመርዳትና በማደፋፈር ረገድ ማለት ነው። ሌሎቹ ደግሞ ራሳቸው እንዲሄዱ ተጠርተዋል። እግዚአብሔር የሚልኩትንም ሆነ የሚላኩትንም ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አንዱ ወደ ውጪ ለመሄድ የተዘጋጀ ቢሆንና ሌላው ደግሞ ቤት የሚቀር ቢሆንም እያንዳንዱ ክርስቲያን ምስክር መሆን ይገባዋል። ኢየሱስ እያንዳንዳችን እርሱን ለማገልገል በተጠራንበት ተመሳሳይ ተግባርና መሥዋዕትነት እንድናሳይ ይፈልግብናል።

---

[1] በማቴዎስ 28፥19 «ሕዝቦች» የሚለው የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው በፖለቲካ ካርታ የተለያዩ አገሮችን ሳይሆን አንድ ዓይነት ቋንቋና ባህል ያላቸውን ብሔር ብሔረሰቦችን ነው።

[2] ይህ ቁጥር በአሁኑ ወቅት በክርክር ላይ ነው፤ ቁጥሩ ሰዎች ስብሔር ብሔረሰቦች በሚሰጡት ትርጓሜና እነዚህንም እንዴት እንደሚከፋፈሉአቸው ባላቸው ግንዛቤ ላይ ተመሥርቶ ሊለያይ ይችላል።

# መነቃቃት

ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ ወደክርስቶስ ሲመጡ በታላቅ ደስታ፥ በነፃነትና በፍቅር ይሞላሉ፤ ወደ ኢየሱስም በጣም የቀረቡ ይመስላቸዋል፤ ልባቸውም እርሱን በማገልገል ምኞት ይቀጣጠላል። ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ያ የመጀመሪያ ከፍተኛ ፍላጎታቸው ቀስ በቀስ እየቀነሰ ይሄዳል፤ ብዙውን ጊዜም ጨርሶ ይጠፋል። ለምን? በምንስ ምክንያት ይህ ሊሆን ቻለ? ያንን በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ ስንመጣ የነበረንን ሁኔታ እንዴት መልሰን ለማምጣት እንችላለን?

መቼም በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ለክርስቶስ ያለንን ቅንአትና ፍቅር እያደር ከማጣት የበለጠ ችግር የለም። ኢየሱስ እነዚህን አስፈሪ የሆኑ ቃላት ለጥንታዊቱ የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ጽፎአል «*ነገር ግን አንድ የምንቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል፤ ከመውደቅህ በፊት የት እንደነበርህ አስታውስ፤ ንስሓም ግባ በመጀመሪያ ታደርገው የነበረውን ሥራህን አድርግ ይህን ሁሉ ባታደርግ ግን ወደ አንተ እመጣለሁ፤ ንስሓም ካልገባህ መቅረዝህን ከስፍራው አነሣዋለሁ*»(ራእ. 2፥4-5)።

አንድ ሰው የሰይጣንን የጨለማ መንግሥት ትቶ እምነቱን በክርስቶስ ላይ በማድረግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በሚገባበት ጊዜ ሰይጣን አጥብቆ ይቆጣል። ስለዚህም አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ሰይጣን ባገኘው መሣሪያ ሁሉ ሊያጠቃው ይፈልጋል፤ የሰይጣን ዋና ግብ አማኙ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ከእርሱ ለመንጠቅ ጥረት ማድረግ ነው። ሰይጣን አንድ እውነተኛ አማኝ የሆነን ሰው ከኢየሱስ እጅ ነጥቆ ለመውሰድ እንደማይችል ያውቃል (ዮሐ. 10፥28)። ይሁን እንጂ ያን ክርስቲያን የማይረባ (የማይሠራ)፥ ፍቅሩና ሕይወቱ የቀነሰ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል። ይህንንም በማድረግ ብዙ ጊዜ ሊሳካለት ይችላል።

ስለዚህ በክርስትና ሕይወታችን፥ ዘወትር በመንፈስ የተነቃቃን መሆን ያስፈልገናል። በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን አብያተክርስቲያናትም መነቃቃት ያስፈልጋቸዋል። በማያቋርጥ ደረጃ ራሳችንን እየመረመርን መኖርም ይገባናል። በዓለም ላይ ከሚገኙት ከሌሎች ነገሮች ሁሉ ይልቅ ኢየሱስን እንወደዋለን? (ማር. 12፥30)። ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔርን መንግሥት እናስቀድማለን? (ማቴ. 6፥33)። ከእያንዳንዱ ክርስቲያን ወንድም ወይም ከእያንዳንዱ ክርስቲያን እህት ጋር ፍጹም የሆነ ፍቅርና ኅብረት አለን? (1ዮሐ. 1፥7፤ 4፥20)። የመንፈስ ቅዱስንስን ፍሬ በየቀኑ በሕይወታችን እንለማመዳለን? (ገላ. 5፥22-23)። በሕይወታችንስ መንፈሳዊ ኃይል ይገኛልን? ይኸው ኃይል በቤተክርስቲያናችንስ ይሠራልን? (ሉቃ. 24፥49፤ የሐዋ. 1፥8)። ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ አይደለም የሚል ከሆነ መነቃቃት ያስፈልገናል ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል ከምናጠናበት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው መታደስንና መነቃቃትን ለመለማመድ ነው። ይህ የማብራሪያ መጽሐፍ ከተጻፈበት ምክንያቶች ዋነኛውም ይኸው ነው። ይህንን የማብራሪያ መጽሐፍ በምታጠኑ ጊዜ ፀሎታችሁ የእግዚአብሔር ቃል በአዲስ ትርጉምና ኃይል በልባችሁ ይዘራ ዘንድ ይሁን። ይህን ማብራሪያ በምታጠኑበትና በምትጠቀሙበት ወቅት መነቃቃት በልባቸሁና በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዲፈጠር ጸልዩ።

እስቲ አሁን ስለመነቃቃት እንመልከት። በመጀመሪያ መነቃቃት ማለት ምን ማለት ነው? መነቃቃት ማለት ለክርስቶስ የነበረንን የቀድሞ ፍቅር ማደስ ማለት ነው። መነቃቃት ማለት ከኢየሱስ ጋር በብርሃን የምንመላለስበትና ኢየሱስ የራሱን ሕይወት በእኛ ውስጥ እንዲኖር የምንፈቅድበት፥ እንዲሁም ለብዙ ጊዜ አሽቆልቁለን ከኖርን በኋላ ወደ መንፈሳዊ ጤንነት የምንመለስበት ነው። መነቃቃት ማለት ኃጢአተኛነታችን ገብቶን ይቅርታ እንዲያደርግልንና እንዲያነፃን ወደ ኢየሱስ ድምፃችንን ከፍ አድርገን መጮኽና ኢየሱስ ሁለንተናችንን እንዲቆጣጠር መፍቀድ ማለት ነው።

መነቃቃት ማለት ሕይወታችን ተለውጦ በጥልቀት የሚንቀሳቀስበት ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ በስሜት ተንቀሳቅሶ ወደ ዕብደት መሄድ መንፈሳዊ መነቃቃት ሊባል አይችልም። መነቃቃት ማለት የጸሎት፥ የጥሞናና በጨዋነት ራስን በመመርመር ወደ ኢየሱስ ቅርብ የምንሆንበት ግብዝነታችንንና ራሳችንን ስናታልል የኖርንበትን ሁኔታ ሁሉ ገልጠን የምናሳይበት ጊዜ ነው። መነቃቃት ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ጠብን፥ ትችትንና መራራነትን ገልጠን በማሳየት ንስሓ መግባት ነው።

መነቃቃት ማለት የሕይወታችን መለወጥ ሌሎችን እጅግ አስገርሞአቸው ወደ ክርስቶስ ተስበው የሚመጡበት ጊዜ ነው። ከሁሉም በላይ መነቃቃት ማለት መንፈስ ቅዱስ በኃይል ወደ እኛ በመምጣት በግል ሕይወታችንና እንዲሁም በቤተክርስቲያንም ውስጥ ሲሠራ ነው።

መነቃቃት የሚጀምረው እንዴት ነው? መነቃቃት ሁሉም ቦታ ላይ የሚጀምረው ኃጢአተኛነታችንን ተገንዝበን በምንናዘዝበት ጊዜ ብቻ ነው። መነቃቃት ያስፈለገበት የመጀምሪያው ምክንያት ኃጢአት በመኖሩ ነው። ዲያብሎስ እኛን ለማጥቃት የሚጠቀምበት ዋና ዘዴ ኃጢአት እንድንሠራ በመፈተን ነው። ኃጢአት ስንሠራ ከእግዚአብሔር እንለያለን፤ በውስጣችን የሚኖረውንም የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ እናሳዝናለን፤ ከኢየሱስ ጋር ያለንን ኅብረት እናጣለን፤ ደስታችንን፥ ሰላማችንን፥ ኃይላችንን እናጣለን፤ እንግዲህ በእኛ መካከል ኃጢአት ባይኖር ኖሮ መነቃቃትም ባላስፈለገንም ነበር። ስለዚህ መነቃቃት የሚጀምረው ኃጢአት መኖሩን አውቀን ንስሓ ለመግባት በምንዘጋጅበት ጊዜ ነው።

እኛ ራሳችንን ኃጢአተኞች እንደሆንን አድርገን ማሰብ አይሆንልንም። ኃጢአታችንን በጣም አሳንሰን ነው የምንመለከተው፤ እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ኃጢአት እንዳለብን አናስተውልም። እኛ «እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ትእዛዛትን ሁሉ ጠብቄአለሁ» በማለት ለኢየሱስ የተናገረውን ሀብታሙን ወጣት እንመስላለን (ማር. 10፥17–21)። እርሱ ምንም ኃጢአት እንደ ሌለበት ነበር በእርግጠኛነት የተናገረው።

ነገር ግን እኛ ኃጢአቶቻችንን ልብ ባንላቸውም እግዚአብሔር ግን በእርግጥ ያያል። ኃጢአት ማለት ትእዛዛትን ማፍረስ ብቻ አይደለም፤ በሕይወታችን ያለ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይስማማ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው። ይህም ማለት የስሕተት አቅጣጫ የያዙ ዝንባሌዎችን ሁሉ ያጠቃልላል ለምሳሌ ራስን መውደድ፥ ኩራት፥ ምቀኝነት፥ ቅንአት፥ ቂም፥ ጭንቀት፥ እምነተቢስነት ከኃጢአት ይቆጠራሉ። ኃጢአት ስሕተት የሆነውን ነገር ማድረግ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ትክክል የሆነውንም ነገር አለማድረግ ኃጢአት ነው (ያዕ. 4፥17)። እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፥ በሙሉ አሳባችን፥ በሙሉ ኃይላችን አለ መውደድና (ማር. 12፥30)፤ ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ አለመውደድም ኃጢአት ነው (ማር. 12፥31)። እስከ መጨረሻው ድረስ በእምነት ጸንቶ አለመቆየትም ኃጢአት ነው (ማር. 13፥13)። መልካም አጋጣሚ እያለን ወንጌልን ሳናደርስ ብንተውም ኃጢአት ነው (1ጴጥ. 3፥15)። በችግር ላይ የሚገኘውን ወንድማችንን ሳንረዳው ብንቀርም ኃጢአት ነው (ማቴ. 25፥41–45)። ከእኛ መካከል ኃጢአት የለብኝም ለማለት ከቶ ማን ይችላል? (1ዮሐ. 1፥8)።

ስለሆነም የመነቃቃት የመጀመሪያው ደረጃ ኃጢአታችንን መናዘዝ ነው። ኢየሱስ እኛን ከኃጢአት ለማንጻት ምንያህል ዋጋ እንደከፈለ እናስታውስ። መንፈስ ቅዱስንም የተደበቀ ኃጢአታችንን ገልጦ እንዲያሳየን እንለምነው። ከዚህ በታች ራሳችንን መጠየቅ እንድንችል የጥያቄ ዝርዝሮች እንደ ምሳሌ ተሰጥተውናል፤ በእነዚህም ጥያቄዎች በኢየሱስ ጌትነት ሥር ያልሆኑ የሕይወታችን ክፍሎች መመርመር እንችላለን።

በሕይወቴ ከእግዚአብሔር ይልቅ አብልጬ የምወደው ነገር ይኖራልን? ምንአልባት ቤተሰቤን፥ ሥራዬን፥ ደስታዬን፥ ራሴን አብልጬ እወድ ይሆንን? (ማቴ. 6፥33፤ ማር. 12፥30)።

በሕይወቴ በተፈጠረ በማንኛውም ሁኔታ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ተበሳጭቼ ወይም አጉረምርሜ አውቃለሁን? (1ቆሮ. 10፥10፤ ፊል. 2፥14፤ 1ተሰ. 5፥18)።

ከሌሎች ሰዎች የማገኘውን ምስጋና እወዳለሁን? ለማደርገው መልካም ነገር ሌሎች ሰዎች ጎሽ እንዲሉኝ እመኛለሁን? የሰዎችን አክብሮት ወይም ታይታን በመውደድ የማደርገው ነገር አለን? (ማቴ. 6፥1–5፤ ዮሐ. 12፥43)።

ከሌሎች ጋር ባለኝ ግንኙነት ብስጩነት ይታይብኛልን? በሌሎች ላይ ስሕተት ፈላጊ ነኝን? በእኔ ላይ ስሕተት በሚፈልጉት ላይ ብስጩ ወይም አትንኩኝ ባይነት የሚታይብኝ ነኝን? በሰው ላይ ቂም ለመያዝ የሚቸኩል መንፈስ አለኝን? በእኔስ ውስጥ መራራነት ይታይብኛልን? (ዕብ. 12፥15)።

እልኸኛና የማልበገር ነኝን? ጠብና ክርክርን የምወድ ነኝን? ሁልጊዜ ትክክለኛ የሆንኩ ይመስለኛልን? ኃይለኛና አሽሙረኛስ ነኝን? (ፊል. 2፥3፤ ኤፌ. 5፥21)። ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን በማለት እፈራለሁን? ሥራ እንዳልሠራ ራሴን አገልላለሁን? እግዚአብሔር የሰጠኝን ችሎታ ደብቄ እይዛለሁን? (ማቴ. 25፥24–28)።

በሰው ላይ እቀናለሁን? አንድ ሰው በሚወድቅበት ጊዜ በውስጤ በስውር ደስ ይለኛልን? አንድ ሰው የኑሮ መሰላካት ሲገጥመው በውስጤ በስውር ሐዘንተኛ እሆናለሁን? (1ቆሮ. 13፥4–6)።

በሕይወቴ ፍጹም የሆነ ታማኝነት ያላሳየሁበት ነገር ይኖራልን? በውስጤ ደብቄ የያዝሁት እውነት ይኖራልን? ስሕተቴንስ ሸፋፍኜ ለመያዝ እሞክራለሁን? ከእውነተኛው ማንነቴ የተሻለ ግምት ለራሴ ለመስጠት እሞክራለሁን? ስለ አንድ ነገር ሲነገር አጋንናለሁን? (ማቴ. 23፥27–28፤ ያዕ. 5፥16)።

ተስፋ መቁረጥ ወይም ሐዘን ይታይብኛልን? በእግዚአብሔር ላይ የነበረኝን ፍጹም እምነት አቋርጫለሁን? እምነቴ ደካማ ሆኖአልን? (ሮሜ 1፥17፤ 14፥23፤ ዕብ. 11፥6)። በመንፈሳዊ ሕይወቴ ደረቅና ወግ ጠባቂ ብቻ ሆኛለሁን? ክርስቶስን ለማያውቁ ሰዎች አጥብቄ ማሰብ ትቻለሁን? በመንፈሳዊ ሕይወቴ

ደካማ ሆኜአለሁን? ለብ ያለ ሕይወት አለኝን? ከደቀመዝሙር ሕይወት ወደ ኋላ አፈግፍጊያለሁን? (ማር. 8፡34፣ ራእ. 2፡4–5፣ 3፡15–16)።

የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ ተከትዬአለሁን? የማያምኑ ሰዎች እንደሚያስቡት ማሰብ ጀምሬአለሁን? ዓለምንና በውስጧ ያለውን ደስታ መውደድ ጀምሬአለሁን? (ሮሜ 12፡2፣ 1ዮሐ. 2፡15–17)።

ከነዚህ ጥያቄዎች ለአንዱ እንኳ የምንሰጠው መልስ አዎ ከሆነ ያንን ኃጢአት እንዳደረግን እርግጠኞች ሆነን ለእግዚአብሔር መናዘዝ አለብን። እንደዚህ የምናደርግ ከሆነም እግዚአብሔር እንዲያነቃቃን መንገድ እንሰጠዋለን ወይም በሩን እንከፍትለታለን፣ ይህንን የማናደርግ ከሆነ ግን ባለ ማቋረጥ ደካሞች እንሆናለን፣ ከእግዚአብሔርም እየራቅን እንሄዳለን።

*የመነቃቃት* ሁለተኛው ደረጃ መንፈስ ቅዱስ የገለጠልንን ኃጢአት በሙሉ ለእግዚአብሔር መናዘዝ ነው። ንስሐ መግባት ማለት ስለ ኃጢአቶቻችን በጣም ማዘን፣ ከእነርሱም ጨርሶ *መመለስ* ነው። ይህን በምናደርግበት ጊዜ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፣ ደግሞም ያነጻናል (1ዮሐ. 1፡9)፣ ይህን ይቅርታና ንጽሕና የማናገኝ ከሆነ ግን ምክንያቱ አንድ ብቻ ነው፣ ይኸውም ከኃጢአታችን ፊታችንን *ሙሉ* በሙሉ አልመለስንም ማለት ነው።

*የመነቃቃት* ሦስተኛው ደረጃ በሌሎች ሰዎች ላይ የፈጸምነው ስሕተት ነገር ካለ፣ ማስተካከል ይኖርብናል (ማቴ. 5፡23–24፣ ሉቃ. 19፡8)። በበደልነው ኃጢአት አንድን ሰው ይቅርታ መጠየቅ ይኖርብን ይሆናል፣ የአንድን ሰው ዕቃ ያለፈቃዱ ወስደን ከሆነ ያንን ዕቃ መመለስ ይኖርብን ይሆናል፣ የሰውን ስም አጥፍተን ከሆነ ይቅርታ ጠይቀን ስሙ እንዲታደስ መጣር ይኖርብናል፣ ከሁሉም በላይ መራራነትን ወይም ቂመኛነትን በሰው ላይ መያዝ ታላቅ ኃጢአት ስለሆነ ያንን ሰው ይቅርታ መጠየቅ ይኖርብን ይሆናል (ማቴ. 6፡12፣ 14–15)።

*የመነቃቃት* አራተኛው ደረጃ «በድጋሚ ሕይወታችንን ለክርስቶስ ማስገዛት» ነው። የሕይወታችን ሁለንተና ለክርስቶስ ማስገዛት ይኖርብናል፣ ከእርሱ የምንደብቀው ምንም ነገር መኖር የለበትም። የሚያገዘንን ነገር ሁሉ ለመፈጸም ራሳችንን የሰጠን መሆን ይገባናል (ዮሐ. 14፡15)። በአጠቃላይ እኛ የራሳችን አይደለንም፣ ሕይወታችን በሙሉ የእርሱ ነው (1ቆሮ. 6፡19–20)።

*የመነቃቃት* አምስተኛው ደረጃ፣ እግዚአብሔር ለትሑቶችና ንስሐ የገባ ልባቸውን ፈጽመው ወደ እርሱ ላዞሩ ሰዎች ሊሰጣቸው ቃል የገባላቸውን ነገር ለእኛም እንዲሰጠን መጠየቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሙላት እንዲኖርበት ልባችንን ከፍተን መስጠት ይኖርብናል፣ በመንፈሱ እንድንሞላ እግዚአብሔር አዝዞናል (ኤፌ. 5፡18)። ዘወትር *ለመሞላት መመኘት* ይኖርብናል (ሮሜ 12፡1)፣ ለመሞላትም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይኖርብናል (ማቴ. 7፡7–8፣ 11፣ ሉቃ. 11፡13)።

*የመነቃቃት* ስድስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ መኖር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አይችልም። ስለዚህም ጳውሎስ *«በመንፈስ ኑሩ፡ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ»* ብሎ ጽፎልናል (ገላ 5፡16)። ክርስቶስን በመምሰል ለመኖርና መንፈሳዊ ድል ለማግኘት ዋናው ቁልፍ ይህ ነው። ድልን በሚነናጸፍ ሕይወት መኖር ማለት ክርስቶስ ራሱ በእኛ ውስጥ እንዲኖር መፍቀድ ማለት ነው (ገላ. 2፡20)። እንግዲህ ግባችን ክርስቶስን ለመምሰል ውሳኔ ማድረግ ነው (ሮሜ 8፡29)። ከዚህ የላቀ ከፍ ያለ ግብ የለንም።

ለመነቃቃት ስንዘጋጅ ልንወስዳቸው የሚገቡ ደረጃዎች እነዚህ ናቸው። ማስታወስ የሚገባን ሌላው ጉዳይ *የመነቃቃቱን* ሥራ በሙሉ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ነው። ሥራውንም የሚሠራው በራሱ መንገድና በራሱ ጊዜ ነው። እኛ ልናደርገው የሚገባንን ሁሉ ካደረግን በኋላ በመጠባበቅ *መመልከት* የሚገባን እርሱን ነው።

*«ሕዝቤ ከሚያደርጉት ክፉ ነገር በመራቅ ተጸጽተውና ንስሐ ገብተው ወደ እኔ ቢጸልዩ በሰማይ ሆኜ እሰማቸዋለሁ፡ ኃጢአታቸውንም ይቅር እልላቸዋለሁ፣ ምድራቸውም እንደገና የበለጸገች እንድትሆን አደርጋለሁ»* (2ዜና. 7፡14)።

እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ አነቃቃን!

# የብሉይ ኪዳን እጥርጥር

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አንባቢዎቻቸው መጠነኛ የሆነ የብሉይ ኪዳን ዕውቀት ይኖራቸዋል በማለት ገምተዋል። አብዛኛውን ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ጽሑፎችና በዚያው ስፍራ ከተመዘገቡት የአይሁድ ሕዝብ ታሪክ ያጠቅሳሉ (የሐዋ. 7 እና ዕብ. 11 ይመለከቷል)። ይህ ጽሑፍ በተለይ በአዲስ ኪዳን በተጠቀሱት አንዳንድ ክንዋኔዎችና ግለሰቦች ላይ አጽንኦት በማድረግ የብሉይ ኪዳንን እጥርጥር በመጠኑ ያቀርባል። ከእነዚህ ክንዋኔዎችና ግለሰቦች ጋር የሚገናኙትንም የአዲስ ኪዳን ማጠቃሻዎች ያቀርባል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስም ዝርዝር ሰርዝ ተደርጎባቸው ተጽፈዋል።

*በመጀመሪያው ኦሪት ዘፍጥረት* መጽሐፍ ቀድሟል። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ (ዘፍ. 1፥1–25፤ ዮሐ. 1፥1–3)። እግዚአብሔር ዓለማትን በስድስት ቀን ፈጠረ፣ በስድስተኛውም ቀን የመጀመሪያውን ወንድና የመጀመሪያዋን ሴት ማለትም አዳምንና ሔዋንን ፈጠረ (ዘፍ. 1፥26–31)። በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሥራው ዐረፈ። ይህም የሰንበት ዕረፍት መጀመሪያው ነው፡በኋላም እግዚአብሔር የሰው ልጆች እንዲያከብሩት ትእዛዝ ሰጠ (ዘፍ. 2፥1–3፤ ዕብ. 4፥1–11)።

አዳምና ሔዋን በዔደን ገነት ውስጥ አንድ ትዕዛዝ ብቻ ተሰጥቷቸው እንዲቀመጡ ተደርገው ነበር። መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ ምንም ፍሬ እንዳይበሉ ታዘዙ። ነገር ግን ሰይጣን በእባብ ተመስሎ ሔዋንን አታለላት፤ የተከለከሉትንም ፍሬ እንድትበላ ፈተናት፤ እርስዋ በላች። ከዚያም በኋላ አዳም በላ። በዚህ ዐይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ኃጢአትና ሞት ወደ ዓለም ገቡ (ዘፍ. 3፥1–19፤ ሮሜ 5፥12–19)። ይህም «የሰው ውድቀት» ተብሎ ተጠራ። ከዚህ በኋላ የአዳምና የሔዋን መጀመሪያ ልጅ ቃየል ከቅንዓት የተነሣ ወንድሙን አቤልን ገደለው፤ የሰው ደም ሲፈስ የመጀመሪያው ነበር (ዘፍ. 4፥1–12፤ ዕብ. 11፥4፤ 1ዮሐ. 3፥12)። ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን «ሴት» የተባለ ሌላ ወንድ ልጅ ወለዱ (ዘፍ. 5፥3)።

ከሴት ዝሪያዎች አንዱ ሄኖክ ነበር፤ እርሱም በቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተወሰደ እንጂ ሞትን አላየም (ዘፍ. 5፥21–24፤ ዕብ. 11፥5)። ከሄኖክ በኋላ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊዎች ሆኑ፥ ስለዚህም እግዚአብሔር በዓለም ላይ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ በጎርፍ ውሃ ሊያጠፋ ወሰነ። ኖኅ የተባለውን አንድ ጻድቅ ሰው አንድ ትልቅ መርከብ ሠርቶ ቤተሰቡንና ከእያንዳንዱ የእንስሳ ዐይነት አንዳንድ ጥንድ እንዲያስገባ መመሪያ ሰጠው። በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ከጎርፍ ጥፋት ዳኑ፤ ሌሎች ሕያው ነፍስ የነበራቸው ፍጥረቶች በሙሉ ጠፉ (ዘፍ. 6፥1–22፤ 7፥11–24፤ 1ጴጥ. 3፥18–20)።

አብርሃም የኖኅ ልጅ የሴም ዝርያ ነበር፤ የተወለደውም በአሁኑ ዘመን ኢራቅ በምትባል አገር ውስጥ የምትገኝ ዑር በምትባለው ስፍራ ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን ዑር ከምትባለው ስፍራ ተነሥቶ ወደ ከነዓን (በአሁኑ ዘመን እስራኤል) ወደምትባል አገር እንዲሄድ አዘዘው። በዚህችም ምድር እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር እንደሚያበዛለትና ከዘሩ አንድ ታላቅ ሕዝብ እንደሚያስነሣ፥ በእርሱም በኩል የዓለምን ሕዝብ ሁሉ እንደሚባርክ ተሰፋ ሰጠው (ዘፍ. 12፥1–7)። ይህም በረከት እውነት የሆነው በቀጥታ የአብርሃም ዘር የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ነው (ማቴ. 1፥1፤ ሮሜ 4፥16–18፤ ገላ. 3፥6–9፤14፥29)።

አብርሃምም እግዚአብሔርን በመታዘዝ የተወለደበትን አገር ጥሎ ሄደ። አንድ ጊዜ ከአንድ ትልቅ ጦርነት በኋላ አብርሃም ከጦርነቱ ከማረከው ንብረት ሁሉ አንድ ዐሥረኛውን የእግዚአብሔር ካህን ለነበረው ለመልከ ጻዴቅ ሰጠው (ዘፍ. 14፥17–20፤ ዕብ. 5፥6፤10)። እዚህ ላይ «ዐሥራት» የሚባለው ነገር ስሙ ሲጠራ ለመጀመሪያ ነው፤ ዐሥራት ማለት አንድ ሰው ከገቢው ምንጭ ወይም ከምርቱ አንድ ዐሥረኛውን አውጥቶ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚሰጠው ነው።

እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ ወንድ ልጅ እንደሚሰጣቸው ቃል ኪዳን ገብቶላቸው ነበር። ነገር ግን ይህ ቃል ኪዳን እስከሚፈጸም ብዙ ጊዜ ስለወሰደ፥ ሣራ አገልጋይዋን አጋርን ለአብርሃም ሰጠችው። አጋርም ለአብርሃም እስማኤል የሚባል ወንድ ልጅ ወለደችለት (ዘፍ. 16፥1–4፤15)። ነገር ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባለት ዲቃላ ያልሆነ ወንድ ልጅ ከሕግ ሚስቱ ከሣራ

እንደሚሰጠው ነው። ስለሆነም አብርሃም እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መታመኑን ቀጠለ፤ በመጨረሻም ሣራ ዘጠና ዓመት ሲሞላት ወንድ ልጅ ወለደች። በዚህ ጊዜ አብርሃም አንድ መቶ ዓመት ሆኖት ነበር! ለልጁም «ይስሐቅ» የሚባል ስም አወጣለት። ይስሐቅም የአይሁድ ዘር መሥራች ሲሆን፤ እስማኤል ደግሞ የዓረብ ዘር መሥራች እንደሆነ ይታመናል። አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ዓረቦች የአይሁዳውያን ጠላቶች ናቸው (ዘፍ. 17፥15-22፤ 21፥1-5፤ ገላ. 4፥21-31)።

እግዚአብሔር በወንዶች ብልት ጫፍ የሚገኘውን ሸለፈት ቆርጦ በመጣል በሚደረግ የግርዘት ምልክት ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ገባ። ከዚያም በኋላ ወንዶች የሆኑ የአብርሃም ዝርያዎች (በይስሐቅ በኩል) በሙሉ በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ይገረዙ ነበር። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆናቸው ምልክት እንዲሆን ነው (ዘፍ. 17፥1-14)። ግርዘት ለአይሁዳውያን በጣም አስፈላጊ ነገር ነበር። ጳውሎስ ግን «አይሁዳውያን ያልሆኑ ሌሎች ሕዝቦች መገረዝ የለባቸውም» በማለት አጥብቆ ይከራከር ነበር (ሮሜ 2፥፥25-29፤ 4፥9-12፤ ገላ. 5፥2-6፤ ቆላ. 2፥11-12)።

የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ሎጥ በጣም ኃጢአተኛ በሆኑት በሰዶምና በጎሞራ ከተሞች ውስጥ ይኖር ነበር። እግዚአብሔር ሦስት መላእክትን ወደ አብርሃም ልኮ በእነዚህ ከተሞች ላይ እንደሚፈርድና እንደሚያጠፋቸው ነገረው (ዘፍ. 18፥1-2፤ 20-21)። ሎጥ ማምለጥ የቻለው በእነዚህ በሦስት መላእክት ዕርዳታ ነው (ዘፍ. 19፥15-29፤ ማቴ. 10፥15፤ ሉቃ. 17፥28-30)።

ጥቂት ዓመታት እንዳለፉ እግዚአብሔር አብርሃምን «አንድ ልጅህን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ» ብሎ በመጠየቅ ፈተነው። አብርሃም ግን በሙሉ ልቡ ታዛዥ ሆነ። ወዲያውም ይስሐቅን ወስዶ ሊሰዋው አስቦ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ከለከለው። በይስሐቅ ፈንታ የሚሠዋው አንድ የበግ ወጠጤ አዘጋጀለት (ዘፍ. 22፥1-18፤ ዕብ. 11፥17-19)። በተመሳሳይ ሁኔታም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ላከልን፤ እርሱም በእኛ በሁላችን ምትክ መሥዋዕት ሆኖ ሞተ (ዕብ. 10፥10)።

ይስሐቅ ርብቃን አገባ፤ እርስዋም ኤሳውና ያዕቆብ የተባሉ ሁለት መንትያዎችን ወለደች። ኤሳው ትልቁ ነበር፤ ነገር ግን ያዕቆብ የኤሳውን የበኩርነት በረከቱን አታልሎ ወሰደበት (ዘፍ. 25፥19-34፤ 27፥1-40)። ያዕቆብ ከኤሳው ቁጣ አምልጦ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ ሳለ ጌታን በህልሙ ተገናኘ፤ እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ሁሉ ለያዕቆብም ሰጠው፤ በእርሱ ዝርያዎች በኩል የዓለም ሕዝብ በሙሉ እንደሚባረክ ነገረው (ዘፍ. 28፥10-17)። ከላይ እንደተመለከትነው ይህ የተስፋ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ እንረዳለን።

ያዕቆብ ልያና ራሔል የተባሉ ሁለት እህትማማቾችን አገባ፤ እነርሱና የእነርሱ ገረዶች ለያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለዱለት። እነዚህም የያዕቆብ ልጆች ዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች መሠረቱ (የሐዋ. 7፥8)። ሮቤል፥ ስምዖን፥ የካህናት ጎሣ የሆነው ሌዊ፥ ይሁዳ (ክርስቶስ የመጣበት ነገድ)፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፥ ዳን፥ ንፍታሌም፥ ጋድ፥ አሴር፥ ዮሴፍና ብንያም (ዘፍ. 35፥23-26፤ ራእ. 7፥3-8) ነበሩ። ቤተሰቡም ወደ ከነዓን ተመለሱ፤ በመንገድም ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ያዕቆብን «እስራኤል» ብሎ አዲስ ስም አወጣለት። ከዚህም በኋላ የአይሁድ ሕዝብ በሙሉ «እስራኤላውያን» ተብለው መጣራት ጀመሩ (ዘፍ. 32፥22-32)።

ዮሴፍ ለያዕቆብ የተወደደ ልጅ ነበረ፤ ከቅንዓታቸውም የተነሳ የዮሴፍ ወንድሞች በባርነት ለነጋዴዎች ሸጡት፤ እነርሱም ወደ ግብጽ ወሰዱት (ዘፍ. 37፥12-36)። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር፤ ሁኔታዎችንም ወደ መልካም እየለወጠ ታላቅ የመንግሥት ባለሥልጣን አደረገው (ዘፍ. 39፥1-5፤ 41፥41-57)። በረሃብም ዘመን የዮሴፍ ቤተሰቦች ምግብ ለመግዛት ወደ እርሱ መጡ፤ ነገር ግን እርሱ ራሱን እስከገለጠላቸው ድረስ ሊያውቁት አልቻሉም (ዘፍ. 42፥1-8፤ 45፥1-11)። በኋላም መላው ቤተሰብ ወደ ግብጽ በመምጣት እዚያው መኖር ጀመሩ። ያዕቆብ (እስራኤል) የዮሴፍን ሁለት ወንዶች ልጆች ኤፍራምና ምናሴን እንደራሱ ልጆች አድርጎ ወሰዳቸው (ዘፍ. 48፥1፥5፤ የሐዋ. 7፥9-16)።

*የኢዮብ* መጽሐፍ ምናልባት የተጻፈው በአብርሃም ዘመን ሳይሆን አይቀርም፤ መጽሐፉ የሚያወሳው አንድ ኢዮብ የተባለ ሰው ስለደረሰበት ሥቃይ ነው፤ ኢዮብ ብዙ ችግር ቢደርስበትም በእምነቱ ጸና።

እስራኤላውያን በግብጽ አገር የቆዩት ለአራት መቶ ዓመታት ያህል ነበር፤ ሕዝባቸውም እጅግ እየበዛ ሄደ። ግብጻውያንም እስራኤላውያንን እጅግ ይፈሩአቸው ስለነበር ባርያዎቻቸው አደረጓቸው። እስራኤላውያን በግብጾች የደረሰባቸው ጭቆናና ሥቃይ በጣም ታላቅ ነበር፤ በመጨረሻም ከነበሩበት ሥቃይ እንዲያድናቸው እግዚአብሔር ሙሴን አስነሣው። *<u>ዘጸአት</u>* መጽሐፍ የእስራኤላውያንን ታሪክ ግለትም ከግብጻውያን እጅ እንዴት እንደዳኑ በኋላም ወደ ሲና ተራራ ጉዞአቸውን እንደቀጠሉ ይናገራል። ይህም የተፈጸመው በግምት 1400 ከ.ክ.ል.በ. ነበር። ሙሴና ታላቅ ወንድሙ አሮን የግብጽ መሪ የነበረው ፈርዖን እስራኤላውያንን ይለቃቸው ዘንድ በመደጋገም ጠየቁት፤ በእያንዳንዱም ጊዜ ፈርዖን እምቢ አለ። እግዚአብሔርም የግብጻውያን በኩር ከሚገድለው የመጨረሻው መቅሰፍት እስራኤላውያንን ለማዳን «ፋሲካ» ተመሠረተ። ከእያንዳንዱ የግብጽ ቤተሰብ ውስጥ በኩር ልጅ ሲሞት፥ የእስራኤላውያን ቤተሰቦች የሞት መልአክ «ያልፍ ዘንድ» በሰውነቱ ላይ ምንም እንከን የሌለበት አንድ በግ ጠቦት ይሠዋል፤

እያንዳንዱም የእስራኤላዊ ቤተሰብ ይበለዋል፤ ደሙም በበሩ መቃኖች ላይ ይረጫል። ይህ የሚደረገው ደምሳሹ መልአክ ቤቱን «አልፎ» እንዲሄድ ምልክት እንዲሆነው ነበር (ዘጸ. 12፥1–23)። ከዚህ አንጻር እኛም ከሞት የዳንነው ከኢየሱስ ደም የተነሣ ስለሆነ (1ቆሮ. 5፥7፤ 1ጴጥ. 1፥19፤ ራእ. 5፥6–10) ኢየሱስ «የፋሲካ በግ» ተብሎ ይጠራል። ያልበሳ ቂጣ ይበላ የነበረውም፤ ሊጡ እስኪቦካ ለመጠበቅ ጊዜ ስላልነበረ ነው። ፈርዖን የመጀመሪያ ልጁ እንደሞተ በተረዳ ጊዜ እስራኤላውያን በዚያችው ሌሊት አገሩን ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ ሰጠ (ዘጸ. 12፥29–39)። ነገር ግን ገና እስራኤላውያን ለቀው እንደወጡ ፈርዖን አሳቡን ለውጦ፤ የግብጽ ወታደሮችን ወደ እነርሱ ላከ (ዘጸ. 14፥5–14)። የእግዚአብሔርም ደመና በግብጽ ወታደሮችና በእስራኤላውያን መካከል ይመላለስ ነበር። እግዚአብሔር የቀይ ባሕርን ውሃ ከሁለት ከፈለው፤ እስራኤላውያንም በደረቅ ምድር ተሻገሩ (ዘጸ. 14፥15–22፤ 1ቆሮ. 10፥1–2)። ግብጻውያን እነርሱን ተከትለው ሲሄዱ ተከፍሎ የነበረው ውሃ ባንድነት ገጠመ፤ ግብጻውያንንም በሙሉ ሰጠሙ (ዘጸ. 14፥23–31)።

እስራኤላዊያን፥ እግዚአብሔር ሙሴ ስለመገናኛው ድንኳን አሰራር መመሪያ ወደሰጠበት ወደ ሲና ተራራ ተጓዙ (ዕብ. 9፥1–10)። እግዚአብሔር ለሙሴ ሕጉን የሰጠው በዚሁ በሲና ተራራ ላይ ነበር። የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት «የሕግ መጻሕፍት» ተብለው ይጠራሉ። በነዚህ መጻሕፍት በተለይም በዘሌዋውያን ውስጥ ለአይሁድ ሕዝብ የተሰጡት ደንቦችና ሥርዓቶች በሙሉ ይገኙባቸዋል። የአይሁድ ሕዝብ በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ትክክል ሆኖ እንዲገኝና በእግዚአብሔር የተባረኩ እንዲሆኑ ካስፈለገ እነዚህን ሁሉ ሕጎች መታዘዝ ይኖርባቸዋል። እነዚህም ሕጎች በተለያዩ ክፍሎች ይከፈላሉ፤

1/ የቁርባኖችና የእንስሳት መሥዋዕቶች፤
2/ የካህናትና የቤተመቅደስ ደንቦች፤
3/ የመንፃትና የመቀደስ፤
4/ የክብረ በዓላት፤
5/ የማህበራዊ ግንኙነት ህጎች ናቸው።

እኛ ከእንግዲህ ወዲያ የአይሁድን ሕግ[1] የመፈጸም ግዴታ የለብንም፤ ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈፅመዋል (ማቴ. 5፥17)። እግዚአብሔር የእንስሳትን መሥዋዕት የጠየቀው ደም ሳይፈሰ የኃጢአት ይቅፍታ ስለማይገኝ ነው (ዕብ. 9፥22)። ይሁን እንጂ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በእርግጥ ሕዝቡን አያነጹም፤ ልባቸውንም አይለውጡም (ዕብ. 9፥9–10)። ክርስቶስ በእውነት ሊያነፃንና በእግዚአብሔር ፊት ቅዱሳን ሊያደርገን ፍፁምና የመጨረሻ መሥዋዕት ሆነ (ዕብ. 9፥14፤ 10፥10)። ስለዚህ ክርስቶስ ከመንፃትና ከመስዋዕት ጋር የሚገናኙ ሕግጋትን ፈፅሞአቸዋል። ምድራዊ ቤተመቅደስ ፈርሶአል፤ ኢየሱስ በእውነተኛው ሰማያዊ መቅደስ የሚያገለግል ታላቅ ሊቀ ካህናችን ነው (ዕብ. 8፥1–2)።

የብሉይ ኪዳን ክብረ በዓላትም (ዘሌ. 23) ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ ፈጽሞአቸዋል ወይም ዳግመኛ ሲመጣ ይፈጽማሉ። የፋሲካና የቂጣ በዓል (ዘሌ. 23፥4–8) የተፈጸመው ኢየሱስ የእኛ የፋሲካ በግ ሆኖ ከሞት ሊያድነን በፋሲካ ወቅት በሞተልን ጊዜ ነው። (የመጀመሪያው የጌታ ራትና ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የተመገበው የፋሲካ ምግብ ነበር)። የበኩራት በዓል (ዘሌ. 23፥9–14) የተፈጸመው፥ በዚያ በዓል ቀን ክርስቶስ ከሞት በመነሣት የመጀመሪያ (በኩር) በሆነበት ቀን ነበር። እርሱ ከሞት በመነሳት የመጀመሪያ ነው፤ በኋላም በእርሱ ያመኑት ሁሉ ይነሣሉ (1ቆሮ. 15፥22–23)። የጴንጠቆስጤ በዓል አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠራውም የመኸር በዓል (ዘሌ. 23፥15–21) የተፈጸመው መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ኃይል ለመስጠት በጴንጠቆስጤ ቀን በመጣ ጊዜ ነበር (የሐዋ. 2፥1–4)። የኃጢአት ስርየት ቀን (ዘሌ. 16፥1–34፤ 23፥26–32) የተፈጸመው ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ሲሆን፤ እርቱ ሙሉ ሊሆን የቻለውም እርሱ ወደ ሰማይ ወጥቶ ያፈሰሰውን ደሙን ወደ ሰማያዊው ቤተመቅደስ ባቀረበ ጊዜ ነው (ዕብ. 9፥11–14፥ 24፥28)። ቀሪዎቹ ሁለቱ በዓላት ማለትም የዓመት መባቻ ቀንና የዳስ በዓላት (ዘሌ. 23፥23–25፤ 33–36)፤ በኢየሱስ ዳግም ምፃት ይፈጸማሉ።

የማኅበራዊ ግንኙነት ሕጎች፥ ለምሳሌ እንደ ዐሥርቱ ትእዛዛት ያሉት ሕጎች (ዘጸ. 20፥1–17) እንፈፅማቸው ዘንድ እግዚአብሔር የሚጠብቅብን ናቸው። ይሁን እንጂ እነርሱን በመጠበቅ ጻድቅ ሊሆን የሚችል ሰው እንደሌለ እናውቃለን፤ ምክንያቱም እነዚህ ሕጎች ሙሉ በሙሉ ሊፈጽም የሚችል የለም (ገላ. 2፥15–16፤ ያዕ. 2፥10)። ሕግ በላያችን ላይ ሥልጣን እንዲኖረው የተደረገው ክርስቶስ መጥቶ በእርሱ እንድናምን እስከሚያደርገን ድረስ ነበር (ገላ. 3፥24)። በኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች ከሆንን በኋላ ግን ከእንግዲህ ወዲህ ከሕግ በታች አይደለንም (ሮሜ 7፥6፤ ገላ. 3፥13፥ 25)። ይሁን እንጂ በኃጢአት እየኖርን

---

[1] ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን «የሞራል ሕግ» እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል፤ በተለይም ዐሥርቱን ትእዛዛት መጠበቅ ይኖርባቸዋል (ዘጸ. 20፥1–17)። ሆኖም ኢየሱስ የሞራልን ሕግ በሁለት ሕጎች አጠቃሎታል፤ እግዚአብሔርን መውደድና ሌላውን ሰው መውደድ (ማር. 12፥30–31)፤ እነዚህን ሁለት ታላላቅ ሕጎች ብንጠብቅ ዐሥሩንም ትእዛዛት እንደጠበቅን ይቆጠራል (ማቴ. 22፥40፤ ሮሜ 13፥9)።

የተሰጠንን ነጻነት መቀለጃ ማድረግ አይገባንም፡ (ገላ. 5፥13)። በአዲስ ኪዳን ዋና ትምህርት የሕግ ፍፃሜ «እርስ በርሳችን መዋደድ ነው» (ማቴ. 22፥36-40፤ ሮሜ 13፥8-10፤ ገላ. 5፥14)። ኢየሱስን በሚገባ የሚወድዱ ሰዎች ደግሞ የእርሱን ትእዛዝ ይፈጽማሉ (ዮሐ. 14፥15፤ 1ዮሐ. 2፥4-5)።

*በዘኍልቁ* መጽሐፍ የእስራኤላውያንን የሲና በረሃ ጉዞአቸውን እንደቀጠሉ እናነባለን፤ ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ያጉረመርሙና ያምጹ ነበር። ቆራሕ የተባለ ሰው ከነዚህ አመጾች ለአንዱ መሪ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን እርሱንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች አጠፋ (ዘኍ. 16፥1-40)። በጉዞአቸው መጨረሻ ላይ «የተስፋይቱን ምድር»፥ ምድረ ከነዓንን (እስራኤልን) ሄደው እንዲሰበኙ ዐሥራ ሁለት ሰላዮች ተላኩ። ይህች ምድር እግዚአብሔር ለአብርሃም ዝርያዎች ማለትም ለእስራኤላውያን ሊሰጣቸው ተስፋ የገባላቸው ምድር ናት። ከሰላዮቹ ዐሥሩ «ምድሪቱ ግዙፋን ሰዎችና ጠንካራ ከተሞች የሚገኙባት ስለሆነች እርስዋን ወርሮ ለመያዝ በጣም ያስቸግራል» አሉ (ዘኍ. 13፥17-33፤ 1ቆሮ. 10፥1-11)። ሕዝቡም እነዚህ ሰላዮች በሰጡት መረጃ በጣም ፈሩ። ስለዚህም እግዚአብሔር ሕዝቡ እምነት ስላልነበራቸው በምድረ በዳ ለአርባ ዓመት እንዲንከራተቱ በማድረግ ቀጣቸው (ዘኍ. 14፥1-38)። በእነዚህ በአርባ ዓመታት ውስጥ «መና» የሚባል ከሰማይ የሚወርድ ልዩ እንጀራ እንዲመገቡ ተደረገ (ዘጸ. 16፥14-31፤ ዮሐ. 6፥30-35)። ሁለት ጊዜ «ውሃ ጠማን!» እያሉ አጉረመረሙ፤ እግዚአብሔርም ከዐለት ውሃ አጠጣቸው (ዘጸ. 17፥1-7፤ ዘኍ. 20፥1-11፤ 1ቆሮ. 10፥3-5)። አንድ ጊዜ ደግሞ ከማጉረምረማቸው የተነሣ በመርዘኛ እባብ በሚቀጡበት ወቅት፥ እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ ለሙሴ ሕዝቡን እንዴት መርዳት እንዳለበት ነገረው። ሙሴም የነሐስ እባብ ሠርቶ በእንጨት ላይ ሰቀለው፤ በመርዘኛ እባቦቹ የተነከሱ ሰዎች ወደ ተሰቀለው የነሐስ እባብ ሲመለከቱ በሕይወት ይኖራሉ (ዘኍ. 21፥4-9)። እኛም እንዲሁ በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ኢየሱስን በእምነት ስንመለከት ከኃጢአትና ከሞት እንድናለን (ዮሐ. 3፥14-15)።

የአርባው ዓመት የበረሃው ጉዞ ሊያበቃ አካባቢ እስራኤላውያን ወደ ሞአብ ምድር ተጓዙ። የሞአብ ንጉሥ የነበረው ባላቅ ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ፤ ደግሞም ፈራ። ስለዚህ በምድሪቱ የሚገኘውን አንድ በለዓም የተባለ ነቢይ ቀጠረና እስራኤላውያንን እንዲረግምለት አዘዘው። በለዓምም ሄዶ እንዲረግም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠየቀ፤ በኋላም «እሺ ሂድ» የሚለውን ፈቃድ አገኘ። ነገር ግን እግዚአብሔር በለዓምን እጅግ ተቆጥቶት ነበር። በለዓም ሲሄድ ሳለም፥ አህያው በመንገድ ላይ አንድ የሚያስፈራ የእግዚአብሔርን መልአክ አየች፤ ስለዚህ አህያይቱ በለዓምን በማስጠንቀቅ ተናገረችው። በለዓምም እስራኤላውያንን መረቀ እንጂ አልረገማቸውም። ይሁን እንጂ በለዓም የባላቅን ገንዘብ መውሰድ ስለፈለገ፥ እስራኤላውያን የሚደክሙበትን አንድ ከፋ ምክር መከረው። ይህም ባዓል የተባለውን ጣዖት እንዲያመልኩ እንዲያታልላቸው ነበር (ዘኍ. 22፥21-35፤ 25፥1-3፤ 2ጴጥ. 2፥15-16፤ ራእ. 2፥14)።

እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ሙሴ ለመጨረሻ ጊዜ ለሕዝቡ መልእክት አስተላለፈ፤ ይህም መልእክት *በዘዳግም* መጽሐፍ ተመዝግቧል። ሙሴ ስለ እስራኤላውያን ታሪክና ስለ ሕግም በድጋሚ አመለከተ፤ ሕግን ቢፈጽሙ የሚያገኙትን በረከትና ባይፈጽሙ ግን የሚከተላቸውን መርገም በሙሉ ዘረዘረላቸው (ዘዳ. 11፥26-28)። ከዚህ በኋላ ሙሴ ሞተ፤ እግዚአብሔርም ቀበረው።

*በኢያሱ* መጽሐፍ ኢያሱ ሙሴን በመተካት እንዴት የእስራኤል መሪ ሊሆን እንደቻለ እናነባለን። እስራኤላውያን የኢያሪኮን ከተማ ወረሱ፤ በእግዚአብሔር እቅድና በእግዚአብሔር ኃይል ተመርተው አንድ ምድር ሲወርሱ ይህ የመጀመሪያቸው ነበር። እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት በሰልፍ ሆነው በከተማይቱ ዙሪያ ከሄዱ በኋላ መለከታቸውን ነፍተው ጮኹ፤ የከተማይቱም ግንቦች ፈረሱ፤ እነርሱም ሰተት ብለው ወደ ከተማይቱ ገቡ (ኢያ. 6፥1-21)። ረዓብ የተባለች አንዲት ሴተኛ አዳሪ ቀደም ሲትል ሁለት የእስራኤላውያንን ሰላዮች በከተማ ውስጥ ደብቃ ነበር፤ ከተማይቱ ከወደቀች በኋላ ይህች ሴተኛ አዳሪ ከጥፋት በመትረፍ ተሸልማ ነበር (ኢያ. 2፥1-21፤ 6፥22-25፤ ዕብ. 11፥30-31)። በኋላም የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋ ትውልድ ሐረግ ልትሆን በቅታለች (ማቴ. 1፥5)። ኢያሱ ቀሪውን የከነዓን ምድር ወርሶ በቁጥጥሩ ሥር አደረገ፤ ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ጎሣዎችም አከፋፈላቸው።

*የመሳፍንት* መጽሐፍ ኢያሱ ከሞተ በኋላ የእስራኤልን መንግሥት ያስተዳድሩ ስለነበሩ መሳፍንት ይነግረናል። ንጉሣቸውም እግዚአብሔር ነበር፤ ይሁን እንጂ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በመታዘዝ አልኖረም። ብዙውን ጊዜ ፊታቸውን መልሰው በጎረቤቶቻቸው የነበሩትን አማልክትና ጣዖታት ይከተሉ ነበር። እንዲህም በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ያደርጉ ነበር። እግዚአብሔርም በጨቋኞቻቸው እጅ እንዲወድቁ አሳልፎ ይሰጣቸው ነበር። ከጠላቶቻቸው እጅ ነጻ እንዲወጡ ወደ እግዚአብሔር በሚጮሁበትም ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ እነርሱን ነጻ ለማውጣት አንድ አዳኝ ያስነሣላቸው ነበር (መሳ. 2፥10-19)። በጣም ዝነኞች የነበሩት አዳኞች ወይም መሳፍንት ጌዴዎን፥ ባርቅና፥ ሳምሶን ነበሩ (ዕብ. 11፥32)።

*የሩት* መጽሐፍ የሚነግረን የዳዊት ቅድመ አያት ስለነበረች ስለአንዲት ሞአባዊት ሴት ነው። ይህች ሴት እስራኤላዊት አልነበረችም፤ ነገር ግን በእውነተኛው አምላክ ያመነች ሙአባቲት ነበረች፤ አንድ እስራኤላዊ ሰው አግብታ የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ለመገኘት በቅታለች (ማቴ. 1፥5)።

*1ሳሙኤል* የሚናገረው የመጨረሻው መስፍን ስለነበረ ሰው ነው። የሳሙኤል እናት ልጅዋ ገና ከሕፃንነቷ በቤተ መቅደስ ውስጥ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንዲሆን በፈቃዱ ሰጥታው ነበር። በዚያም እግዚአብሔር ሳሙኤልን አነጋገረው፤ ሳሙኤል ነቢይም መስፍንም ሆኖ ያገለግል ነበር። በዕድሜው እየሸመገለ ሲሄድ ሕዝቡ በዙሪያቸው እንደነበሩት አገሮች ሁሉ ንጉሥ እንዲኖራቸው ፈለጉ። ሳሙኤልም ምድራዊ ነገሥታት ብዙ ችግር ሊያመጡባቸው እንደሚችሉ አስጠነቀቃቸው፤ ሕዝቡ ግን እምቢ አሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር በመጨረሻ ንጉሥ ሊሰጣቸው ወሰነ (1ሳሙ. 8፥6–22)። ሳኦል የተባለ ሰው በእግዚአብሔር ተመረጠ፤ እርሱም በመጀመሪያ በሚገባ መራቸው። ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ኃጢአት በሚሠራበት ወቅት ንስሓ አልገባም፤ በመጨረሻም እግዚአብሔር ከንጉሥነቱ አስወግደው።

እግዚአብሔር ሳሙኤልን «ሂድና ዳዊት የሚባል አንድ ወጣት እረኛ ልጅ በዘይት ቀባው፤ እርሱም የሚቀጥለው የስራኤል ንጉሥ ይሆናል» አለው። የጌታም መንፈስ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ ሆነ። አንድ ጊዜ ጎልያድ የሚባል አንድ ግዙፍ ሰው እስራኤላውያንን ይገዳደር ነበር፤ ከእርሱ ጋር ሊዋጋ የደፈረ አንድም አልነበረም። በመጨረሻ ዳዊት «እኔ ይህን ሰው እዋጋዋለሁ!» አለ፤ በአንድ ወንጭፍ ጠጠርም ያንን ግዙፍ ሰው በመሬት ላይ አንከባለለው (1ሳሙ. 17፥32–51)። ከዚያን በኋላ ዳዊት አንድ ታላቅ ወታደር ሆነ፤ ሳኦልም በዚህ ምክንያት ቀናበት። ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ብዙ ጊዜ ሞከረ፤ ዳዊትም በእያንዳንዱ ጊዜ አመለጠ። ምንም እንኳ ዳዊት ሳኦልን ለመግደል ሁለት ምቹ አጋጣሚዎች ቢያገኝም እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን የቀባውን ሰው እኔ አልገድልም በማለት ሁለቱንም ጊዜ ለቀቀው። ምንም እንኳ በኋላ እግዚአብሔ የናቀው ቢሆንም ሊገድለው አልፈለገም።

*2ሳሙኤልና 1ዜና መዋዕል* ሁለቱም መጻሕፍት የሚናገሩት ሳኦል በጦርነት ከሞተ በኋላ ዳዊት እንዴት ንጉሥ ሊሆን እንደቻለ ነው። ዳዊት ነግሦ የነበረው ከ1010 እስከ 970 ከ.ክ.ል.በ. ነበር። ንጉሥ ከሆነም በኋላ ወዲያውኑ የጌታን ታቦት መልሶ አመጣ፤ ቀደም ሲል ይህን ታቦት የእስራኤል ጠላቶች ፍልስጤማውያን ማርከው ወስደውት ነበር። አሁን ግን በታላቅ ደስታ የአይሁድ ዋና ከተማ ወደነበረችው ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው (2ሳሙ. 6፥12–15)። ዳዊት ለጌታ አንድ ቋሚ ቤተ መቅደስ ለመሥራት ፈለገ፤ እግዚአብሔር ግን «ልጅህ ይሥራ እንጂ አንተ አትሥራ» ብሎ ነገረው፤ ዳዊት ታላላቅ ጦርነቶችን ድል ነሥቶ በእግዚአብሔር ተባርኮ ነበር። እግዚአብሔር ለዳዊት «መንግሥትህ ለዘላለም የጸና ይሆናል» የሚል ተስፋ ሰጠው፤ ይህም ተስፋ መንግሥቱ ለዘላለም በጸናው በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሞአል። ኢየሱስ ከዳዊት ዘር የተገኘ ነው (ማቴ. 1፥1)፥ በኋላም «የዳዊት ሥርና» «የይሁዳ አንበሳ» ተብሎአል (ራእ. 5፥5)። የኋለኞቹ ነቢያት ዳዊትን «እውነተኛ ንጉሥ» እያሉ ይጠሩታል፤ ይሁን እንጂ ዳዊትም ቢሆን ኃጢአት የሠራበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን ከሳኦል በብዙ መንገድ ይለያል፤ ምክንያቱም እርሱ ሁልጊዜ ንስሓ እየገባ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት ያድስ ነበር። ዳዊት ሙዚቀኛና ግጥም ገጣሚም ነበር። ከመዝሙሮቹም ብዙዎቹን የጻፈው እርሱ ነበር፤ ከእነዚህ መዝሙሮች አንዳንዶቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለሞቱ ጭምር ትንቢት ይናገራሉ (መዝ. 22፥69)።

*1 እና 2 ነገሥት* እንዲሁም *2 ዜና መዋዕል* የሚናገሩት ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን መንገስ ጀምሮ ስለ እስራኤል መንግሥት ነው። እግዚአብሔር ስለሞንን «የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ፤ እኔም እሰጥሃለሁ» አለው። ሌሎች ብዙ ሰዎች ቢሆኑ የሚጠይቁት ሀብት ወይም ክብር ነበር፤ ሰለሞን ግን አስተዋይ ልብ ወይም ጥበብ እንዲሰጠው ጠየቀ (1ነገ. 3፥5–9)። እግዚአብሔርም የጠየቀውን ጥበብና በተጨማሪም ብዙ ሀብትና ክብርም ሰጠው (ማቴ. 12፥42፤ ሉቃ. 12፥27)። ሰለሞን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የጥበብ መጻሕፍትን ጽፎአል፤ እነርሱም *ምሳሌ፥ መክብብና፥ መኃልየ መኃልይ* የተባሉት ናቸው። ሰለሞን የፈጸመው ታላቅ ሥራ ለእግዚአብሔር ቋሚ ቤተመቅደስ፥ በኢየሩሳሌም መገንባት ነበር።

ሰለሞን ከሞተ በኋላ የእስራኤል መንግሥት ተከፋፈለ። ዐሥሩ የሰሜን ነገዶች ለብቻቸው ተገነጠሉ፤ ይህም የእስራኤል መንግሥት ተብሎ ተጠራ። የቀሩት ሁለት መንግሥታት በደቡብ የይሁዳ መንግሥት የተባለውን መሠረቱ። የይሁዳ መንግሥት ይገዛ የነበረው ከሰሎሞን ልጅ ከሮብአም ጀምሮ በዳዊት ነገድ ነበር። የመጀመሪያው ንጉሥ የሰለሞን ልጅ ሮብዓም ነበር፤ የተከፈለውም መንግሥት ይዞታ ለ344 ዓመት ቀጠለ። ከይሁዳ ነገሥታት አንዳንዶቹ ለእግዚአብሔር ታዘዙ፤ ሕዝቡንም ጣዖትን ከማምለክ ወደ እውነተኛው አምላክ መለሱአቸው። ሌሎቹ ነገሥታት ግን በእግዚአብሔር ፊት ጻያፍ ነገር ሠሩ፤ ሕዝቡንም ወደ ጣዖት አምልኮ መሩአቸው። በሰሜን ከነበረው ከእስራኤል መንግሥት ነገሥታት አንድም እግዚአብሔርን ያመለከ አልነበረም። የመጀመሪያው ንጉሥ ሁለት ከወርቅ የተሠሩ ጥጆችን ሠርቶ አንዱን በቤቴኤል፥ ሌላውን በዳን ተከለ። ሕዝቡም (በኋላ ሳምራውያን የተባሉ) እነዚያን ጣዖታት ማምለካቸውን ቀጠሉ። ይህንኙም ያደረጉት እውነተኛን አምላክ በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተመቅደስ ማምለክ ትተው ነው። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዳውያን ሳምራውያንን ይጸየፉአቸው ከነበረው ምክንያት አንዱ ይህ ነበር (ዮሐ. 4፥9፥ 19፥19–24)። አንዱ ዐመጸኛ የእስራኤል ንጉሥ አክአብ ሲሆን፤ እርሱም ኤልዛቤል የምትባል አንዲት የባዕድ አገር ሴት አግብቶ ነበር። ባልና ሚስቱ በጊዜው የነበረውን ኃይለኛ፥ የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልያስን አይወዱትም ነበር (1ነገ. ከምዕራፍ 17–18)። ኤልያስና እርሱንም የተካው ኤልሳዕ (2ነገ. 2፥8) እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ለማሳየት ብዙ ተአምራትን ፈጽመዋል። (ሉቃ. 4፥24–27) ኤልያስ አልሞተም፤ ይልቁንም በቀጥታ ወደ ሰማይ ተወሰደ (2ነገ. 2፥11፤ ማር. 9፥4–5)።


በነዚያ ዓመታት ውስጥ ሌሎች ብዙ ነቢያት ለእስራኤልና ለይሁዳ ሕዝቦች ትንቢት ተናግረዋል። ሕዝቡ በዐመፅና በኃጢአት መኖራቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ ፍርድ ሊመጣባቸው እንደሚችል ነቢያቱ አስጠንቅቀዋል። በሁለቱ መንግሥታት ውስጥ ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች ንስሓ የማይገቡ ከሆነ ወደ ባዕድ አገር ተሰድደው ሊሄዱ እንደሚችሉ ነቢያቱ ትንቢት ይናገሩባቸውም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሕዝቡ ማስጠንቀቂያውን በመስማት ንስሓ ሲገቡ፤ ብዙን ጊዜ ግን ንስሓ ለመግባት ፈቃደኞች አልሆኑም። በመጨረሻም ልክ ነቢያቱ እንደተናገሩት ሆነ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደሌሎች አገሮች እንዲሰደዱ አደረገ። የእስራኤል ሕዝብ በ722 ከ.ክ.ል.በ. ወደ አሦር (የአሁኑ ሲርያ) ተወሰዱ። የይሁዳ ሕዝብ ደግሞ በ586 ከ.ክ.ል.በ. ወደ ባቢሎን (የአሁኑ ኢራቅ) ተወሰዱ። በተከፈለው መንግሥት ዘመን የጻፉት ነቢያት በቅደም ተከተል ተራቸው የሚከተሉት ናቸው፤ *ኢዮኤል* (የሐዋ. 2፥16–21)፥ *ዮናስ* (ማቴ. 12፥38–41)፥ *አሞጽ፥ ሆሴዕ፥ ኢሳይያስ* (እነዚህ ከሌሎች ነቢያት ይልቅ በአዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ ተጠቅሰዋል) *ሚክያስ፥ ናሆም፥ ሶፎንያስ፥ ዕንባቆምና ኤርምያስ፥ ሰቆቃው ኤርምያስንም* የጻፈው ይኸው ነቢይ ነው። ከነቢያት አብዛኛዎቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ፥ መሞትና ዳግም መምጣት ትንቢት ተናግረዋል።

በስደት በነበሩበት ወቅት ምንም *ታሪካዊ* ጽሑፍ አልነበረም፤ ነገር ግን ነቢያቱ *ሕዝቅኤልና ዳንኤል* በዚህ ዘመን ይጽፉ ነበር። ምናልባት *ኦቢድይም* በዚህ ዘመን ትንቢት ሳይናገር አልቀረም። የምርኮ ዘመን ሊያበቃ አካባቢም የፋርስ መንግሥት (የአሁኑ ኢራን) ባቢሎንን ማርኮ ያዘ።

በ538 ከ.ክ.ል.በ. የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ አዋጅ አውጀ፤ አዋጁም «የሚፈልግ ሰው ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ ቤተመቅደሱን ማደስ ይችላል» የሚል ነበር። ስለዚህም አዋጅ *ዕዝራ* በጻፈው የታሪክ መጻሕፍ ውስጥ ማንበብ እንችላለን። በመጀመሪያ ጥቂት ሰዎች በዘሩባቤል መሪነት ሄደው፤ ቤተ መቅደሱንም ማደስ ጀመሩ፤ ተቃውሞ ስለነበረባቸው ሥራው ለጥቂት ጊዜ ቆመ። ሕዝቡ በነቢያቱ *በሐጌና በዘካርያስ* ተበረታትተው በመጨረሻ ቤተ መቅደሱን ሰርተው ጨረሱ (ዕዝ. 6፥14–16)። በ458 ከ.ክ.ል.በ. ዕዝራ ሁለተኛውን ከምርኮ የተመለሰ ሕዝብ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ዕዝራ ካህን ስለነበረ የአይሁድን ሕግ እንደገና አስተማረ፤ አንዳንድ ለውጦችንም አደረገ፤ ለውጡም አንዳንድ የባዕዳን ሴቶችን በማግባት ኃጢአት የሠሩትን ሰዎች የሚነካ ሲሆን፤ እነዚህ ሴቶች አይሁዳዊ ባሎቻቸውን ወደ ስሕተት አምልኮ ይመሩ ነበር። በዚሁ ዘመን *አስቴር* የተባለች አንዲት አይሁዳዊት የፋርስ ንግሥት ታሪክ ተከናወነ፤ ይህች ሴት የአይሁድን ሕዝብ ከታላቅ ጥፋት ለማዳን እግዚአብሔር የተጠቀመባት ነበረች።

ከዓመታት በኋላም የፋርስ ንጉሥ የወይን ጠጅ አሳላፊ የነበረው *ነህምያ* ከሦስተኛው የምርኮ ተመላሽ እስራኤላውያን ጋር በመሆን በኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ የነበሩትን ግንቦች ለማደስ ወደዚያ ሄደ (ነህ. 6፥15–16)። ነቢዩ *ሚልክያስ* የተናገረውም በዚህ ዘመን ነበር። ከ400 ዓመት ከ.ክ.ል.በ. መጥመቁ ዮሐንስ መጥቶ የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት እስከተናገረ ጊዜ ድረስ ሌላ ማንም ነቢይ ስለ እስራኤል ትንቢት አልተናገረም።

**የብሉይ ኪዳን መጽሀፍትን በተፃፉበት ዘመን ቅደም ተከተል የሚያሳይ ሰሌዳ**


1100
1000
900
800
700
600
500 ዓ.ዓ.
ፍጥረት
አብረሃም
400 ዓመታት በግብጽ ባርነት
መሳፍንት
የተከፈለው መንግሥት
70 ዓመት በምርኮ
መመለስ
የ40 ዓመት የምድረበዳ ጉዞ
የተስፋይቱ ምድር
ጥምር መንግስት
ዘፍጥረት
ዘጸአት
ዘሩጌቅሩ
ዘዳግም
ኢያሱ
መሳፍንት ፣ ፣
1 ሳሙኤል
2 ሳሙኤል
1 2
ነገስት
ዕዝራ
ነህምያ
ፍጥረት
ጎርፍ
ቃል ኪዳን
አብርሃም
ይስሐቅ
ያዕቆብ
ዮሴፍ
12 ጎሣዎች
ከግብጽ እስከ ሲና
ከሲና እስከ ዮርዳኖስ
የሙሴ የመጨረሻ ንግግር
ወደ ተስፋይቱ አገር መግባት እያሸነፉ ምድርን መውረስ
እያንዳንዱ ሰው በዐይኑ ፊት ትክክል የመሰለውን ሲያደርግ
ንጉሥ ሳኦል
ሳኦልና ዳዊት በመካከላቸው የነበረ ግጭት
1 ዜና
ንጉሥ ዳዊት
2
ሰሎሞን
ዜና
እስራኤል ይሁዳ
ዕዝራ
የመጀመሪያው ና የሁለተኛው ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለስ
የቤተ መቅደስ መታደስ
ነህምያ
የሥ ስተኛው ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለስ
የግንቡ መሰራት
እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሲናገር
ዘሌዋውያን
ሕግ
እግዚአብሔር በኢያሱ በኩል እየመራው
ሩት
ከክርስቶስ ቅድመ አያቶች አንዱ
መዝሙር
እስራኤል
ዮናስ
አሞጽ
ሆሴዕ
ይሁዳ
አብድዮ
ኢዮኤል
ኤሳይያስ
ሚክያስ
ናሆም
ሶፎንያስ
ኤርምያስ
ዕቆቃው
ዕንባቆ
ሕዝቅኤል
ዳንኤል
አስቴር
ሕዝቡን አዳነች
ሐጌ
ዘካሪያስ
ሚልክያስ
ምሳሌ
መክብብ
መኃልየ መኃልይ
ኢዮብ ?
መልካም ሰው ሲሠቃይ
ቁልፍ
ትክክለኛው ቀን አልታወቀም
በግምት 100 ዓመታት
ከዚህ በኋላ ቀኖቹ ተረጋግጠዋል
ታሪክ
ግጥም
ትንቢት

# መጽሐፍ ቅዱሳችን እንዴት ተፃፈ

ብሉይ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በአንድ ሺ ዓመታት ዘመን ውስጥ ነው፤ ይህም በግምት ከ1400 እስከ 400 ከ.ክ.ል.በ. መሆኑ ነው። የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት፥ አንዳንድ ጊዜ የሕግ መጻሕፍት ወይም የሙሴ ሕግ ተብለው የሚጠሩት አብዛኛዎቹ የተጻፉት በሙሴ ሲሆን እነርሱም የተጻፉት 1400 ከ.ክ.ል.በ. ነበር። የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ የተጻፈው በነቢዩ ሚልኪያስ ሲሆን እርሱም የተጻፈው በ400 ከ.ክ.ል.በ. ነበር።

የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በአይሁዳውያን ጸሐፊዎች በጥንቃቄ በእጅ በመገልበጥ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ መጥተዋል። አንድ ጸሐፊ የቅዱሳት መጻሕፍትን አንድ አዲስ ግልባጭ በሚገለብጥበት ጊዜ አሮጌውን ግልባጭ ያጠፋዋል፤ ከዚህም የተነሣ ብዙ ዘመን የቆዩትን የብሉይ ኪዳን ግልባጮች በአሁኑ ዘመን ማግኘት አይቻልም። ዛሬ የሚገኘው ብዙ ዘመን የተቆጠረለት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በጣም በሩቅ ጊዜ የተገለበጠ ነው ቢባል ከክርስቶስ ልደት በኋላ በዐሥረኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተገለበጠ ነው (1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው)።

ይሁን እንጂ በ1947 ዓ.ም. ብዙ ዘመን የቆዩ የቆዳ የጽሑፍ ጥቅልሎች በእስራኤል አገር በአንድ እረኛ ልጅ ተገኝተዋል። ልጁም ያገኛቸው ከኢያሪኮ ከተማ በስተደቡብ 8 ማይል ርቆ በሙት ባሕር አጠገብ በሚገኝ በአንድ ዋሻ ውስጥ ነው። ስለዚህም «የሙት ባሕር የጽሑፍ ጥቅልሎች» በመባል ይታወቃሉ። በጥቅልሎቹም ውስጥ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አብዛኛዎቹ ይገኙባቸዋል። የሙት ባሕር የጽሑፍ ጥቅልሎች የተገለበጡት ከ.ክ.ል.በ. በአንደኛውና በሁለተኛው መቶ ዓመት ውስጥ ነው። በጣም ጥቃቅን የሆኑ የሆሄያትና የአፃፃፍ ዘይቤ ልዩነት ከመያዛቸው በቀር ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ግልባጭ ከተገኘው ከአሁኑ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ግልባጭ ጋር ቀጥታ ተመሳሳይ ናቸው። ይህም የአይሁድ ጸሐፊዎች መጻህፍትን ይገለብጡ የነበረው በታላቅ ጥንቃቄና ፍጹምነት እንደነበረ ማስረጃ ነው። በመሆኑም በቅርብ ጊዜ የተገለበጡት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (ዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደባቸው) በጥንት ጊዜ ብሉይ ኪዳንን ከጻፉት ሰዎች መጻህፍት ጋር ሙሉ በሙሉ ትክክል እንደሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ብለን የምናምንበት ምክንያት ቀጥሎ እንደምንመለከተው፥ የመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች በልዩ መንገድ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው፥ እግዚአብሔር እንዲጻፉ የፈለገውን ስለፃፈ ነው። ስለዚህ፥ የእነርሱ ጽሑፍ ቅጂ በታማኝነትና ያለምንም ስህተት በዓመታት መካከል ወደ እኛ ተላልፈዋል ብለን መተማመን እንችላለን።

አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች የተጻፉት የአይሁዳውያን የጥንት ቋንቋ በሆነው በዕብራይስጥ ቋንቋ ነበር። ይሁን እንጂ በክርስቶስ ዘመን ዕብራይስጥ ቋንቋ በተራው ሕዝብ የሚነገር አልነበረም፤ በይብራይስጥ ቋንቋ የሚጠቀሙት የአይሁድ ካህናትና የሃይማኖት ጠበብት ነበሩ። በክርስቶስ ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ የተለመደ ቋንቋ አረማይክ ሲሆን፤ ክርስቶስም ይናገር የነበረው በዚህ ቋንቋ ነበር።

ይሁን እንጂ በክርስቶስ ዘመን የሚጠቀሙበት ሌላ ዋና ቋንቋ ነበር። እርሱም የግሪክ ቋንቋ ነው። ግሪክ በሜድትራኒያን ባሕር ዙሪያ የሚገኙ አገሮች ሁሉ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ብዙ የተማሩ ሰዎች የሚያውቁት ቋንቋ ነበር። ዕብራይስጥ የሚያውቁ ሰዎች ጥቂት ስለነበሩ፥ ብሉይ ኪዳን ከ.ክ.ል.በ. 200 ዓመት በግሪክ ቋንቋ ተተረጎመ። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን ሲጠቅሱ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙት ከዚህ ከግሪክ ትርጉም እንጂ ጥንት በዕብራይስጥ ከተጻፈው አልነበረም።

ብሉይ ኪዳን የያዘው ሠላሳ ዘጠኝ መጻሕፍትን ሲሆን እነርሱም በብዙ ደራሲያን የተጻፉ ነበሩ። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ስላሉ ዝርዝር ነገሮች የተሰጠውን ማብራሪያ በአጠቃላይ መግለጫው «የብሉይ ኪዳን እጥርጥር» በሚባለው ክፍል ይመለከታል።

## አዲስ ኪዳን

አዲስ ኪዳን የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ሲሆን መጻፍ የተጀመረውም ክርስቶስ ከሞተ ከሃያ ዓመት በኋላ ነበር። ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው የመጨረሻ ትእዛዝ፤ ለዓለም በሙሉ ምስክሮቹ እንዲሆኑ ስለነበር (የሐዋ. 1፥8)፤ ከኤንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ ደቀመዛሙርቱ ስለ ክርስቶስ ሕይወትና ትምህርት ለሌሎች መንገር ጀመሩ። ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ደቀመዛሙርቱ ወይም ሐዋርያቱ በአፍ እየተናገሩ ቃሉን ያስተምሩ ነበር። ነገር ግን ሐዋርያቱ እያረጁ ሲሄዱ ትምህርታቸው አንዳች ሳይዛነፍ በጹሑፍ ለመጪው ትውልድ መተላለፉ አስፈላጊ ሆነ። ይህም ለወደፊት ዘመናት በትክክል መተላለፉን ለማረጋገጥ ይጠቅም ነበር፤ ስለዚህ ከሐዋርያት አንዳንዶቹና የቅርብ ተባባሪዎቻቸው ስለ ክርስቶስ ሕይወት መጻፍ ጀመሩ። ሐዋርያው ጴጥሮስ የማርቆስን ወንጌል ለመጻፍ ከማርቆስ ጋር አብሮ ሠራ (በማርቆስ መግቢያ ውስጥ ይመለከቷል)። ሐዋርያው ማቴዎስ የማቴዎስን ወንጌል ጻፈ። ሐዋርያው ዮሐንስ የዮሐንስን ወንጌል ጻፈ። የሐዋርያው ጳውሎስ የቅርብ ረዳት የነበረው ሉቃስ የሉቃስን ወንጌልና የቀድሞይቱ ቤተክርስቲያን ታሪክ የሆነውን የሐዋርያት ሥራን ጻፈ።

ስለ ክርስቶስ ሕይወት ከመጻፍ በተጨማሪ ሐዋርያቱ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበትን ምክንያት አስፋፍተው ለመጻፍ ግድ ሆነባቸው። እንዲሁም በአዳዲስ አብያተክርስቲያናት ዘንድ መብቀል የጀመሩትን አንዳንድ ስሕተቶችና ሐሰተኛ ትምህርቶች ለማረምም መጻፍ ነበረባቸው። ስለዚህ ለመሠረቱአቸው አዳዲስ አብያተክርስቲያናት መልእክት መጻፍ ጀመሩ። ሐዋርያው ጳውሎስ በ50 ዓ.ም. ገደማ ከተፃፈው የገላትያ መልዕክት አንስቶ (የገላትያ መግቢያን ይመለከቷል) በአጠቃላይ ዐሥራ ሦስት መልእክቶችን ጻፈ። አንዳንድ ሊቃውንት ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በመጀመሪያ የተጻፈው የያዕቆብ ማለትም የኢየሱስ ወንድም መልእክት ነው ብለው ያምናሉ (የያዕቆብን መግቢያ ይመለከቷል)።

ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በመጨረሻ የተጻፈው የራእይ መጽሐፍ ነው፤ ይህም መጽሐፍ የተጻፈው በሐዋርያው ዮሐንስ ሲሆን እርሱም የተጻፈው ከ90–95 ዓ.ም. ገደማ ነው። ስለዚህ መላው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው ያበቁት ከ50 ዓ.ም. እስከ 100 ዓ.ም. መካከል ባለው ዘመን ነው።

ከአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከመጀመሪያዎቹ ጽሑፎች አብዛኛዎቹ የተጻፉት ፓፒረስ[1] ከሚባል ተክል ከተሠራ ወረቀት ነበር፤ ይህ ፓፒረስ እንደ ዘመኑ ወረቀት ነዋሪ አልነበረም፤ ስለሆነም ለብዙ ጊዜ አይቆይም ነበር።

ከዚህም የተነሣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በፓፒረስ ጥቅል የጻፉአቸው ጹሑፎች በሙሉ ጠፍተዋል፤ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ጹሑፎች ሁሉ ዛሬ የሚገኙት የአዲስ ኪዳን ጹሑፎች የዋናው ቅጅ ማለትም ከፓፒረሱ የተቀዱ ናቸው።

ከክርስቶስ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት አዲስ ኪዳን ጹሑፎች በጥንቃቄና በትክክል በፓፒረስ ጥቅል በጸሐፊዎች አማካይነት የተገለበጡ ናቸው። 1900 ዓመት እንደገባ ወዲያውኑ፥ ከነዚህ ከፓፒረስ ግልባጮች ከነበሩት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጥቂቶቹ በግብጽ አገር በአሸዋ ውስጥ ተቀብረው ተገኝተዋል። ሌሎቹ ደግሞ በመከላከያ መያዣ ያዎች በጥንቃቄ ተጣጥፈው ተገኝተዋል። ከነዚህም በጣም ያረጀው ግልባጭ በ135 ዓ.ም. የተሠራ ሲሆን ከዮሐንስ ወንጌል ጥቂቱን ክፍል የያዘ ነበር። በመቀጠል በጣም የቆዩት ጥቅሎች በ200 ዓ.ም. ላይ የተገለበጡና ከአዲስ ኪዳን አብዛኛውን ክፍል የያዙ ነበሩ፤ እነዚህ የጥንት ጥቅሎች በአሁኑ ጊዜ በሙዝየም ውስጥ ተጠብቀው ይገኛሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረ ሌላው የወረቀት ዐይነት፤ ብራና ከሚባል በተለየ ሁኔታ ለፍቶና ታሽቶ የተሠራ የፍየልና የበግ ቆዳ ነበር። ብራና ከፓፒረስ ይልቅ በጣም ውድ ሲሆን፤ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጥቂቶቹ በመጀመሪያ የተጻፉት ከብራና እንደነበረ ይገመታል። ይህ ከሆነ ደግሞ በደንብ ተጠብቀው አልተያዙም ማለት ነው። ሙሉው አዲስ ኪዳን በጣም ያረጀው ግልባጭ የተሠራው በአራተኛው መቶ ዓመት ላይ ነበር። የተጻፈውም በብራና ሲሆን ይህም ያረጀ ግልባጭ የተገኘው በ1800 ዓ.ም. መካከለኛ ላይ በግብጽ አገር በሚገኘው በሲና ተራራ በመነኩሳት ገዳም ውስጥ ነበር። ከዚህም ካረጀ ጥቅል ሌላ የግሪክ አዲስ ኪዳን ግልባጮች የሆኑ በብራና ላይ የተጻፉ ሌላ 270 ግልባጮች በአሁኑ ወቅት ይገኛሉ። የተፃፉትም በአራተኛና በዘጠነኛ መቶ ዓመታት መካከል ነበር።

ከዘጠነኛው መቶ ዓመት እስከ ዐሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት በግሪክ ብዙ ቋንቋ አዲስ ኪዳን ግልባጮች ተሠርተዋል፤ ከእነርሱም ከ2700 በላይ የሚሆኑ ግልባጮች እስከ አሁኑ ዘመን ተጠብቀዋል። ከዚያም በኋላ በ1456 ዓ.ም. ጆሐን ጎትንበርግ በተባለ በአንድ ጀርመናዊ አንድ ማተሚያ ተስራ፤ የመጀመሪያው የታተመ መጽሐፍ በመሆን መጽሐፍ ቅዱስ ታተመ። ከዚያ ጊዜ በኋላ መጻሕፍት በእጅ መገልበጣቸው አበቃ፤ በማተሚያ ቤቶች አማካይነት በፍጥነትና በቀላል ዋጋ ሊታተሙ ቻሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በብዙ ቋንቋዎች ይደረግ ስለነበር፥ አሁን መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ተራ ሰው እጅ ሊገኝ ቻለ። በዛሬ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከዓለም ቋንቋዎች 1200

---

[1] ፓፒረስ በግብጽ አገር የሚበቅል ረዘም ያለ የውሃ ተክል ነው። ከዚህ ተክል አገዳ በቀጫጭኑ ተቆርጦ በአንድነት ይቀመጣል፤ በአንዱ መደዳ ላይ ሌላ መደዳ ተደራርቦ በመጀመሪያው መደዳ ላይ ይከመራል፤ ፓፒረስ ዋና የወረቀት ዐይነት በመሆን ከክ.ል.በ. እስከ 3ኛ መቶ ዓመት ድረስ ይጠቀሙበት ነበር።

በሚያህሉት ተተርጉሞአል፤ በዓለም ታሪክ ውስጥ ይህን በሚያህል ቋንቋዎች የተተረጎመ ወይም ይህን በሚያህል ሕዝብ የተነበበ ሌላ መጽሐፍ ጨርሶ አይገኝም።

እነዚህ በመቶና በሺ የሚቆጠሩ ጥንታውያን ጽሑፎች እስከ አሁን ጊዜ ድረስ ተጠብቀው መቆየታቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው የግሪክ ጹሑፎች በትክክል ተገልብጦ ወደ እኛ ለመድረሱ ማረጋገጫ ነው። ምንም እንኳ አንዳንድ ጸሐፊዎች ሲገለብጡ አልፎ አልፎ ስሕተት ማድረጋቸው የሚታወቅ ቢሆንም ብዙዎቹ ጹሑፎች በአንድነት በሚጠኑበት ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች በእያንዳንዱ ሁኔታ ምን ለማለት እንደፈለጉ መወሰን ይቻላል። ይህን ያህል የጥንት ግልባጭ ያለው ሌላ የጥንት መጽሐፍ በጭራሽ አይገኝም። የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እግዚአብሔር አስቀድሞ ለመጀመሪያዎቹ ፀሐፊዎች የሰጣቸው ቃል ነው ብለን የምንታመነውም ስለዚህ ነው።

ዛሬ የሚገኙ መጽሐፍ ቅዱሶች ትክክለኛ መሆናቸውን የምናረጋግጥበት ሌላም በጣም ጠቃሚ የሆነ ምክንያት አለ። ይኸውም እግዚአብሔር ቃሉን ጠብቆ ለትውልዶች ሁሉ አንዲተላለፍ የሰጠው ተስፋ ነው (መዝ. 119፥89፤152፤160)። እግዚአብሔር ቃሉ እንዳይጠፋና መሠረታዊ ለውጥ እንዳይደረግበት በማድረጉ በጣም ልንተማመን እንችላለን።

## የአዲስ ኪዳን ቀኖና

ገና ከመጀመሪያው በአዲስ ኪዳን ቀኖና[2] ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው መጻሕፍት አንድ አጠቃላይ ስምምነት ተደርጎአል። በ200 ዓ.ም. አዲስ ኪዳን ያጠቃለላቸው መጽሐፍት አሁን እኛ ያሉን መጽሐፍ ቅዱሶች ከያዙት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ጋር አንድ ዐይነት ናቸው። ይሁን እንጂ በአንዳንድ መጻሕፍት ላይ አለመስማማት ነበር፤ ይህም አለመስማማት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ቀጠለ። በተለይ አንዳንድ ክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዕብራውያን፥ ያዕቆብ፥ 2ጴጥሮስ፥ 2 እና 3ዮሐንስ፥ ይሁዳና ራእይ መግባት አይኖርባቸውምን? ብለው ጠየቁ። ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ጽሑፎች በመጀመሪያው መቶ ዓመት ገደማ በአንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች የተጻፉ ሲሆኑ አንዳንድ ሰዎች በቀኖናት ውስጥ መግባት አለባቸው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ጨርሶ መግባት የለባቸውም ይሉነበር። በአራተኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ እነዚህ ሁሉ አለመስማማቶች ተወግደው ነበር። በዓለም ላይ የሚገኝ ቤተክርስቲያን በአሁኑ ዘመን የሚገኘውን አዲስ ኪዳን ቀኖና በሙሉ ልብ ተቀብለው አፈሲላዊ አድርገውት ነበር፤ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በአዲስ ኪዳን ቀኖና ውስጥ በሚገኘውም ክፍል አለመስማማት አልተፈጠረም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የትኛው መጽሐፍ መግባት አለበት ለሚለው ውሳኔ አራት መለኪያዎች ነበሩ። መጀመሪያ አንድ መጽሐፍ በሐዋርያ ወይም ለሐዋርያው ቅርብ ረዳት በነበረ ሰው መጻፍ ይኖርበታል። ሁለተኛ መጽሐፉ የያዘው ምስጢር ከፍተኛ መንፈሳዊነት ሊኖረው ይገባል፤ እንዲሁም ከብሉይ ኪዳን ትምህርትና ከሐዋርያት ትምህርት ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይገባል። ሦስተኛ መጽሐፉ ከአብያተክርስቲያናት አብዛኛው ክፍል ሊቀበለው ያስፈልጋል። አራተኛ መጽሐፉ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሊኖረው ያስፈልጋል። የትኞቹን መጻሕፍት በቀኖና ውስጥ ማስገባት እንደሚያስፈልግ ውሳኔ ሲደረግ የጥንት ቤተክርስቲያንን ትመራ የነበረው በመንፈስ ቅዱስ ነበር፤ ሰዎች በራሳቸው ውሳኔ ብቻ መጻሕፍትን መርጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማስገባት አይወስኑም፤ ይልቁንም መንፈስ ቅዱስ እየመራቸው የትኞቹ መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ ያሳያቸዋል።

## መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ ልዩ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት ልዩ የሆነበት ምክንያት፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያንን እግዚአብሔር ራሱ በቀጥታ በተለየ መንገድ ስለመራቸው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እግዚአብሔር እንዲጽፉ የፈለገውን ነገር የጻፉት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት ነበር (2ጢሞ. 3፥16፤ 2ጴጥ. 1፥21 እና ገለፃዎቹን ይመለከቷል)። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ቃል ብቻ አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔር የራሱ ቃል ነው።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ በሰዎች ተጠቅሞአል። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ቃል በመናገር እንዲጻፍ አላደረገም፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በራሳቸው አእምሮ ተጠቅመው ስለ ጻፉት የግለሰብ ስብእናቸውና ጠባያቸው በጽሑፎቻቸው ውስጥ ሊታይ ይቻላል። ልክ ኢየሱስ ራሱ በአንድነት እግዚአብሔርም ሰውም እንደነበረ፥ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ በአንድነት የእግዚአብሔርም ቃል፥ የሰውም ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የእግዚአብሔርን ሀሳብ በተለየ መንገድ በሚያውቁ ሰዎች ነው። እግዚአብሔር አሳቡን ገለጠላቸው፤ እነርሱም እግዚአብሔር በገለጠላቸው መሠረት ጻፉት። ሌሎች ክርስቲያን ጸሐፊዎች በአጠቃላይ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እግዚአብሔርን

---

[2] የአዲስ ኪዳን ቀኖና በግልጽ እውቅና ያገኙ የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ሲሆን በሁሉም ቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያገኘ ነው።

የሚያስደስቱ መጻሕፍትን መጻፋቸው እርግጥ ነው። ነገር ግን እነርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች የነበራቸውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ በተለየ መንገድ የማወቅ ችሎታ አልነበራቸውም። ከዚህም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ የተለየ ነው። የተገለጠና ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው፤ ምንም ስሕተት የለበትም። አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ «በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሕተት አገኘን» ይላሉ። በኋላ ግን የተሳሳቱት ራሳቸው እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልነበረ ይረዳሉ። በተደጋጋሚ ጊዜያት በታሪካዊና በከርሰ ምድር ምርመራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን እውነት አረጋግጠዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በታሪክም ሆነ በሳይንስ በሁሉ አቅጣጫ ተመርምሮ እውነተኛነቱ ተረጋግጦአል።

ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን የታሪክ ወይም የሳይንስ መጽሐፍ እንደምናነበው ማንበብ ብቻ በቂ አይደለም። በአእምሮአችን ብቻ ተጠቅመን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብ በቂ አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈሳችን ጭምር ማንበብ ይኖርብናል፤ አለበለዚያ ግን የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥቅል መንፈሳዊ እውነት ለማወቅ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ በትሕትና ራሳችንን ዝቅ አድርገን የእግዚአብሔርን እውነት ለመቀበል የተከፈተ አእምሮ ሊኖረን ያስፈልጋል። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ማስተዋል እንዲሰጠን መጸለይ ይኖርብናል። ይህንንም በእምነት በምናደርግበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ሕያው ይሆናል፣ ሕይወታችንንም ይለውጠዋል።

መጽሐፍ ቅዱስን ሕያው ሊያደርግና በአንባቢው ልብ ውስጥ ኃይለኛ ሊያደርገው የሚችል መንፈስ ቅዱስ ነው (2ቆሮ. 3፥6)። መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው የሚኖር ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛና ሕያው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በውስጣቸው ሊረዱ ይችላሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ወይም ክርስቶስ ማን እንደሆነ በእርግጠኝነት ሊያውቁ ይችላሉ። እግዚአብሔር ያደረገውንም ነገር ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ሊያውቁ ይችላሉ። ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰዎችን ለመገናኘት ያደረገውንና የሰዎችንም እምቢተኛነትና ኃጢአት መዝግቦ የያዘ ነው። ብሉይ ኪዳን በግልጥ የሚያሳየው ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውንና አዳኝም እንደሚያፈልጋቸው ሲሆን አዲስ ኪዳን ገልጦ የሚያሳየው ደግሞ ሰዎችን የወደደ አምላክ መኖሩን ነው። ይህ አምላክ ሰዎችን በጣም ከመውደዱ የተነሣ ራሱ ወደ መሬት መጣ፣ የመጣውም በሰው አምሳል ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳንና የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት ነው። መክራ ተቀበለ፥ ሞተም።

አንባቢ ይህንን መጽሐፍ በሚያጠናበት ጊዜ እግዚአብሔር ከቅዱሳት መጽሐፍ ያስተምረው ዘንድ ራሱን እንደሚያዘጋጅ ይታመናል። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ብቻ ሳይሆን እንኖርበትም ዘንድ ግድ ነው።